# ሐመር

## ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር 1 መጋቢት 1986 ዓ.ም.



ከጣና ሐይቅ ደሴቶች አንዱ




- ስለ ክርስቶስ የተቃዋሚዎች ጥያቄና መልሶቻቸው ........
- ወደ ምስራቅ ተመልከቱ.....
- ቬንስያ ................
- ማዳኑን ያዩ ይናገሩ ...
- የጣና ሐይቅ ዕንቁዎች ....

በመገለጥ ላይ መገለጥ ....

- ክፉ ባልንጀርነት ....
- ምክንያተኝነት.......

መዳን በክርስቶስ ነው እንዴት? ....

- እናቶች በቤተ ክርስቲያን....
- ቅዱሱን ኪዳን አስበ ....


©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org



«የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል አለው ጌታም ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም አለው»

ማቴ. 4 ፡ 4 ።

«የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ ወደ ታች ራስህን ወርውር አለው ኢየሱስም ጌታን አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ ደግሞ ተጽፎአል አለው»

ማቴ. 4 ፡ 7 ።



«ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው ያን ጊዜ ኢየሱስ ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና አለው ።

ማቴ. 4 ፡ 11



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# ሐመር

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር 1
መጋቢት 1986 ዓ.ም.

## ይዘት

ከአዘጋጁ ............................ 1
የማኅበሩ መልእክት ............... 2
ደብዳቤዎች ........................ 3
ትምህርተ ሃይማኖት
- ስለ ክርስቶስ የተቃዋሚዎች ጥያቄና መልሶቻቸው ............. 4
- ወደ ምስራቅ ተመልከቱ........... 7
- ዐቢይ ጾም ......................... 8
- እመ አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ ........... 9

ኪነጥበብ
- ቬኒስያ ............................10
- ማዳኑን ያዩ ይናገሩ ...............12

እናስተዋውቃችሁ
- የጣና ሐይቅ ዕንቁዎች .............15
- አባ ሳሙኤል ዘደብረ ቀልሞን...18

በመገለጥ ላይ መገለጥ ...........19
ዓምደ ወራዙት
- ክፉ ባልንጀርነት ....................21
- ምክንያተኝነት.........................23

መዳን በክርስቶስ ነው እንዴት? .............. 24
ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ
- እናቶች በቤተ ክርስቲያን. .......26
- ለወላጆች ..............................29

በረከተ ወንጌል
- ቅዱሱን ኪዳን አሰበ .............30

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ የሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የመዝሙርና ሥነ ጽሑፍ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ።

# ከአዘጋጁ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

«እነሆ ከደመና ጋር ይመጣል ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ። አዎን፣ አሜን። ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ :- አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ ይላል።»

ራእይ 1፥7–8።

## ሐመር አንደኛ ዓመትዋን አከበረች፥

የሐመር ደንበኞች እንኳን ለመጽሔታችን ሁለተኛ ዓመት መጀመሪያ ኃያሉ አምላክ በሰላምና በጤና አደረሳችሁ አደረሰን።

ሐመር መጽሔታችን ወደ ምእመናን ብቅ ማለት ከጀመረችበት ከጥር 1985ዓ.ም. ጀምሮ የተለያዩ መንፈሳዊ ትምህርቶችንና ዕፁብ ድንቅ የተሰኙ ታሪካዊ ቦታዎችን ስታስተዋውቃችሁ ከርማ ዛሬ ሁለተኛ ዓመትዋን ይዛለች።

በዚህ የአንድ ዓመት የሐመር ጉዞ ከእናንተ አንባብያን የደረሰን ገንቢ ሒስና የማበረታቻ መልእክት ለእኛ ለአዘጋጆቹ ብርታትና ጥንካሬ እንደሰጠን ሳንጠቅስ አናልፍም። አሁንም እንደወትሮአችሁ ከእኛ ጋር እንደምትሆኑ እምነታችን ነው።

እስከ መጨረሻ የሚጸና እርሱ ይድናል ነውና ወንጌሉ የሚለው፣ እኛንም አምላክ እስከመጨረሻው ያበረታን ዘንድ በጸሎትም ሆነ በሐሳብ እንዳትለዩን እየጠየቅን ዓመታዊ ክብረ በዓልዋን ምክንያት በማድረግ ሐመር መጽሔት ይዛላችሁ የቀረበችውን ግብዣ እነሆ እንላለን።

ዋና አዘጋጅ – ብርሃኑ ጎበና ካሣ
ም/ዋና አዘጋጅ – ዲ.እሸቱ ታደሰ ወ/አገኘሁ
✉ 80078
☎ 11 07 54
አዲስ አበባ

## የማኅበሩ መልእክት

# የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በእውነት ክርስቶስን አትሰብክምን?

ራሷና ጉልላቷ ኢየሱስ ክርስቶስ የሆነው ሐዋርያዊቱ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት ብዙ መከራዎችን አሳልፋለች። ከውጭ በአላውያን ነገሥታት፥ ክርስቶስን በማያምኑ አሕዛብ፥ ከውስጥ ደግሞ በመናፍቃን ስትፈተን ኖራለች። ነፋሱ ነፈስ ጐርፍም ጐረፈ መሠረቷ ክርስቶስ ነውና አልተናወጠችም፥ አስቀድሞ መድኃኒታችን

«የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም» ብሎ ተናግሯልና። ማቴ.16፥18።

ዘመን እየተለወጠ በሄደ ቁጥር የመከራውና የፈተናውም ዓይነት እየተለወጠ መሄዱ የተለመደ ነው። በዚህም መሠረት በዘመናችንም ፈተናው ለቤተክርስቲያን አልቀረላትም። በክርስትና ስም የመጡ ተኩላዎች በጐቿን እያደቡ ሲነጥቁ፥ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት የካዱ ተረፈ-አርዮሳውያን በገንዘብ ኃይል ምእመናኖቿን ሲያስኮበልሉ፥ ተመሳስለው ወደ በረቷ የገቡ ይሁዳውያን ደግሞ ምእመናኖቿን በማመስ ላይ ይገኛሉ። የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን «ክርስቶስን አትሰብክም» እያሉም ሲናገሩ ይሰማሉ።

ለብዙ ዘመናት በመንበሯ ሲፈተት የነበረው ሥጋና ደም የማን ይሆን? ስታጠምቅስ የነበረው በማን ስም ይሆን (በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም) ማቴ.28፥19። በዱር በገደሉ ግርማ–ሌሊቱን፥ ድምፀ–አራዊትን፥ ጸብአ–አጋንንትን ታግሠው ሲጋደሉ የኖሩት ቅዱሳን አባቶቻችንስ በማን ስም ነው?

በውዳሴዋና በዝማሬዋ እንዲሁም በቅዳሴዋ ያለማቋረጥ ኢየሱስ ክርስቶስን ለዘመናት ስትሰብክ የኖረችውንና ዛሬም የምትሰብከውን ቤተክርስቲያን ‹ጌታን አታውቅም፥ አትሰብክም ማለቱ «ልጅ ለእናቷ...» አይሆንባቸውምን? በውዳሴ ማርያም «ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ዘተሰብአ እምኔኪ... ከአንቺ ሰው የሆነና በኛ ያደረው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» እያለች፥ ዳግመኛም «ዘሀሎ ወይሄሉ ዘመጽአ ወካዕበ ይመጽእ ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ዘተሰብአ እምኔኪ...» «የነበረው፥ ዳግመኛ የሚመጣው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ያለመለወጥ ከአንቺ ፍፁም ሰው ሆነ...» (የሰኞ ውዳሴ ማርያም) ብላ ምሥጢረ ሥጋዌውንና፥ ዮሐንስ አፈወርቅም በቅዳሴው «የማይሞተው ሞተ፥ ሞትን ይሽረው ዘንድ ሞተ፥ ሙታንን ያድናቸው ዘንድ ሞተ» (ቁ58) ብሎ እንደተናገረው ሁሉ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም የተወለደው በቀራንዮ አደባባይ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ያዳነን መድኃኒተዓለም ክርስቶስ መሆኑን ለዘመናት አስተምራለች። በቃል ብቻ ሳይሆን በደምም መስክራለች። ካህናት አባቶቻችንም በማኅሌታቸው ዘሰተይከ በእንቲአነ ከርቤ ወሐሞተ በሞተ ዚአከ ከመትቅትል ሞተ። «በሞትህ ሞትን ታጠፋ ዘንድ ስለኛ ስትል ከርቤንና ሐሞትን ጠጣህ» በማለት ፍፁም አምላክ የሆነ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ በፈጸመልን መሥዋዕትነት ሞት እንደተወገደልን ይመሰክራሉ። በሰዓታት አባ ጊዮርጊስ «አ አምላክ መድኃኒዓለም አምላክ አዳም፥ ኢየሱስ ንጉሠ ሰላም ፈውሰነ እምሕማም» አቤቱ አምላካችን መድኃኒዓለም አንተ የአዳም አምላክ የሰላም ንጉሥ የሆንከው ኢየሱስ ሆይ በኃይልህ ከሕመም ፈውሰን። ያለውን በመያዝ ዛሬም ቤተክርስቲያናችን የኢየሱስ ክርስቶስን የሥጋና የነፍስ መድኃኒትነት ትሰብካለች–ታስተምራለች።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ በቅዳሴው «አቤቱ ሞትህን፥ ቅድስት ትንሣኤህንም እንነግራለን፥ ዕርገትህን ዳግመኛም መምጣትህን እናምናለን።» (ቁ.37) ብሎ እንደተናገረው የጌታችንን ሞቱንና ትንሣኤውን እንዲሁም ዕርገቱንና ዳግመኛ መምጣቱን መናገር የክርስቲያኖች ተግባር ነውና ቤተክርስቲያናችን ይህን ትመሰክራለች።

እንግዲህ አንዳንድ አላዋቂዎች የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን «ክርስቶስን አትሰብክም» ማለታቸው ከየት ያገኙት ይሆን? ምናልባት እነርሱ እንደሚሉት ክርስቶስ አማላጅ፥ ክርስቶስ ፍጡር፥ ክርስቶስ ታናሽ አምላክ ወይም ክርስቶስ ከነቢያት እንደ አንዱ ብላ አለማመኗ ይሆን? ወይስ ክርስቶስ «የነበረ፥ ያለ የሚኖር ዘለዓለማዊ ሁሉን ቻይ አምላክ» ራእ.1፥8። በፈቃዱ የሞቱትን ያድናቸው ዘንድ የሞተ፥ ዮሐ.10፥18። የተቀበሩትን ያስነሣቸው ዘንድ የተቀበረ፥ ሕያዋንንም ይጠብቃቸው ዘንድ ያደፉትን ያነጻቸው ዘንድ ኃጥአንንም ያጸድቃቸው ዘንድ የበደሉትንም ወደ ክብር ወደ ጉትንት ይመልሳቸው ዘንድ ሞትን ድል አድርጐ የተነሣ» 1ቆሮ.15፥20። ብላ ማመኗ እንዲሁም ደግሞ «እኔ የአብርሃም፥ የይስሐቅ፥ የያዕቆብ አምላክ ነኝ ያለ እርሱ ዘጸ.3፥15። በኋለኛው ዘመን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በቀራንዮ ተሰቅሎ እንዳዳነን ለመመስከር አምላከ ቅዱስ ጊዮርጊስ፥ አምላከ ቅዱስ ተክለሃይማኖት፥ አምላከ ቅዱስት ክርስቶስ ሠምራ...እነርሱን የመረጠ የቅዱሳን አምላክ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን» እያለች መናገሯ ነው። ክርስቶስን አልሰበከችም ያሰኛት?

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን አልሰበከችም ማለታቸው በስውር ለያዙት ዓላማቸው ሽፋን እንጂ በእውነት ቤተክርስቲያናችን ክርስቶስን ሳትሰብክ ቀርታ አይደለም። መሠረቷስ ማን ሆነና? አንዳንዶች «ኢትዮጵያ ለሦስት ሺህ ዓመታት እጆቿን ወደ እግዚአብሔር አልዘረጋችም ክርስቶስንም አልሰበከችም» ብለው መናገራቸው የዚህችው ቤተክርስቲያን ልጆች ነን ባዮችም ይህንን ቃል ማስተጋባታቸው ከማስደነቁም በላይ ከበስተጀርባ ያላቸውን የዓላማ አንድነት ያመለክታል።

ስለዚህ «...ይህን አስቀድማችሁ ስለምታውቁ በዓመጸኞች ስሕተት ተስባችሁ ከራሳችሁ ጽናት እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ።» 1ጴጥ.3፥17።

ከዚህ አንፃር ማኅበራችን እውነተኛይቱ ቅድስት ቤተክርስቲያን የምትሰብከውን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት እንዲሁም ሥርዓቷንና ትውፊቷን ሙሉ በሙሉ በመቀበልና ይህንኑ ለምእመናን በማስተማር የመናፍቃንን ግልጽም ሆነ ሥውር ትምህርት ይቃወማል።

ውድ አንባብያን! በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ስም ተመሳስለው ገብተው ቤተክርስቲያንን ለማፍረስና በጐቿንም በኑፋቄ መርዝ ለመመረዝ የተነሡትን የውስጥ መናፍቃን ስውር ዓላማ በሚቀጥለው እትማችን እናስነብባችኋለን።

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ አበዊነ!



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ደብዳቤዎች

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

## ለሐመር መጽሔት አዘጋጆች በሙሉ

ከሁሉ አስቀድሞ ቸርነቱ የማያልቅበት አምላክ ክብር ምሥጋና ይድረሰው አሜን። ባለፈው እትማችሁ በቁጥር 7 ላይ በኪነጥበብ ዓምድ ቬኒስያ የሚለው መጣጥፍ ልብን እንጠልጥሎ ይቀጥላል ስለተባለ በጣም ያጓጓል። የሚቀጥለው እስኪወጣም ያለውን ጊዜ የዓመት ያህል አስረዝሞብናልና እባካችሁ እንደዚህ ዓይነት ጽሑፍ ስታቀርቡ በአንድ እንዲያልቅ ብታደርጉት የተሻለ ነው። እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን

የሺጥላ ሰሎሞን – (ከመልካ ሰዲ)

አሜን ስለሰጠኸን አስተያየት ከልብ እናመሰግናለን። ነገር ግን ምን እናድርግ ታሪኩ ረዥም ስለሆነብን ነው እና ለርስዎ ትዕግስቱን እንዲሰጥዎትና በተከታታይ እንዲያነቡ ብቻ ነው የምንጸልይሎት በአስተያየቱም ይግፉበት።

✣ ✣ ✣

## ውድ የሐመር መጽሔት አዘጋጆች

ፀጋና ሰላም ይብዛላችሁ

መጽሔታችሁና ከዕለት ወደ ዕለት የእግዚአብሔርን ቃል ጥማችንን በማርካትና በሃይማኖታችን ለመጽናት መሠረት እየሆነችን ስለሆነ በርቱልን እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን የእመቤታችን ምልጃ ይጠብቃችሁ።

መ/ር በላይነህ ደስታ – (ከአጋዬን)

አሜን። አንተም በተሳትፎህ አትለየን

✣ ✣ ✣

## ለሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል

ከፀሐይ መውጫዋ እስከ መግቢያዋ ድረስ የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን። የአምላካችን የልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ የእናታችንን የቅድሳት ቤተ ክርስቲያንን እንደበት ርቀን ከምንገኝበት ከባሕር ማዶ ድረስ በ«ሐመር» አማካይነት አስትምራችሁናልና ለመጽሔታችሁና ለአዘጋጆች ለእናንተ ምሥጋናችን ከፍ ያለ ነው።

ከሀገር ርቀን የምንኖር በመሆኑ በየወሩ እትማችሁን እንደልብ አግኝተን ለማንበብ ባንችልም አልፎ አልፎ የሐመር ገበታ ተቋዳሾች ነን ሐመር ከዳር እስከዳር ትምህርት ሰጪ በመሆኗ የእናንተ የአዘጋጆች ልፋት ፍሬያማ መሆኑን ይመሰክራል በርቱ ጥረታችሁ አይቋረጥ እንላለን። እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን በጸሎታችን ከእናንተ ጋር ነን፤ እናንተም አስቡን።

የቅድስት ማርያም መንፈሳዊ ወጣቶች ማኅበር – ሞስኮ (ራሺያ)

አሜን። እናንተበርቱልን እንጂ አይዟችሁ እንተሳሰባለን መጽሔቷም እንዳትቋረጥባችሁ ከዚህ ከአገር ቤት ተከታትሎ የሚል ክላችሁ ሰው ፈልጋችሁ ጻፉለት።

✣ ✣ ✣

## ለሐመር መጽሔት አዘጋጆች በሙሉ

በመጀመሪያ የከበረ ሰላምታዬን አቀርባለሁ። መጽሔታችሁ በንፍር ውኃ ልንጠፋ የተቃረብነውን እንደ ኖኅ ሥጋዊ መዳን ሳይሆን በኑፋቄ ማዕበል ልትጠፋ የተቃረበችውን ነፍሳችንን እያዳነችን ነውና ግፉበት በተለይም «መጽሐፈ ጨዋታ» ብላችሁ ታወጧት የነበረችውን ከፈገግታ ጋር የምታስተምረውን ጽሑፋችሁን ቀጥሉባት። የእግዚአብሔር ቸርነት የቅዱሳን ጸሎትና ምልጃ አይለያችሁ።

ዲ/ንዋይ ገብረሐና – (ጅጅጋ)

ውድ ወንድማችን በተሳትፎአችሁና በጸሎታችሁ አትለዩን እንጂ እናንተን ለማስደሰት የተቻለንን ሁሉ እናደርጋለን ምርቃቷንም አሜን ብለን ተቀብለናል።

✣ ✣ ✣

## ለሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል

እስከአሁን ያወጣችኋቸው እትሞችና ዓምደ ሃይማኖትና ኖኅተ ሃይማኖት መጻሕፍት በጣም አርክተውኛል። በእምነታችንም እንድንጸና ረድተውናልና በርቱልን አደራ ያከይሲ ዲያብሎስም መሃላችሁ እንዳይገባና ሥራችሁን እንዳያደናቅፍ የዘወትር ጸሎታችን ነው። እግዚአብሔር ዛሬ እንዳስጀመራችሁ ለፍፃሜ ያድርሳችሁ።

አበራ በቀለ እና ንጉሱ
ከኢት/ቡና ገበያ ኮርፖሬሽን – አ/አ

አሜን በጸሎትህ በተሳትፎህም በርታልን መጽሔቷንም አንተ እንዳነበብክ እንደረካህባት ለሌሎች አድርሳት።

✣ ✣ ✣

## ውድ ሐመሮች!

በቁጥር «7 መዝሙርና ምስጢራዊ ሥርዓቱ» በሚለው ጽሑፍ ቤተ ክርስቲያናችን ቀደምትና በሥርዓት የምትመራ መሆኗን በሚገባ ገልጾልናል። አርክቶናልም። በተረፈ ይህንን ዓይነቱን በቤተ ክርስቲያን ንዋየ ቅዱሳት ላይ መፃፉን አትርሱ ለወደፊት ጽሑፍ ይገፍ ብቅ እላለሁ ለሁሉም እግዚአብሔር ያበርታችሁ።

ከመዝሙረ ዳዊት – ቦንጋ ከተማ (ከፋ)

መዝሙረ አይዞህ ከዚህች መጽሔት ጀምሮ አምድ ከፍተን ያልከንን ጀምረናል። አንተም ቃልህ አይታጠፍብን።

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ 1ዱ አምላክ አሜን።

ስለሥራችሁ እግዚአብሔርን እያመሰገንኩ በ2ዮሐ.1፥4–5 ያለው ለማን እንደተነገረና ማንበቡን ብንችል በማናውቀው የግዕዝ ቋንቋ የምናቀርበው ጸሎት እንደጸሎት ይቆጠራል የሚሉትን ጥያቄዎች እንድትመልሱልን እጠይቃለሁ።

ግዛቸው አበራ (ሰሜን አሞ)

✣ ✣ ✣

የመጀመሪያው ጥያቄ መልስ ዮሐንስ «እመቤት ሆይ» ብሎ የጻፈላት ሮምና ለተባለች ሴት ነው ይህች ሴት በትርጓሜ መጻሕፍት (ሰልስቱ ሀዲሳት) እንደሚነገረው ቀደሞ ጣዖት አምላኪ ኋላ ግን ዮሐንስና አብሮኮሮ ከዚህ ጣዖታዊ ሕይወት አውጥተው ክርስቲያን አድርገዋታል። እርሷም ቤቷን የሐዋርያት ማረፊያ በማድረግ ታገለግል ነበር። እርሱም ቀድሞ «እመቤት» እያለ ነበርና ያሚጠራት ሲጽፍላትም «እመቤት ሆይ» ብሎ ጽፎላታል።

በግዕዝ የምንጸልየው ጸሎት እንደጸሎት ይቆጠራል ወይ ለሚለው አዎን ነው መልሳችን። ለዚህም በ1ቆሮ.14፥16 ቅ/ጳውሎስ የተናገረውን ተመልከት።

ከዚህ በታች ስማችሁ የተዘረዘረ የመጽሔታችን አንባቢዎች ጥያቄዎቻችሁ ጽሑፎቻችሁና አስተያየታችሁ ደርሰውናል። ስለአስተያየታችሁ እናመሰግናለን። ጥያቄዎቻችሁንም በሚመለከተው ዓምድ ስር ወደፊት እየጠበቅን እናወጣለን። ቅዱሳን እንዲራዱን በጸሎታችሁ እያሰባችሁን በትዕግስት ጠብቁን።

ተማሪ ውድነሽ ወርቁ (ግቢ ገብርኤል)፣ ወጣት ተክሉ አበራ/ባሎ ደይላ/፣ ሽታ ቡዙዬ/ቡሬ ቅ.ዮሐንስ ሰ/ት/ቤት፣ መ/ር ጥላሁን ዓለማየሁ (ሽሬ ኪዳነምህረት ሰ/ት/ቤት) ወለተማርያም ሽፈራው አ.አ./መ/ር እንዳለ ገመቹ (አርሲ ጢቾ) ጌድዮን በየነ (ሐረር)፣ የባቲ ቅ/አማኑኤል ሰ/ት/ቤት ተማሪዎች (አለማያ) አባ ገ/ኪዳን እጅጉ (አዋሽ አርባ) ይርጋ ዓለም አስናቀ (አ.አ) ወንድሜ አበራና ሳሙኤል አዳነ (አ.አ.) መ/ር አበበ አሰፋ (ሲሬ ወለጋ) መኳንንት ዘርይሁን (ፍኖተ ሰላም ጐጃም) ተማሪ ታሪኩ ጋርኮበ (መተግራ) እውነቴ ተስፋዬ (አ.አ.) መኮንን አሳዬ (ፊፀዥጪአ ወለጋ) አበባው ዘውዱ (አ.አ.6ኪሎ) ዲ/ዮሴፍ ወልደ (ግደበረት ከ ሲ/ ደረጀ አባይነህ (ባሌ ሴፍ ታ) ሌሎችም ወደፊት የምናወጣቸው ለአንባቢዎቻችን! የምትልኳቸው ግጥሞች ከ10ስንኝ ያልበለጡ ትምህርታዊ ጽሑፎቻችሁም ከ500 ቃላት ያልበለጡ መሆን አለባቸው።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ትምህርተ ሃይማኖት

ይህ ዓምድ ስለ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ትምህርተ ሃይማኖት (ዶግማና ቀኖና) የምንማርበት ነው።

## የክርስቶስ ተቃዋሚዎች የሚያቀርቡዋቸው ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

● ካለፈው የቀጠለ

ከብርሃኑ ጎበና

1 ጢሞ 2፥5። «አንድ እግዚአብሔር አለና በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።»

ብዙ ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስን አማላጅ አድርገው የሚያቀርቡ ክፍሎች የሚጠቅሱት ጥቅስ ነው።

ክርስቶስ አማላጅ ወይስ ተማላጅ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በቅድሚያ የምልጃን ትርጉም ማወቅ ይገባል። አማላጅ የሚለው ቃል ትርጉም ለማኝ፣ አስደራጊ፣ ጸላይ ማለት ነው። ከእርሱ በላይ ላለው ለምኖ የሚያስደርግ ነው። ተማላጅ ሲባል ደግሞ አድራጊ፥ ሠሪ፥ ፈጣሪ፥ ተለማኝ ማለት ነው። በሥላሴ ትምህርት ላይ አብ ከወልድ አይበልጥም፥ ወልድም ከመንፈስ ቅዱስ አይበልጥም፤ በሥላሴ ዘንድ የሥልጣን ተዋረድ እንደሌለና በሥልጣን፣ በአገዛዝ፣ በመለኮት፣ በባሕርይ አንድ መሆናቸው የተረጋገጠ ከሆነና በሥላሴ ትምህርት አምናለሁ የሚል ሰው ወልድን (ኢየሱስ ክርስቶስን ለማኝ) (አማላጅ) አብን ተማላጅ አድርጐ ከቀረበ በሥላሴ ትምህርት ላይ ያለው እምነት እንደ አርዮስ የተሳሳተ ነው ማለት ነው። ወልድን ከአብ አሳንሶ ያስተማረ አርዮስ ነውና።

በሥላሴ ዘንድ መበላለጥ ከሌለ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ወደ አባቱ ለምን ጸለየ? «አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» ሉቃ. 23፥ 34። የሚለውንና የመሳሰሉትን ልመናዎች እንዴት ሊያቀርብ ቻለ?

የዚህን ጥያቄ መልስ ለመመለስ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሰው የመሆን ምሥጢር ዓላማ ማወቅ ያሻል። ይህም ስለ ጌታ ሰው መሆን ከመናገራችን አስቀድሞ ሰው እንዲሆን ያደረገው ምንድር ነው? ወደሚለው ጥያቄ ያመራናል። ምንም እንኳን ይህ ርእስ እንደ ባሕር የጠለቀና በዚህ ጽሑፍ ተንትነን የምንዘልቀው ባይሆንም በመጠኑ ለግንዛቤ ያህል ልንገልጽ እንወዳለን።

በመለኮታዊ ባሕርይ አንድ ከሆኑት ከሦስቱ አካላት አንዱ እግዚአብሔር ወልድ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥቶ (ወስዶ) ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው እንዲሆን ያደረገው የአዳም መበደልና ኋላም መፀፀቱ ነው።

እግዚአብሔር አምላክ ከእርሱ የተጣላውን አዳምን ከእራሱ ጋር ሊያስታርቀው በፈለገ ጊዜ አዳም በበደለው ሁሉ እርሱ (እግዚአብሔር) ስለ አዳም ተገብቶ (ተወክሎ) ካሣ ሊከፍልለትና ፍጹም ድኅነትን ሊያጎናጽፈው በመሻቱ አዳምን ከወደቀበት የጐስቁልና ሕይወት ወደ ቀደመ ክብሩ መመለስ አዳም የወደቀበትን ቦታ ሁሉ አስሷል።

እግዚአብሔር ወልድ ስለ አዳም ለመካሥ ወደዚህ ዓለም በመጣበት ጊዜ ልደቱን ያለ ወንድ ዘር አደረገው፤ ስለምን ቢሉ በዘር በሩካቤ ተወልዶ ቢሆን ዕሩቅ ብእሲ (አምላክነት የሌለው) ለሚለው ለአይሁድና ለመሰል ክፍሎች ምክንያት በሆን ነበርና። በዚሁም ላይ ድንግልና ከሌላት ሴት መወለድ ሲችል ከድንግል መወለዱ በአንድ ወገን «ድንግል በድንግልናዋ ትፀንሳለች በድንግልናዋ ትወልዳለች» ኢሳ.7፥14። የሚለውን ትንቢት ሊፈጽም ሲሆን በሌላ ወገን ደግሞ ከኅቱም ምድር ለተገኘው ለአዳምና ከኅቱም ገቦ (ጐን) ለተገኘች ሔዋን ካሣ ለመክፈል (ለማዳን) የመጣ መሆኑን ሲያስገነዝበንም ነው። እንግዲህ ከፅንሰቱ ጀምሮ አመጣጡ ለአዳምና ለልጆቹ ቤዛ ለመሆን፥ ካሣ ለመክፈል መሆኑን እየገለጠልን ነው የመጣው። በእመቤታችን ማኅፀን በተፀነሰ ጊዜ ዲያብሎስ ከዚያ በፊት በማኅፀን ሰዎችን ሁሉ ይቆራኝ ነበር፥ በጌታ ግን የማኅፀን ቁርኝት ቀረ። ዲያብሎስ ሊቆራኘው አልቻለም አዳምን ከዲያብሎስ ሊያላቅቅ የመጣ ነውና። እንግዲህ ካሣ የተጀመረው በማኅፀን መሆኑን ልብ ልንል ይገባል።

ልደቱንም በቤተ መንግሥት አላደረገም። አመጣጡ ልዩ ከሆነችው ከገነት ወጥቶ በጐስቋላ ሕይወት የወደቀውን አዳምን ነፃ ለማውጣት ለአዳምና ለልጆቹ ካሣ ለመክፈል ነውና በከብቶቹ ግርግም በትናቀው ሥፍራ አደረገው። በእርሱ ውርደት እኛን ሊያከብር።

መሰደዱም ለካሣ ነው። በጥፋቱ ከገነት የተሰደደውን አዳምን በእራሱ (በጌታ) ስደት ወደቀድሞ ቦታው ወደ ገነት ሊመልሰው ነውና የመጣው። በዚህም አዳም ያጣትን ገነት አግኝቷል።

በ30 ዘመኑ በዮርዳኖስ ወንዝ መጠመቁም እንደ እኛ ልጅነትን ሊያገኝበትና ሊከብርበት ሳይሆን ለአዳም መካሡንና በዮርዳኖስ ወንዝ ተቀብሮ የነበረውን የዕዳ ደብዳቤ ለመደምሰስ ነበር። አዳምና ሔዋን ፈጣሪያቸውን አሳዝነው ከገነት ከወጡ በኋላ ዲያብሎስ በጨለማ ጋርዶ ፍዳ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

አጽንቶ «አዳም የዲያብሎስ ወንድ አገልጋይ ነው። አዳም ገብሩ ለዲያ ብሎስ ሔዋን ደግሞ የዲያብሎስ ሴት አገልጋይ ናት ሔዋን አመቱ ለዲያብ ሎስ» ብላችሁ ስመ ግብርናችሁን ጽፋችሁ ስጡኝ ብሏቸው ነበር። እነርሱም ፍዳ የሚቀልላቸው መስሎ አቸው እንዳላቸው አደረጉ። ዲያብ ሎስም ያንን የዕዳ ደብዳቤ አንዱን በሲኦል ሌላውን በዮርዳኖስ አኑሮት ነበርና በጥምቀት ጊዜ በዮርዳኖስ የነበረውን የዕዳ ደብዳቤ ሲጠመቅ ረግጦት ደምስሶታል። ቆላ.2፥14።

በሠላሳ ዘመኑ መጠመቁ፥ ከሠላሳ ዘመን ሳያስበልጥ ሳያሳንስ ሠላሳን ጠብቆ ጥምቀቱን ማድረጉም አዳም የሠላሳ ዘመን ጐልማሳ ሆኖ ተፈጥሮ በአርባ ቀን ያገኛትን ልጅነት አስወስ ዷልና ለእርሱ ሊክሥ የመጣ መሆኑን ሊያስረዳን ነው።

ከተጠመቀም በኋላ ዕለቱን ልዋል ልደር አላለም፥ ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ ገብቶ ከዘረጋበት ሳያጥፍ ከቆመበት ሳይቀመጥ 40 መዓልትና 40 ሌሊት ጾመ፥ ከዲያብሎስም ተፈተነ፥ ዲያብ ሎስንም ድል አደረገው። ወደ ገዳም መሄዱ፥ ከዚህ ዓለም ውጭ በምትሆን በገነት አዳም ድል ተነሥቶ ነበርና እሱም ጌታ ከዚህ ዓለም ውጭ (በመን ፈሳዊ ሕይወት) በምትሆን በገዳም ዲይብሎስን ድል ለመንሣት። እንዲ ሁም በመብል ምክንያት ኃጢአት ወደ ዓለም (ወደ አዳም ሕይወት) ገብቶ ነበርና መብልን በመተው በጾም ወደ ዓለም የገባውን ኃጢአት ለማራቅና ለእኛም አብነት ለመሆን፤ ሰይጣን ድል የሚሆነው በጾም እንደሆነ ሊያስገነዝበን ነው።

ዓርብ ሊሰቀል ሐሙስ በጌቴሴ ማኒ በጸለየው ጸሎት በመከራችንና በፈተናችን ወቅት ልናደርገው የሚገባን ምን ዓይነት ድርጊት እንደሆነ አብነት ሆኖናል፥ እንዲሁም አዳም ዕንባውን ጨርሶ ደም እስኪያ ነባ ጌታው ይምረው ዘንድ አልቅሶ ነበርና ስለ አዳም ፍጹም ካሣ ሊክሥና ሐዘኑ መና እንዳልቀረ ሊያሳውቀው «ከብርቱ ጩኸትና ከዕንባ ጋር ጸሎ ትንና ምልጃን አቀረበ» ዕብ.5፥6።

በዕለተ ዓርብ እርቃኑን በመስቀል ላይ እንደ ብራና ተወጠረ። እራፊ ጨርቅ እንኳ በአካሉ ላይ አልነበረም። ጌታ እርቃኑን ሊሰቀል አይሁድ እርቃኑን ሆኖ እያዩት ይሣለቁበት ዘንድ ለምን ፈቀደ? መላእክት የእሳት መጋረጃ ሊጋርዱለት እንዳይችሉ አይሁድ ከልክለዋቸው ይሆን? አል ነበረም። ሰው መሆኑ ዋናው ምሥ ጢሩ ዕፀ በለስን በልቶ ጸጋውን ተገፎ እርቃኑን ቀርቶ ከገነት ለተባረረው ከእርሱ ለተጣላው አዳም የቀደመ ክብሩን ሊመልስለትና ጸጋውን ሊያጎ ናጽፈው የመጣ መሆኑን ሊያረጋ ግጥልን ነው።

በዚህም በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ ግርማአይሁድን በዓይኑ ተመለከተ፥ እግሩና እጁንም ተቸነከረ፥ መራራ ነገርንም በአፉ ተጐ ነጨ፥ ግን አልዋጠውም ተፋው። አዳምና ሔዋን በዓይናቸው ዕፀ በለስን አይተው ምኞትና መጐምጀት አድሮ ባቸዋልና ለስህተት ላበቋቸው ዓይኖ ቻቸው ሊክስ የመጣ ነውና በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ ግርማአይሁድን አየ። በዓይናቸው ያይዋትን በለስ በእግራ ቸው ሄደው በእጃቸው ቀጥፈው በአፋ ቸው በልተዋልና ጌታም ለእነርሱ ሊክስ መጥቷልና እጁና እግሩን ተቸነከረ፥ በአፉም መራራ ሐሞት ተጐነጨ፤ ግን መራራ የኃጢአት ምሳሌ ነውና ተፋው እናንተም ኃጢአ ትን በሕይወታችሁ ወዳችሁ ለምዳ ችሁ አትያዝዋት በንስሐ ከሕይወ ታችሁ አስወግዷት ትፏት ሲለን ነው። እንግዲህ የበደሉት የአዳምና የሔዋን እግሮች መቸንከር ሲገባቸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለእነርሱ (ስለእኛ) እርሱ ተቸነከረ ስለዚህም ከዲያብሎስ ባርነት ነፃ ወጥተናል።

በመስቀል ላይ ሳለ ከተናገራቸው ሰባቱ ቃላት (አጽርሐ መስቀል) አንዱ «ተጠማሁ» የሚል ነበር። በዚህም ሕይወትን፥ ጽድቅን፥ ለተጠማነው ለእኛ ለመካሥና በምትኩ የዘላለም የሕይወት ውኃን ሊሰጠን የመጣ መሆኑን ገለጸልን።

«አምላኬ አምላኬ ስለምን ተውኸኝ» በማለት በሲኦል ውስጥ ኾኖ «አምላኬ አምላኬ ምነው ተው ኸኝ» መዝ.21፥1 እያለ የመዳኑን ጊዜ ተስፋ ለሚያደርገው ለአዳም ተገ ብቶ (ተወክሎ) የእርሱን (የአዳምን) ጸሎት እንዳቀረበለት እንረዳለን።

«አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» ሉቃ.23፥34። በማለት በቅንአት መንፈስ ተነሣሥተው ለሰቀሉት አይሁድ እሱን በመስቀላቸው ዕዳ በደል እንዳይሆንባቸው ጸለየላቸው። በዚህም ለተከታዮቹ ለጠላቶቻችን ክፉ ለሚያደርጉብን መልካም መመለስ መልካምን መመኘት እንጂ መርገም እንደማይገባን አብነት ሆኖናል። ይህን ምሳሌነት በመጠቀም እስጢፋኖስ በድንጋይ ለሚወግሩት አይሁድ ጌታ ባስተማረው ትምህርት መሠረት «ጌታ ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» ብሏል። የሐዋ.7፥30። ጌታ አባት ሆይ ሲል እስጢፋኖስ ደግሞ የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ጠርቶ ይቅር በላቸው ማለቱ የጌታ አነጋገር ለትምህርት መሆኑን አረጋግጦልናል። ዳሩ ግን ይህን ያልተረዱ ሰዎች ጌታ ኃይል እንደሌለውና ከአብ የሚያንስ ኾኖ ወደ አብ ለመነ በማለት ከስህተት ማጥ ሲወድቁ ይታያሉ።

በመጨረሻም «ተፈጸመ» በማ ለት ቅድስት ነፍሱን ከቅድስት



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሥጋው በገዛ ሥልጣኑ ለይቷል። ዮሐ.10፥17። «ተፈጸመ» የሚለው አነጋገር በውስጡ የሰው ልጆች የደስታ ሰዓት መሆኑን የሚያመለክት ነው።

በብዙ ነቢያት ይነገር የነበረው የጌታ መወለድና በምድር ላይ መመላለስ በመጨረሻም ተሰቅሎ መሞት በአሁንዋ ሰዓት ተፈጸመ። እንዲሁም በማኅፀን የተወጠነው ካሣ በአሁንዋ ሰዓት ተፈጸመ። የዲያብሎስ አገዛዝ አበቃ፥ የአዳም የባርነት ሕይወት ተፈጸመ፥ ነፃነት ታወጀ የሚል ምሥጢር ያዘለ ነው።

እንግዲህ ኃያሉ አምላክ ኃይል እንደሌለው፥ ብርቱው ደካማ መስሎ በሥጋ የተመላለሰበት የትሕትና ዘመን አበቃ፥ ስለ አዳም ለመካሥ ሲል ለአዳም ተገብቶ ያቀረበው ምልጃ፡ ጾም፥ ጸሎት፥ ስግደት፥ መንገላታት (የትሕትና ሥራዎች) አበቁ፥ ከእንግዲህ ወዲህ ራሱን ዝቅ አድርጐ አይታይም በልዕልናው በመለኮታዊ ክብሩ ለመፍረድ ይመጣል እንጂ።

«ተፈጸመ» ጌታ በመዋዕለ ሥጋዌው ያደረጋቸው የትሕትና ሥራዎች ምልጃን ጨምሮ ለካሣ፥ ለቤዛዓለም ያደረገው በመሆኑ ከእንግዲህ ወዲህ ለጌታ እንደማይነገሩ የሚገልጽ ነው። ስለ አዳምና ስለ ልጆቹ ጸሎትና ምልጃ አቅርቦ ነበር ይባላል እንጂ አሁን በልዕልና እያለ ያማልዳል አይባልም።

ዳሩ ግን ሕያው አምላክ የፈጸመው የቤዛነት ሥራ (የማስታረቅ አገልግሎት) መሥዋዕት መሆኑ ነው አስታራቂ ያሰኘው። መቼም መች ቢሆን ዘመን አይሽረውም፥ አይለውጠውም። የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት ገደማ የፈጸመው የማስታረቅ አገልግሎት ዛሬም ለእኛ ይሠራል። ለወደፊትም እንደዚያው። ይህ የቤዛነት ሥራ ዛሬም ሕያው መሆኑን ጳውሎስ ሲገልጥ «ዘወትር በእሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡትን ሊያድናቸው ይቻለዋል። ለዘለዓለም ሕያው ነውና ያስታርቃቸዋል» ብሏል። ያስታርቃቸዋል ሲል በዕለተ ዓርብ የፈጸመው መሥዋዕትነት (የማስታረቅ አገልግሎት) ማለቱ ነው እንጂ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ሲጸልይ ሲያማልድ እንደነበረው አይደለም።

እንግዲህ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው መካከለኛው ኢየሱስ ክርስቶስ የሚለው ትርጉም ከላይ ባተትነው ሁኔታ ሲተረጐም እግዚአብሔር የሚለው ስም የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ የአንድነት መጠሪያ ስም ስለሆነ ለአብ ብቻ ሰጥቶ መናገር አግባብ አይደለም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተለየ አካሉ የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ መሥዋዕት በመሆኑ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን የጠብ ግድግዳ አፍርሶታል። በዚህ መሥዋዕትነቱም ከፅንስ ጀምሮ እስከ ስቅለት ድረስ በፈጸመው ካሣ ሰውን ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ እንዲሁም ከራሱ ጋር አስታርቋል። ይህን በዕለተ ዓርብ በጌታ የተፈጸመውን የማስታረቅ አገልግሎት ጳውሎስ ገለጠ እንጂ ዛሬም ኢየሱስ ክርስቶስ አማላጅ ነው አላለም። ምናልባት አንድ ሰው «በሰውና በእግዚአብሔር መካከል አንድ አለ» አለ እንጂ «ነበረ አላለም» ስለዚህም ዛሬም ቢሆን እንደ ቀድሞው ያማልዳል ሊል ይደፍር ይሆናል። ይህ ግን አያስኬድም የወደፊት ጊዜን በኃላፊ ግሥ ኃላፊን በወደፊት ግሥ መግለጽ የመጽሐፍ ቅዱስ አጻጻፍ ዘይቤ ነው።

ለምሳሌ ዘፍ.3፥22 «እግዚአብሔር አምላክም አለ፥ እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ»

ይህ አነጋገር ለወደፊት ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ የሰውን ሥጋ (የአዳምን) እንደሚዋሐድ የሚገልጽ ሲሆን ዳሩ ግን «ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ» በማለት አዳም በሳተበት ወቅት እንደሆነ አድርጐ ገልጾታል።

መዝ.21/22/፥12–20። ያለው ቃል ሁሉ ለወደፊት በጌታችን በመድ ኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የሚፈጸመውን ድርጊት የሚገልጽ ሲሆን ዳሩ ግን አነጋገሩ በዚያን ወቅት እንደተፈጸመ ሆኖ ነው የተጻፈው «እጆቼንና እግሮቼን ይቸነከሩኛል» ማለት ሲገባው ‹ቸነከሩኝ› ‹በቀሚሱም ላይ ዕጣ ይጣጣላሉ› ማለት ሲገባው «ተጣጣሉ» እያለ ነው የገለጸው።

ኢሳ.53፥1–2። ያለውን ብናይ «በእውነት ደዌያችንን ይቀበላል ማለት ሲገባው ተቀበለ (በኃላፊ ግሥ) እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ይቆስላል ማለት ሲገባው ቆሰለ (ኃላፊ ግሥ) ስለ ዓመፀኞችም ይማልዳል ማለት ሲገባው ማለደ ኃላፊ ግሥ

ስለዚህ የጌታ የማስታረቅ አገልግሎቱን በዕለተ ዓርብ ስለፈጸመ ዛሬ ያማልዳል አማላጅ ነው ማለት ከአብ አሳንሶ ማየት ስለሆነ የጌታን የባሕርይ አምላክነት የሚጻረር በመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ቤተክርስቲያናችን አጥብቃ ታወግዘዋለች።

በምድር ላይ በሥጋ ተገልጦ በነበረበትም ጊዜ መማለዱ ስለ አዳምና ስለ ልጆቹ ተወክሎ እንጂ በባሕርይው ደካማ ሆኖ ወይም አማላጅ ሆኖ አለመሆኑም ሊጤን ይገባዋል። «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘላለም ያው ነው (የባሕርይ አምላክ ነው) ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ» ዕብ.13፥8።

ይቀጥላል



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# «ወደ ምሥራቅ ተመልከቱ»

ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቪኖዳ የግብፅ ኦ.ተ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ

በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖታችን ቤተ ክርስቲያን የምትታነፀው በስተምሥራቅ ሲሆን ቤተልሔሙም ያለው በዚያው አቅጣጫ ነው። በጸሎት ሰዓትም ወደምሥራቅ ዞረን ነው የምንጸልየው። በሥርዓተ ቀብርም ሟች ሲቀበር ራሱ ወደ ምዕራብ እግሩ ወደምሥራቅ ሆኖ ፊቱን ወደምሥራቅ አቅንቶ ነው። በሌላም በኩል ደግሞ በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ ዲያቆኑ ወደምሥራቅ ተመልከቱ ይለናል ለምን ይሆን?

1. የአዳም የአባታችን ጥንተ ርስት፥ ገነት በምሥራቅ ናት። ዘፍ.2፥8።

ይህችም ርስታችን በአዳም በደል ምክንያት በኪሩቤል ሠይፍ ተዘግታ ስትኖር ሞትን ድል አድርጐ፥ በበደልን ክሦ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ከፈተልን ሉቃ.23፥43። ወደ ምሥራቅ በዞርን ቁጥር ወደገነት ለመግባት የተሰጠን ተስፋ ትዝ ይለናል። የተከፈተችው ቤታችን ወለል ብላ ትታየናለች፥ በክርስቶስ ያገኘነውን ጸጋ እናስባለን፥ ምድራውያን አለመሆናችንም ይታወሰናል።

2. ጌታ የተወለደው በምሥራቅ ነው። ሰብአ ሰገልም ኮከቡን ያዩት ከምሥራቅ ሲሆን ያ ኮከብም የምሕረተ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው። እነርሱን ወደጌታ እንዳደረሳቸው ሁሉ እኛንም ምሕረቱ ወደ ለመለመው መስክ ይመራናልና ማቴ.2፥2። መዝ.22፥14። ወደ ምሥራቅ በዞርን ቁጥር የጌታ መወለድና ያደረገልን ውለታ ይታወሰናል። የምሕረቱ ኮከብ እየመራን መሆኑ ትዝ ይለናል።

3. ምሥራቅ የእመቤታችን ምሳሌ ነው። ከምሥራቅ የፀሐይ መውጣት የጌታ ከእስዋ መወለድ ምሳሌ ነው። ሚልክያስ «ለእናንተ ስሜን ለምትፈሩ የጽድቅ ፀሐይ ትወጣላችኋለች» ሚል.4፥1። ሕዝቅኤልም በተዘጋች ቤት እናታችንን ያያት ከምሥራቅ ነው። ሕዝ.44፥1–4። በመሆኑም ወደ ምሥራቅ በዞርን ቁጥር እናታችን ትዝ ትለናለች፥ እነሆ ልጅሽ፤ እነኋት እናትህ «የተባልነውን የጌታ ቃል ትዝ እያለን ሰላም ላንቺ ይሁን እንላታለን። የጽድቅ ፀሐይ ስለወጣልንም በጨለማ አለመሆናችን ትዝ እያለን ከኃጢአት እንርቃለን።

4. የዓለም ድኅነት የተገኘው ከምሥራቅ ነው። ጌታ የተሰቀለውና ዓለምን ያዳነው በምሥራቅ ነው። ኢየሩሳሌም ምሥራቃዊት ከተማ ናትና። በመሆኑም ወደ ምሥራቅ ስንዞር የተሰቀለውን ጌታን እናስባለን። የገላትያ ሰዎች ከተወቀሱበት ዕዳም ነፃ እንሆናለን። ገላ.3፥1–3።

5. ክርስትናና ቤተ ክርስቲያን የተመሠረቱት በምሥራቅ ነው። የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በኢየሩሳሌም ሲሆን ወንጌል የተሰበከውም ከዚሁ በመነሣት ነው። ስለዚህ ወደ ምሥራቅ ስንዞር የቤተክርስቲያን ጉዞ፥ የወንጌል መስፋፋትና የሕዝበ ዓለም መዳን ትዝ እያለን ላልደረሳቸው እንዲዳረስ ቤተክርስቲያን በሌለባቸው ሥፍራዎች እንድትተከል እንጸልያለን።

6. የመጀመሪያው ሰማዕት የተገኘው ከምሥራቅ ነው። የመጀመሪያው ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ ስለወንጌል ተይዞ የተወገረውና እውነትን መስክሮ የተሠዋው ከዚሁ ነው። ወደ ምሥራቅ በዞርን ቁጥር በሰማዕታት ምልጃ ማረን እያልን እንጮኸለን፥ እኛንም ለነርሱ ክብር አብቃን እያልን እንለምናለን፥ ደም እስከ ማፍሰስ (እስከ ሞት) ድረስ ኃጢአትን እንድንቃወም አብቃን እያልንም እንጸልያለን። ዕብራ.12፥5።

7. ምሥራቅ የእግዚአብሔር ክብር መግለጫ ነው።

ኢሳ.29፥13። እግዚአብሔርን በምሥራቅ የእሥራኤልንም አምላክ የእግዚአብሔርን ስም በባሕር ደሴቶች አክብሩ።

ሕዝ.43፥2። የእሥራኤል አምላክ ክብር ከምሥራቅ መንገድ መጣ።

8. የጌታ ዳግም ምፅአት ከምሥራቅ ነው።

ዘካ.14፥14። በዚያን ቀን እግሮቹ በኢየሩሳሌም ትይዩ በምሥራቅ በኩል ይቆማሉ።

ሐዋ.1፥11። ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲያርግ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል።

ማቴ.24፥27። መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናል።

9. መንፈሳዊ ሕይወትን ያሳስበናል።

ሕዝ.47፥1–9። የሕይወት ወንዝ ያለው በምሥራቅ ነው፥ ይኸም የክርስቶስ ምሳሌ ነው ዮሐ.7፥38። ወደ ምሥራቅ በዞርን ቁጥር በልውል እግዚአብሔር የሕይወት ውኃ (ቃለ እግዚአብሔር) ዘወትር መመገባችንን እናስባለን። እንዳንጠማም ሁልጊዜ መጠጣት እንደሚያስፈልገን እናስታውሳለን።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

2ነገ.13፥17። ኤልሳዕም እጁን በንጉሡ ላይ ጭኖ የምሥራቁን መስኮት ክፈት አለ፥ ከፈተውም፥ ኤልሳዕም ወርውረው አለ። ወረወረውም፤ እርሱም የእግዚአብሔር መድኃኒት ፍላጻ ነው አለው ይላል። መስኮቱ የእመቤታችን ምሳሌ ሲሆን ከርስዋ የተገኘው ፍላጻ ጌታችን ዲያብሎስን ወግቶ እኛን ነፃ አድርጐናልና። ወደ ምሥራቅ ስንዞር ጠላታችን ዲያብሎስ ድል መሆኑ ዛሬም በዚያ ፍላጻ እንደምናሸንፈው እናሳስባለን።

10.የቅዱሳን አበው ሥርዓት ነው።

ዳን.6፥9–12። ወደ ኢየሩሳሌም ያለውን መስኮት ከፍቶ ይጸልይ ነበር። ነቢዩ ዳንኤል እግዚአብሔር ምሉዕ በኩለሄ (የትም ቦታ ያለ) መሆኑን ያውቃል። ነገር ግን ወደ ኢየሩሳሌም መዞሩ ነፍሱ የምታስበው እንዲኖራት ነው።

11. ታቦቱን በምሥራቅ በኩል ባለው መቅደስ አስቀምጠን ሥጋ ወደሙ የምንፈትተው ጌታ በምሥራቅ ሃገር ለኛ መስቀሉን ሥጋውን መቁረሱን ደሙን ማፍሰሱን በማሰብ ነው።

12 በጥምቀት ጊዜ ተጠማቂው ወደ ምዕራብ ዞሮ ቆይቶ ከተጠመቀ በኋላ ወደ ምሥራቅ የሚዞረው ከጨለማ (ሞት) ወደ ብርሃን (ሕይወት) በጥምቀት መምጣቱን ለመግለጽ ነው።

13. በቀብር ሥርዓታችን የሚቱን ፊት ወደ ምሥራቅ የምናዞረው በዳግም ምፅዓት በሚነሣ ጊዜ ፊቱን ወደጌታው እንዲያዞር በማሰብ ነው።

እንግዲህ ወደምሥራቅ መዞር የክርስቶስን የማዳን ሥራ የቅዱሳንን ሕይወት የሰማዕታትን ገድል፥ የክርስቲያንን ተስፋ የሚያሳስበን ነውና ይኸን ሥርዓት ያስተማሩን አበው በረከት አይለየን። ✣

አሜን።

# ከሰሞኑ በረከት

## ዐቢይ ጾም

በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ይህ የያዝነው ጾም ከሰባቱ አጽዋማት አንዱ ሲሆን፥

1. ዐቢይ ጾም ይባላል። ሌሎች አጽዋማት ከቅዱሳን አበው የወረስናቸው የኑሮአቸው ፍሬዎች ዕብ.13፥7። ሲሆኑ ይኼኛው ግን በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተመሠረተ በመሆኑ ዐቢይ (ታላቅ) ይባላል።

2. ጾመ ሁዳዴ ይባላል። በጥንት ጊዜ ገባሮች ለባለርስቱ የሚያርሱት መሬት «ሁዳድ» ተብሎ ይጠራ ነበር። ይኸውም ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ የጾመው፥ እርሱን እያሰብን የምንጾመው በመሆኑ ጾመ ሁዳዴ እንለዋለን።

3. የካሣ ጾም ይባላል። አባታችን አዳምና እናታችን ሔዋን ከገነት የተባረሩት ለውርደት ሞት፥ ለሲኦል ባርነት የበቁት በመብል ምክንያት ነበር። በሆዳምነቱ የወደቀውን የሰው ልጅ በፈቃዱ በጾመው ጾም ካሠው፥ እንዲሁም አዳም ከገነት ሲባረር ረሃበ ጸጋ (መንፈሳዊ ረሃብ) ደርሶበት ነበርና ረሃቡን በረሃብ ካሠለት የኛን ረሃብ እርሱ ተራበ።

4. የድል ጾም ይባላል። ጌታችን ተጠምቆ ዕለቱን ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ በመሔድ ከሰው ተለይቶ አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት በመጾም አዳምና ሔዋንን በመብል የረታቸውን ዲያብሎስ እርሱ ድል አደረገላቸው። ዲያብሎስን ድል ያደርግ ዘንድ ከዚህ ዓለም ርቆ ወደ ገዳም መሄዱ አዳም ከዚህ ዓለም ርቃ በምትገኘው ገነት ድል ሆኖ ነበርና እርሱም ዲያቢሎስን በገዳም፥ ከዚህ ዓለም ርቆ ድል አደረገልን ለእኛም ፈቃደ ሥጋችንን የምናሸንፍበት ኃይል ሰጠን። ይህ ጾም የዲያቢሎስ ጠላት ነው የተሸነፈበት ነውና።

5. የመሸጋገሪያ ጾም ይባላል። ሊቀ ነቢያት ሙሴ ሕዝቡን ከሕገ ልቡና ወደ ሕገ ኦሪት ሲያሸጋግር አርባ መዓልትና ሌሊት በደብረ ሲና እንደ ጾመው ሁሉ ጌታችንም እኛን ከሕገ ኦሪት ወደ ሕገ ወንጌል ሲያሸጋግረን አርባ መዓልትና ሌሊት ጾመ። ስለዚህም የመሸጋገሪያ ጾም እንለዋለን።

6. ጾመ አስተምህሮ ይባላል። ሁሉን ነገር በቅጽበትና ያለ ድካም ማድረግ የሚችለው አምላክ እኛን ልጆቹን ያስተምረን ዘንድ ራሱን ዝቅ አደረገ። መልካም መምህር ተማሪዎቹ ይገባቸው ዘንድ ዝቅ ብሎ በነርሱ ቋንቋ እየተናገረ በሚችሉት እየመሰለ እንዲያስረዳ ጌታችንም እኛን ወደርሱ ይወስድ ዘንድ አስቀድሞ እርሱ ወደ እኛ መጣ። ረሃባችንን ተራበ፥ ድካማችንን ደከመ፥ ፈተናችንን ተፈተነ ለእኛም አርአያ ሆኖ ትህትናን፥ ትዕግሥትንና ፈተናን በጾም ማሸነፍን አስተማረን።

7. የቀድሶተ ገዳም ጾም ይባላል። እነ መጥምቁ ዮሐንስ እነ ነቢዩ ኤልያስ የኖሩትን የብሕትውና ኑሮ ጌታ ባርኮ ሰጠን። ከከተማ ወጥቶ ከሰው ርቆ በበረሃ ከአራዊት ጋር እየኖረ በዲያብሎስ ተፈትኖ ድል አደረገ። ዛሬም ልጆቹ በየገዳማቱ ድምፀ አራዊትን ግርማ ሌሊትን ታግሠው ዓለምን ንቀው፥ ከሰው ርቀው በጾም በጸሎት ከአጋንንት ጋር ይታገላሉ፥ ድልም ያደርጋሉ።

8. የመዘጋጃ ጾም ይባላል። ለእሥራኤላውያን ስለ በዓለ ፋሲካ አከባበር ሲነገራቸው የፋሲካውን በግ ሥጋ ከመራራ ቅጠል ጋር እንዲበሉት ታዘው ነበር። ዘጸ.12፥8። ይኼም መራራ ቅጠል በግብፅ ይኖሩት የነበረውን የመከራ ኑሮ የሚያሳስባቸውና ደግም ወደ ግብፅ (ምድረ ፋይድ) እንዳይመለሱ ከኃጢአት ይርቁ ዘንድ የሚያስተምራቸው ነበር። የፋሲካው በግ ደግሞ እግዚአብሔር በፍቅሩ የሰጣቸውን ነፃነት ያሳስባቸዋል።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ዛሬም በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ከበዓለ ትንሣኤው በፊት የጾምን ወራት ያስቀደምነው ለዚህ ነው። ከመብል ስንከለከል ለአዳምና ሔዋን የተሰጠውን ሕግ እናስባለን፥ ረሃብ ሲሰማን በሰው ልጅ ላይ ደርሶ የነበረው የጸጋ ረሃብ፥ የመንፈስ ረሃብ ይታወሰናል፥ ስንደክም ስንጐሰቁል በአዳምና ሔዋን የደረሰው የመንፈስ ጉስቁልና፥ የበደልን የዕዳ ቀንበር ተሸክመው የደረሰባቸው ድካም ይታሰበናል። እኛም በነርሱ የደረሰችው ሞት በእኛ እንዳትደርስ ደግሞ ወደ ኃጢአት እንዳንመለስ ይመክረናል ያሳስበናል።

በጾሙም መጨረሻ የሐዲስ ኪዳንን በግ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋና ደም እንቀበላለን። ያን ጊዜም ሞትን ካሸነፈው አምላክ ጋር አንድ እንሆናለን። ዮሐ.6፥55–58። ሞታችን በሞቱ እንዳለፈ እናስባለን። 1ቆሮ.11፥26። በመሆኑም ይህ ወቅት በዓለ ትንሣኤ–የሐዲስ ኪዳን ፋሲካን ለማክበር፥ ሥጋ ወደሙን ለመቀበል ራሳችንን የምናዘጋጅበት የምንፈትንበት ነው። 1ቆሮ.11፥27።

<u>9. የሥራ መጀመሪያ ጾም ነው።</u> ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የማስተማር ሥራውን ከመጀመሩ፥ የመንግሥተ ሰማያትን አንቀጽ ከማስተማሩ በፊት ከገዳመ ቆሮንቶስ አርባ መዓልትና ሌሊት ጾመ። ይህም ለእኛ የማንኛውም ነገር መጀመሪያው ጾም መሆኑን ሲያስተምረን ነው። ለዚህም ነው ሐዋርያት ጾምን የሥራቸው መጀመሪያ ያደረጉት።

<u>እንዲሁም ይህ የጾም ወቅት።</u>

የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡ ተኩላዎች እንድንጠነቀቅ ያስተምረናል።

ጠላት ዲያብሎስ ጌታችንን ሲፈትን ከመጽሐፍ ቅዱስ እየጠቀሰ ነበር። መዝ.20፥11። የእግዚአብሔርን ስም የጠራ ጥቅስ የጠቀሰ ሁሉ መንፈሳዊ ሰው፥ እውነተኛ ክርስቲያን ሊባል አይችልም። መጥቀስማ ዲያብሎስም ይጠቅሳል። ሕይወቱን አይኖረውም እንጂ።

እንዲሁም በዚህ የጾም ሰሞን ጠላታችን ዲያብሎስ ያዘጋጀልንን ወጥመድ አስበን ለገድል የምንዘጋጅበትም ነው። ጌታን ወደ መቅደስ ጫፍ አውጥቶ ወደ ታች ተወርወር እንዳለው ሁሉ እኛንም በትዕቢትና በከንቱ ውዳሴ ወደ ላይ አውጥቶ በኃጢአትና በውርደት በሃፍረትና ከመንፈስ በማራቆት ሊወረውረን ይሻል።

ስለዚህ ትህትናን በምታለብስ ጾም ድል እንንሣው።

እንግዲህ ዐቢይ ጾም ማለት፥

- ጌታ ስለኛ ባየው መከራ የምናዝንበት
- በሰጠን ኃይል ከሰይጣንና ከፈቃደ ሥጋ ጋር የምንዋጋበት
- በበደልነው ተገብቶ የካሠልንን እያስብን ዳግም ወደኃጢአት ላንመለስ ቃል የምንገባበት፥
- አርአያ ሆኖ ከሠራልን ሥርዓት ከኖረልን ሕይወት የምንማርበት:
- ራሳችንን ለፋሲካው በግ ለሥጋወደሙ የምናዘጋጅበት፥ ሰሞን ነው።

በመሆኑም በሰላም በፍቅር በትህትና ጾመን ለበዓለ ትንሣኤው በሰላም እንድንደርስ እግዚአብሔር በቸርነቱ ይጠብቀን አሜን። ✣

# እመ አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ

ዲ.ተክለጻድቅ – ዘጸ.3፥1–12።

ሰዚህ የመጽሐፍ ክፍል የአማቹን በጐች ሲጠብቅ የነበረውን ዕብራዊ ሰውና እግዚአብሔር በኮሬብ ያደረገለትን ድንቅ ነገር እንመለከታለን። ይህ የበጐች እረኛ በኋላ የእሥራኤል መሪ የሆነው ነቢየ እግዚአብሔር ሙሴ ነው። በኮሬብ ተራራ ግርጌ በጐቹን እየጠበቀ ሳለ እግዚአብሔር በቁጥቋጦ መካከል በእሳት አምሳል ተገለጠለት። በዚህ ጊዜ በሚነደው የእሳት ነበልባል ውስጥ ያልተቃጠለች አንዲት ለምለም ዕፅ ነበረች። የሚነደውና ለሙሴ የተገለጠው ነበልባል እሳት በአካባቢው የነበሩትን ዕፅዋት ሁሉ ሲያቃጥል ያችን ለምለም ዕፅ ግን አላቃጠላትም ነበር።

ይህን ለነቢዩ ሙሴ በኮሬብ የተገለጠውን ድንቅ ነገር የቤተክርስቲያናችን አባቶች አምልተውና አስፍተው በምሥጢር ተርጉመው አስቀምጠውልናል። ነቢዩ ሙሴ ያየው ያ የሚነድደው እሳት የእግዚአብሔር የባሕርየ መለኮቱ ምሳሌ ነው፥ እግዚአብሔር በባሕርዩ ማንም ሊያየው ማንም ሊቀርበው የማይችል እሳታዊ ነውና በዚህ ምክንያት ነበልባሉን እሳት በእግዚአብሔር ባሕርየ መለኮት መስለውታል። በሚነድደው እሳት መካከል ሳትቃጠል የተገኘችው ዕፅ ደግሞ የድንግል ማርያም ምሳሌ ናት ምክንያቱም ድንግል እመቤታችን በባሕርዩ እሳታዊ የሆነውን እግዚአብሔር ወልድን በማኅፀኗ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀናት ተሸክማዋለችና ነው።

የሚነድደው የእሳት ነበልባል በአካባቢው የነበሩትን ሌሎች ዕፅዋት በጠቅላላ ሲያቃጥል ያችን ሐመልማል አለማቃጠሉ ከሴቶች ወገን ማንም ለዚህ ምሥጢር ያልበቃና የማይኖርም መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን አንዷቱን ብቻ አለማቃጠሉ ደግሞ ከድንግል ማርያም በስተቀር ሌላ ማንም መለኮትን በማኅፀን ለመሸከም የተመረጠ አለመኖሩን የሚያመለክት ምሳሌ ነው። (የውዳሴ ማርያም ትርጓሜ)

ቅድስት ድንግል ማርያም የመለኮትን ባሕርይ በማኅፀኗ ለመሸከም ብቻ ሳይሆን አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ለመውለድ በመብቃቷ ለዚህ ታላቅ ክብር የተመረጠች ስትሆን ክብርት ሆናም በመገኘቷ እመ አምላክ ወላዲተ አምላክ ትባላለች። ይህ የተለየ ታላቅ ምሥጢርም በእርሷ በመፈጸሙ ከሴቶች ሁሉ የተለየች የተባረከች የተመረጠች ቅድስተ ቅዱሳን ትባላለች አማናዊቱ የእግዚአብሔር ማደሪያ ሆናለችና።

በቤተ እግዚአብሔር እንደሕጉና በቤተ መቅደሱ ያደገችው ቅድስት ድንግል ማርያም እግዚአብሔርን ለተዋሕዶ ምሥጢር በማኅፀኗ ለመሸከም በቃች። ከእርሷ ሥጋን ነሥቶ የተዋሐደው አምላካችን እኛን አዳነን። ስለዚህ እርሷ ምክንያተ ድኂን ለመሆን በቃች። ዛሬም ሰዎች የድንግል ማርያምን ሕይወት አብነት ማድረግና በእግዚአብሔር ቤት በሕጉና በትእዛዛቱ እየኖርን ለቅድስናና ለመልካም ነገር ለመመረጥ መዘጋጀት ያስፈልገናል። ዛሬም የእግዚአብሔር ቃል የሚያድርበትና የሚሸከመው ሰውነት ይፈልጋል። በድንግል ማርያም እንደነበረው ለተዋሕዶ አይደለም ነገር ግን ሰው ለዘለዓለም ሕያው ሆኖ ይኖር ዘንድ ነው። በሕግጋተ እግዚአብሔር በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ተወስኖ ሕይወቱን በመምህረ ንስሐ እያስመረመረ ከኃጢአት ርቆ መኖር የእግዚአብሔር ቃል ማደሪያ መሆን ነው። ስለዚህም የእግዚአብሔር ቃል በእኛ ቢሠራ ሕይወታችን ለቅድስና ቢዘጋጅ ሥጋውና ደሙን ብንቀበል የምንኖረው ንጹሕና ክርስቲያናዊ ኑሮ ሰዎችን ከኃጢአት ለማዳን አብነት ይሆናል የደኅንነት ምክንያት ሆንን ማለት ነው። የእግዚአብሔር የቃሉ ማደሪያዎች የሃይማኖትና የምግባር ሰዎች ሆነን ፍሬ አፍርተን ለመገኘት እንድንችል እግዚአብሔር በቸርነቱ ድንግል ማርያም በአማላጅነቷ አይለዩን አሜን። ✣



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ኪነጥበብ

## ቬነስያ

ከዳንኤል ክብረት

ክፍል ሁለት

ልዑል ማልኮስ እንደ አንበሳ በሚንጐማለል ትከሻው ላይ በወርቅ የተለበጠ ካባውን ደርቦ በኩራት ወደ ልዕልቷ ቤት ገባ። እመቤት ጠርሲዳ ሁለት እጆቻቸውን ወደኋላ አመሳቅለው በሩ ላይ የሚያስተውሉት አንዳች ነገር ያላቸው ይመስላል። ቅዝዝ ብለው ዓይኖቻቸው እንዳፈጠጡ ለተመለከታቸው ሌላው ያልተረዳው እርሳቸው ብቻ የሚዋኙበት የምሥጢር ዓለም ያላቸው ያስመስላቸዋል።

ልዑል ማልኮስ እየተንጐራደደ መጣና «እንደምን ዋሉ እመቤት ጠርሲዳ» ብሏቸው ወደ እልፍኙ ገባ።

ልዕልት ቬነስያ ዓይኖቿ ደፍርሰዋል። ጉንጮቿ ከወረደባቸው የዕንባ ጐርፍ የተነሣ የወንዝ መውረጃ ሸለቆዎች ይመስላሉ። ያ እንደ አጥቢያ ኮከብ ያበራ የነበረው ውበቷ በደመና ውስጥ የጠለቀች ጨረቃ ይመስል የሐዘን ደመና አጥልቶበታል። አንገቷን ከቀበረችበት አልጋዋ ቀና ስትል እና ልዑል ማልኮስ ሲገባ አንድ ሆነ።

«የሮማ ቆነጃጅትእ ኮ ሲዳሩ ማልቀስ ልማዳቸው ነው» ብሎ ፈገግ አለ። ከዚያም ወደ እመቤት ጠርሲዳ ዘወር ብሎ

«ይህች ጽጌረዳ ከሮም ይልቅ ቬነስ ላይ ብትተከል የበለጠ ትፈካለች» አላቸው። እመቤት ጠርሲዳ ግን በራሳቸው ዓለም እየዋኙ ስለነበር ልዑሉ የተናገረው ነገር ከድምፁ በቀር ቃላቱ አልተሰሙዋቸውምና ዓይኖቻቸውን ወደእርሱ መልሰው ቦዘዝ አድርገው አዩት።

«ምነው ሁላችሁም የከፋችሁ ትመስላላችሁሳ» አለ ልዑል ማልኮስ ዓይኑን ከእመቤት ጠርሲዳ ሳይነቅል።

«ምናልባት የሮማ ትዝታ ይሆናላ ጌታው» አሉት እመቤት ጠርሲዳ

«መልካም የቬነስ ቆነጃጅት ዛሬ ይገባሉ። ልዕልትን ሊያስጌጡዋት ተዘጋጅተዋል። ከነገ ወዲያ ሠርጓ ላይ እውነተኛዋን የፍቅር አምላክ ቬነስን መምሰል አለባት። መልካም ሌሊት ቪነስያዬ»

የመጨረሻዋ ቃል ለቬነስያ ጆሮ ከፍቅር ቃናው ይልቅ የሚሰቀጥጥ ሆነባት። የቬነስ ልዑል ሚስት ሆና በውቧ ከተማ የምትኖረውን ኑሮ አሰበችው። እንደገና ወደ ጣዖት አምልኮ፥ እንደገና ስለራስ ውበት ብቻ ወደ መጨነቅ፥ ስለ ታላላቅ ዘፈኖች፥ ስለ ጌጣጌጥና ሽርሽር ከማሰብ በቀር ሌላ ኑሮ አይጠብቃትም። ልዑል ማልኮስ እንደሆነ የመክስምያኖስ ወራሽ ለመሆን እንጂ በርስዋ ረግቶ በትዳሩ ጸንቶ አይቀመጥም፤ ከምዕራብ እስከ ምሥራቅ የማያካልለው የማያንኳኳው የሴቶች ጓዳ የለም። አንጀቷ እያረረ፥ የነገሥታትና የልዑላን ሚስቶች እንደሚታሙት በድብቅ ገላዋን ለዝሙት አጋልጣ መኖር ነው የሚጠብቃት።

ከፊቷ ያለው ጐዳና ከክርስትናዋ ጋር ሆድና ጀርባ የሆነ የፈተና የመከራ መንገድ ነው። ፀሐይዋ እየጠለቀች ስትሄድና ደም የመሰለ ብርሃንዋ በሮማ ተራሮች ጫፍ ተፈንጥቆ በልዕልት ዕልፍኝ ውስጥ ሲገባ ቤቱን የመከራ ቤት አስመሰለው።

«እመቤት ጠርሲዳ!» ልዕልት ቬነስያ ዕንባዋን በመሐረብ ጠርጋ ከአልጋዋ ተነሣች።

«አቤት የኔ ልጅ» ይህን ዓይነቱ የቁልምጫ ንግግር ከልዕልት ክርስቲያን መሆን በኋላ የመጣ የፍቅር ድምፅ ነበር።

«እግዚአብሔር ልጆቹ በእሳት ሲጣሉ ዝም ብሎ ያያል?» እጆቿን ደረቷ ላይ ለጥፋቸው ነበር።

«ልዕልት እሳት ውስጥ ሲጣሉ ዝም ቢልም እንዲቃጠሉ ግን አይፈቅድም» አሁንም ግድግዳውን እንደተደገፉ ነበረ።

«ታዲያ ቬነስ ሄጄ ልኖር ነው ማለት ነው? እንደገና ወደ ኃጢአት ልመለስ? ምን ልሁን እመቤት ጠርሲዳ? ምን ልሆንው?»

ዓይኖቿ ዳግም ዕንባ አቀረሩ። እመቤት ጠርሲዳም በሐዘንና በሃሳብ የደከሙ፥ ሌት ተቀን ዕንቅልፍ በማጣት የታከቱ ዓይኖቻቸውን ቀስ አድርገው ከድን አደረጉዋቸውና መልሰው ከፈቱዋቸው። ቦዘዝ ብለውም ልዕልትን ተመለከቱዋት፥ ሰውነቷ ከስቶ ታያቸው፥ አቅመ ቢስ መሆናቸው ቢሰማቸውም ልዕልትን ከዚህ ማጥ ማውጣት ያለባቸው እርሳቸው መሆናቸውን ያምናሉ።

«እግዚአብሔር የታመነ ነው» አሉ እመቤት ጠርሲዳ። ከንፈሮቻቸውን በዝግታ እያንቀሳቀሱ። ለራሳቸው ነበር የሚያወሩት «ለዚህች የዋሕና አንዲት ፍሬ ልጅ ክርስትናውን ያበሰርኩላት እኔው ነበርኩ። ዛሬም ለፈተናዋ መውጫ የመፈለግ ኃላፊነት አለብኝ። ልዕልት መከሊቴ ናት። ተመልሳ ወደ ኃጢአት ኑሮ ገባች ማለት መከሊቴን ቀበርኩ ማለት ነው። እግዚአብሔርን አምኜ ያንኑ ያሰብኩትን መፈጸም አለብኝ። ሰው መዳኑን ያሰባል እግዚአብሔር ደግሞ መውጫውን ያዘጋጃል»።

ረጋ ብለው ወደ ቬነስያ ተጠጉ።

«የኔ ልጅ» ድምፃቸው ከሩቅ የሚመጣ ይመስል ነበር «ቆራጥ ነሽ?»



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

«ምነው እመቤት ጠርሲዳ»

«ለሰማዕትነት የሚያበቃው ማመን ብቻ አይደለም ልጄ መቁረጥም ጭምር ነው»

«እንዴት እመቤት ጠርሲዳ»

«ከዚህ ቤት ካልጠፋሽ በስተቀር የፈራነው አይቀርም»

«በምን ዕድሌ ያማ ቢሆን እግዚአብሔር እንደሚወደኝ ባረጋገጥኩ ነበር»

«ይወድሻል ልዕልት፤ እግዚአብሔር የሚወዳቸው ልጆቹ ሲያሸንፉ ማየት ይወዳል። ስለዚህ ለውድድር ያቀርባቸዋል»

እመቤት ጠርሲዳና ልዕልት ቬነስያ ምሽቱን በሙሉ ቁጭ ብለው ሲያወሩ ቆዩ ከዚያም በራቸውን ዘግተው ሥዕለ ማርያምን ከቆለፉበት አወጡና ጸሎት አደረሱ። እመቤት ጠርሲዳ የልዕልት ቬነስያን ፀጉር እየዳሰሱ ሲያጽናኑዋት ችግርዋ ሁሉ የተቃለለላት፥ ወጥመድዋ ሁሉ የተበጠሰላት መስሎ ተሰማት።

«መጨረሻ የሚሮጥ ክርስቲያን መጀመርያ ከሚሮጥ ዓለማዊ ይበልጣል የማሸነፍ ዕድሉ በአምላኩ የተረጋገጠ ነውና» የእመቤት ጠርሲዳ ቃል ነበር።

እናም እግዚአብሔር እንደማይተዋት አመነች። አልጋዋ ጫፍ ላይ ቁጭ ብላ ፀጉርዋን ከሚያሻሹላት ከእመቤት ጠርሲዳ ጋር «እግዚአብሔር እረኛዬ ነው» የሚለውን የዳዊት መዝሙር መዘመር ጀመሩ።

በትርና ምርኩዝህ እርሱ ያጽናናኛል፥
በሕይወቴ ዘመን ተከትለሽኛል።
ለፊቴ ገበታ አንተ ሰጥተሽኛል፥
በጠላቶቼ ፊት ግርማ አልብሰሽኛል፥
ምሕረት ቸርነትህ በሕይወት ዘመኔ ተስፋ ይሰጠኛል።
እግዚአብሔር ለኔ እረኛዬ ነው፥
የሚያሳጣኝ የለም ከምለምነው፥
በለመለመ መስክ ማደሪያ አዘጋጅቶ፥
ወደ ዕረፍት ውሃ ይወስደኛል መርቶ፥
በድቅድቅ ጨለማ ብሄድ በሞት ጥላ፥
አልፈራም ጨርሶ ከሆንከኝ ከለላ።

የሠርግ ዋዜማ!

ሸብ ረብ ቀልጧል። ዛሬ እንደ ወትሮዋ አይደለችም ቬነስያ ደስተኛ ሆናለች። አባቷ መክስምያኖስ እንኳን፥ «የሮማ ጽጌረዳ ዛሬ ፈነዳች ነገ ደግሞ ቬነስ ገብታ ታውዳለች» ሲል ተርቷል። ልዑል ማልኩስም አሥር ጊዜ ወጣ ገባ እያለ የቬነስያን ትከሻ ቸብ ያደርግና ዙርያዋን ከበው ለሚያስጌጧት የቬነስ ቆነጃጅት የውበቷን ዝና እንደ ዕውቅ ባለቅኔ ይደረድርላታል። እመቤት ጠርሲዳም ቢሆኑ እንደ ሠርገኞቹ አይፈንድቁ እንጂ ተፍ ተፍ ማለቱን የጀመሩት ገና በማለዳ ነው።

ይኼ ሁሉ ግርግር የመክስምያኖስን ግቢ እንዳጣበበው ጨለማው ገፍቶ መጥቶ ግቢውን ወረረው። የሚንቀለቀሉት የወይራ ዘይት መብራቶች ግቢውን ባለ ግርማ ሞገስ ቢያደርጉትም የአብዛኞቹ ልብ ግን ከድካም የተነሣ የዕንቅልፍ ሰዓትን በናፍቆት ይጠባበቅ ነበር። እመቤት ጠርሲዳ የጓሮውን አጥር ሁለት ሦስት ጊዜ ደጋግመው ተመለከቱት። የተንጠለጠለው መሰላል መሰል ገመድ አጥሩን ዘሎ መሬት ላይ ተነጥፎአል። በአካባቢው ሰው ቀርቶ ወፍ ዝር አይልም። በልዕልት ሠርግ ምክንያት የሮማ ሕዝብ ውሎው ሁሉ ቤተመንግሥት ዙርያ ሆኖአል። የልዕልት እልፍኝ ደግሞ ከቤተ መንግሥቱ ፈንጠር ብሎ አጥሩን ተጠግቶ የተገመረ ነው።

ቀኑን ሙሉ ሲደክም የዋለው ሠራተኛ በያገኘበት ቦታ ላይ ፈንግል እንደያዘው ዶሮ ዕንቅልፍ ያዳፋው ጀመር። ከዘበኞች ጀምሮ ንጉሥ መክስምያኖስ ሳይቀር በዕንቅልፍ ባሕር ተዋጡና የግቢ መብራቶችም ዘይት የሚጨምርባቸው ሲያጡ አንድ በአንድ እየጠፉ ሄዱና ግቢውን ፀጥ ረጭ ያለ ጨለማ ከበበው። እመቤት ጠርሲዳ ወጣ ብለው ግቢውን በደንብ ቃኙት። ዝም ጭጭ ብሏል። አልፎ አልፎ ብቻ የሚያንኮራፉ ሰዎች ይሰማሉ። ጨረቃዋ ደግሞ ዛሬ የለችም። ደመናው ያኮረፈ ይመስላል። ቂም ያረገዘ።

«ልዕልት» አሉ እመቤት ጠርሲዳ። ቀና ብላ አየቻቸው

«በቃ ካሁን በኋላ የሰማዕታት ኑሮ ሊጀመር ነው»

«ደስ ይለኛል» አለቻቸው ፈገግ ብላ።

«ቆርጠሻል»

«እግዚአብሔር ካጸናኝ» ዓይኖቿ የደስታ ስሜት ይታይባቸው ነበር።

«ተዘጋጂ»

እመቤት ጠርሲዳ ለመጨረሻ ጊዜ ግቢውን ለመታዘብ ወጡ፥ ያው ነው። ጨለማው ከመንገሡ ፀጥታው ከማየሉ በቀር ሌላ ለውጥ የለም። ቀስ ብለው ወደ ጓሮ ዞሩ። ሁሉም በቦታው አለ።

ሾከክ ብለው ወደ ዕልፍኙ ተመለሱ፥

«ተነሽ ልዕልት እግዚአብሔር ይርዳን»

ልባቸው ድል ድጭ አለ። ሥዕለ ማርያምን ከተሰቀለበት አውርደው ደረታቸው ላይ አስጠጉት። ያላወቁት ነገር ወረራቸው። ኃይልና ጽናት ሲሰማቸው ታውቋቸዋል።

«ጉዞ ወደ ሰማዕትነት»

እመቤት ጠርሲዳ ቀደሙ ልዕልት ተከተለቻቸው...

«የአብርሃምን ጉዞ የባረክህ አምላክ ተከተለን» ልዕልት በልብዋ ጸለየች። ግራ ቀኙን ተመለከቱ። ከዚያ ፈጠን ጠፈን ብለው ወደ ጓሮው ተጓዙ። ምንም ነገር የለም እመቤት ጠርሲዳ ጀርባዋን ነካ አደረጉት ልዕልት ፈገግ አለች።

ቀደሙና በአጥሩ ተንጠላጥለው በገመዱ ወረዱ። ልዕልት ዕቃዋን ወረወረችላቸው። ቀጥላ ልዕልት አጥሩን መውጣት ስትጀምር፥

«ማነው» የሚል ጐርናና ድምጽ ከኋላዋ ተሰማት – «ማነው»

ልዕልት ዘወር አለች። ✣

ይቀጥላል።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ማዳኑን ያዩ ይናገሩ

ካለፈው የቀጠለ

ከባስልዮስ ዘቄሣርያ

ጉዞ ወደ አይዝራኤል ሜዳ። ኤልዛቤል ናቡቴን ያስገደለችበት እርሷም በኢዩ እጅ ብድርዋን የተቀበለችበት ቦታ (ነገ.20፥10)

በአይዛራኤል ሜዳ ዳርቻ ኤይን ጌኒን ወይም በአረቦች አጠራር ጀኒን የተባለችውን ከተማ እናገኛለን (ኢያ.2፥29) አካባቢው የይሳኮር ርስት ነው። ወደ ከተማ ገብቼ ጌታ የፈወሳቸው አሥር ለምጻሞችን ስጠይቅ ዘጠኙ መጥፋታቸውንና አንዱ ግን በሉቃስ መንደር ቀበሌ 17 የቤት ቁጥር 17 እንደሚገኝ ነገሩኝ። እኔም ሠረገላዬን እየነዳሁ ወደዚያው አመራሁ። ያንን ቅን ሳምራዊ ከጓደኞቹ ጋር ከአንድ መደብር ፊት ለፊት ሲያወራ አገኘሁትና እንደምፈልገው ነገርኩት። የመጣሁበትን ዓላማ ከተረዳ በኋላ ወደ መደብሩ ውስጥ ገባን።

ተርቢኖስ – ያኔ ይዞህ የነበረው በሽታ ምን ነበር? ለአንባብያን ብትገልጽልኝ?

ሳምራዊው – የለምጽ በሽታ መላ ሰውነቴን ወሮት ነበር። በዚህ በእኛ ሀገር ደግሞ ለምጻምን ሰው የሚቀርበው የለም። ለይተው በአንድ መንደር ያስቀምጡን ነበር። ከሁሉም ነገር የተገለለ ነው። እናም አሥራችንም በዚህ ምክንያት ከሕዝብ ተለይተን እንኖር ነበር።

ተርቢኖስ – ወደ ጌታ ቀርባችሁ ከተፈወሳችሁ በኋላ ዘጠኙ የት ገቡ?

ሳምራዊው – ጌታ ራሳችሁን ለካህን አሳዩ አለን። ከዚያም አብረን ወደ ምኩራብ ሄድንና ራሳችንን ለካህን አሳየን ካህኑም እጃቸውን ጭነው ሲጸልዩልን ወዲያው ከለምጻችን ተፈወስን በዚህ ጊዜ ግማሾቹ ወደ ዘመዶቻቸው ሌሎች ለሕዝብ ሉታዩ ወጡ። እኔ ግን ያዳነኝን ጌታ ማመስገን አለብኝ ብየ ተመለስኩ።

ተርቢኖስ – ጌታ ስትመለስ ምን አለህ?

ሳምራዊው – ዘጠኙ የታሉ? አንተ ብቻ ነህ የዳንከው? ብሎ ጠየቀኝ። ጌታን ሊያመሰግኑ ባለመመለሳቸውም አዘነባቸው። እኔንም «እምነትህ አድኖሀል» ብሎ አሰናበተኝ።

ተርቢኖስ – አንተ እንድትመለስ ያደረገህ ምንድን ነው?

ሳምራዊው – ያደረገልኝ ውለታ ነዋ ከሰው ተነጥየ ከአገር ተገልዬ ከመኖር ከውርደት ላወጣኝ አምላክ ምሥጋና ቀርቶ ሌላ በከፈልኩት። እግዚአብሔርኮ በሕይወታችን ውስጥ ብዙ ጊዜ ከገደል፥ ከማጥ አውጥቶናል። ግን ያን አስታውሶ ተመስገን የሚለው ነው የጠፋው። እንዲያውም አንዳንዴማ በጉልበታችን፥ በዕውቀታችን አገኘነው ብለን እንኮራብታለን።

ተርቢኖስ – አሁን ያለህበት ሁኔታ እንዴት ነው?

ሳምራዊ – ያደረገልኝን እየመሰከርኩ፥ ለውለታው ዕለት ዕለት ምሥጋና እያቀረብኩ እውነተኛ ልጆቹ የሚሠሩትን ለመሥራት እየተጋሁ በአገልግሎት እኖራለሁ።

ተርቢኖስ – እግዚአብሔር ይስጥልኝ ወንድሜ አመሰግናለሁ።

ከዚያ በኋላ ዘንበሪ ወደቀረቀራት የሰማርያ ከተማ አመራሁ። ሰማርያ ማለት «የጠባቂ ግንብ» ማለት ነው አሉኝ አንድ አዛውንት መንገድ ላይ። ንጉሥ ዘንበሪ ሣምር ከተባለው ንጉሥ ገዝቶ ከተማዋን ቆረቆረና ሰማርያ አላት (1ኛነገ.16፥24) በ722 ዓ.ዓ አሦራውያን ከተቆጣጠሯት በኋላ መጤዎችን አሠፈሩባት። የዛሬዎቹ ሣምራውያን የነዚያ ትውልድ ናቸው። ከኢየሩሳሌም 65 ኪ.ሜ ትርቃለች። የያዕቆብ ምንጭ የሚገኘው ከዚህ አጠገብ ነው። ያዕቆብ ከሶርያ ሲመለስ በሴኬም ፊት ለፊት አረፈ። ከኤምር ልጆችም ርስቱን በ100 በግ ገዛው ከዚያም የውኃ ጉድጓድ ሠራበት። ጥልቀቱ 32 ሜትር ነው። በዚህ ጉድጓድ አጠገብ ነበር ጌታ ሳምራዊቷን ሴት ያነጋገራት። እርሷ የነበረችባት ከተማ ሲካር ትባላለች። ከሴኬም በስተደቡብ በ1 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ትገኛለች። ከጌባል ተራራ ግርጌ። ዛሬ ያች ሴት በሲካር ከተማ በዮሐንስ አምባ ከፍተኛ 4 ትኖራለች። ቤቷም በቀበሌ 7 ይገኛል። ዛሬ እንደ ድሮው ውኃ ለመቅዳት ከ1 ኪ.ሜ በላይ አትጓዝም የዘለዓለም ሕይወት አግኝታለችና ያነጋገርኳት በግቢዋ ውስጥ ነበር።

ተርቢኖስ – እስቲ ስለዚያ ጊዜው ጉዞሽና ገጠመኝሽ አውጊኝ?

ሳምራዊቷ – በቤት ውስጥ ልጅ አልነበረኝም። ገረዶችም የሉኝም። ስለዚህ ራሴ ውኃ መቅዳት ነበረብኝ። እናም ጠዋት ማታ ያንን የድንጋይ እንሥራ ተሸክሜ ወደ ያዕቆብ ምንጭ እጓዝ ነበር። በዚያን ቀን ወደ ጉድጓዱ ሳመራ አንድ መልኩ የሚያበራ የሚመስል ደርባባ ሰው ከጉድጓዱ አጠገብ ተቀምጦ አየሁ ከእርሱ ራቅ ብሎ የተወሰኑ ሰዎች ወደ ሲካር ከተማ ያመራሉ።

ጠጋ ብየ ውኃ መቀዳት ስጀምር «እስቲ ውኃ አጠጭኝ» አለኝ። ድምፁ የርኅራኄ ቅላፄ አለበት። አይሁዳዊ ነው አለባበሱ ያስታውቃል። ታዲያ ነገሩ እንዴት ነው ብዬ «አንተ አይሁዳዊ ሳለህ ከእኔ መጠጥ ትለምናለህን?» ብየ ጠየቅሁት። እርሱ ግን ፈገግ ብሎ የዘላለም ሕይወት ሊሰጠኝ የሚችል መሆኑን ነገረኝ። እኔም ይህን ጉድጓድ ከሰጠን ከያዕቆብ ይህ ሰው ይበልጣልን ብዬ ተገረምኩ። በዚህን ጊዜ «እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ለዘለዓለም አይጠማም» አለኝ። ድካሜ ጀርባዬ ታይቶኝ «እባክህን ስጠኝ» አልኩት። «መጀመሪያ ባልሽን ጠርተሽ ነይ» አለኝ። ነገሩ ግራ አጋባኝ የልቤን እንዴት ዐወቀ አልኩ «የለኝም» አልኩት። እርሱ ግን ስላገባኋቸው ባሎቼ ሁሉ ነገረኝ። በዚህ ጊዜ «ነቢይ ነህን?» አልኩት። «የኢየሩሳሌም ሰዎች በኢየሩሳሌም ብቻ ስገዱ ይላሉ አባቶቻችን ግን በዚህ በገሪዛን ተራራ



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ሰገዱ» አልኩት። እርሱም «ለአብ የሚሰግዱ በእውነትና በመንፈስ የሚሰግዱበት ቀን ይመጣል» አለኝ። እኔም መልሼ «መሲሕ ሲመጣ ሁሉን ይነግረናል» አልኩት። ያ መሲሕ እርሱ መሆኑን አበሠረኝ ወዲያውም ማድጋዬን ትቼ ወደ ሲካር ከተማ ተመለስኩና ለከተማዋ ነዋሪዎች ሁሉ ዜናውን ተናገርኩ ተከትለውኝም መጡ።

ተርቢኖስ – ለምንድን ነው ማድጋውን ጥለሽው የሄድሽው?

ሳምራዊቷ – ክርስቶስን ካገኙ ወዲያ የምን ማድጋ ማንገት ነው። ሄዶ ተአምሩን መንገር ነው እንጂ። ምንጊዜም ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ ከነ ኃጢአት ማድጋችን ? የዝሙት፥ የክፋት፥ የጉቦ፥ የቅሌት፥ የሥልጣን መባለግ፥ የስርቆት፥ የጠብ ጫሪነት፥ የስግብግብነት፥ የአምልኮ ጣዖት፥ የገንዘብ ፍቅር...ማድጋ ሰይጣን ያሸክመናል። ነገር ግን ክርስቶስ ራሱን ከገለጸልን በወንጌል ከተናገረን ማዳኑን ካሳየን ችግራችን ከወደቀልን በኋላ ያንን ማድጋ መተው አለብን። የዘመናችን ክርስቲያኖች ችግር ይህ ነው። ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደን እናስቀድሳለን፥ እንጸልያለን፥ እንማራለን ግን ከነ ማድጋችን እንመለሳለን። ክርስቶስ የሚፈልገው ግን ሄደን ዜናውን እንድንነግርለት ሌሎችም ማድጋቸውን ያወርዱ ዘንድ እንድንጋብዝለት ነው።

ተርቢኖስ – የአካባቢው ሰዎች እሺ ብለው መጡልሽ?

ሳምራዊቷ – ሁኔታውን ሲሰሙ ተንጋግተው መጡ። ወደ ከተማ ይገባ ዘንድ ያስተምራቸውም ዘንድ ለመኑት። ገብቶም ሁለት ቀን አደረ ብዙዎችም አመኑበት።

ተርቢኖስ – ከዚህ ታሪክ እኛ ምን መማር አለብን ትያለሽ ?

ሳምራዊቷ – ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ትዳራችን፥ ኑሮአችን፥ ሥራችን፥ ሕይወታችን፥ ሥልጣናችን፥ ሀብታችን፥ ዕውቀታችን ጉባዔያችን እንጋብዘው ይመጣል። ከእኛም ጋር አድሮ መሥራት የሚገባንን ቀናውን መንገድ ያስተምረናል። ዕውቀታችን ለጦር መሣሪያ፥ ለመርዝ፥ ለማጥፋት፥ ለክፋት፥ እንዳይውል፥ ሥልጣናችን ሰዎችን ለማንገላታት፥ አገር ለማራቆት እግዚአብሔርን ለመካድ ድሆችን ለማሰቃየት እንዳይውል፥ ሀብታችን ለጥጋብ፥ ለጉልበተኝነት፥ ለፍቅረንዋይ፥ ለዝሙት፥ ለስካር እንዳይውል፥ ትዳራችን የመጥፎ ልጆች ማፍሪያ፥ የጭቅጭቅ ማደሪያ እንዳይሆን፥ ዓለማችን የጦርነት ቋያ፥ የችግር መብቀያ እንዳትሆን፥ ያስተምረናል ይመራናል መንገዱንም ይገልጥልናል።

ተርቢኖስ – ዛሬ ከጥንቱ ኑሮሽ ያሳየሽው ለውጥ ምንድነው?

ሳምራዊቷ – እንደዛን ጊዜው ድካሜ ቀርቷል፥ ባል እንደ ሸሚዝ መቀያየር ቀርቷል ዛሬ ቤቴ የክርስቲያኖች መማሪያ የደቀ መዛሙርት ማረፊያ ነው።

ተርቢኖስ – ስለ ሰጠሽኝ መልስ በልዑል እግዚአብሔር ስም ምሥጋናየን አቀርባለሁ።

አሁን ደግሞ ወደ ምሥራቅ እሥራኤል ነው የምናመራው ከኢየሩሳሌም 25 ኪ.ሜ ርቀት ወደምትገኘው ኢያሪኮ። የ3000 ዓመት ዕድሜ ያላት ጥንታዊት ከተማ ቢታንያን አልፈን ወደ ምሥራቅ ስናመራ ከኢየሩሳሌም 15 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ያ በወንበዴዎች እጅ የወደቀውና የተደበደበው ሰው የወደቀበትን ቦታ እናገኛለን (ሉቃ.10፥30–37።) ይህ ቦታ አድሚን ይባላል። «የደም ቦታ» ማለት ነው። «እያሪኮ ማለት» ይላሉ ያገሬው ሰዎች «የጨረቃ ከተማ» ማለት ነው። መንገዱን ይገፔ ስገባ ነበር ማርቆስ ከተባለው ትንሽ መንደር ውስጥ በሠፈር 10 የቤት ቁጥር 46 በርጤሜዎስን ያገኘሁት። ሰው ልኬ ከቤቱ አስጠራሁትና ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ የመጣሁ በትን ምክንያት ነገርኩት። እርሱም ወደ ሠረገላዬ አብሮኝ ወጥቶ ከተቀመ ጥን በኋላ ውይይታችንን ቀጠልን።

ተርቢኖስ – ዓይንህ ከመብራቱ በፊት የነበረውን ሁኔታ ብትገልጽልኝ?

በርጤሜዎስ – አባቴ ጤሜዎስ ይባላል። ስወለድ ጀምሬ ነው አሉ የታወርኩት ምንም ላገለግላቸው አልቻልኩም እናም ከድህነታችን የተነሳ ወደ ልመናው መስክ ተሰማራሁ። የኢያሪኮ በር ደግሞ ብዙ ነጋዴዎች ስለሚመላለሱበት ብዙ ምጽዋት እናገኝ ነበር።

ተርቢኖስ – እስቲ በዚያን ጊዜ እንዴት ከጌታችን ጋር እንደተገናኘህ አውጋኝ?

በርጤሜዎስ – ቀኑን ሙሉ ስለምን ነው የዋልኩት በኋላ የሚንጫጫ የሕዝብ ድምፅ ሰማሁ። በአጠገቤ የሚያልፉትንም ሰዎች «የምን ድምፅ ነው» ብዬ ስጠይቃቸው «ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢያሪኮ ያልፋል» አሉኝ። ነፍሴን አላውቀውም የለመንኩትን ገንዘብ የለበስኩትን ድሪቶ ጥዬ «የዳዊት ልጅ ማረኝ» እያልኩ ጮኽኩ በአጠገቤ የነበሩት ሰዎች ስወድቅ ስነሣ የዕውር ድንብሬን ስሮጥ ሲያዩ «የዕውር ቅንጡ አርፈህ ተቀመጥ» እያሉ ሰደቡኝ። ሌሎች ደግሞ ጎትተው ሊያስቀምጡኝ ሞከሩ። እኔ ግን ጩኸቴን አበዛሁ። ወዲያውም አንድ የሚያስደስት ድምፅ ሲናገረኝ ሁሉም ጸጥ አሉ። በአጠገቤ የነበሩትም «ይጠራሃል» አሉኝ እየተደናበርኩም ወደእርሱ ቀረብኩ። ጌታችንም «ምን ላድርግልህ» አለኝ። «ለማየት እፈልጋለሁ» አልኩት። «ሂድ እምነትህ አድኖሃል» ሲለኝ ዓይኖቼ ተገለጡ። ብርሃንንም ዓየሁ ተከተልኩትም።

ተርቢኖስ – በርጤሜዎስ እንጂ – ያ ሁሉ ሕዝብ ሲገሥጽህ ወደ ኋላ ለመመለስ አልዳዳህም?

በርጤሜዎስ – እኔ የምፈልግ መዳኔን ነው። ሺህ ጊዜ ቢለፈልፉም አልተመለስኩም። እርግጥ ወደ እግዚአብሔር ስትቀርብ ብዙ ሰዎች ሊያሾፉብህ፥ ሊተርቡህ፥ መካሪ መስለው ሊቀርቡህ፥ ሊያሰናክሉህ በሕይወትህም ሳንካ ሊገጥምህ፥ ...ይችላል። ነገር ግን ፍላጎትና ቆራጥነት ካለህ ወደ ጌታ ከመቅረብ መዳኑን አግኝተህ ብርሃኑን ከማየት የሚያግድህ የለም። አንዳንዶች ምክንያት በመደርደር ወደ እግዚአብሔር ያልቀረቡበትን ምክንያት ሊያሳምኑ ይሞክራሉ። ይህ ሊሆን አይችልም ወደ ማዳኑ ከመቅረብ የሚያግደን ምንም ነገር የለም። መሰናክሉን ችለን አብዝተን መጮህ ነው። ከዚያ በኋላ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

እግዚአብሔር ፈተናውንም፥ መሰናክሉንም ጸጥ ያደርገዋል። ወደእርሱም እንቀርባለን። የኃጢአት ዕውርነታችንንም ይገፈዋል። የማዳን ብርሃንንም ያሳየናል።

ተርቢኖስ — ከዚያ በኋላ እንዴት ሆንክ?

በርጤሜዎስ — ከዚያ በኋላማ ወደ ኋላ ሳልል በመንገዱ ተከተልኩት።

ቴርቤኖስ — እግዚአብሔር ይስጥልኝ በርጤሜዎስ።

ከዚህ በኋላ ሠረገላዬን አስነሥቼ ወደ መሐል ኢያሪኮ ገባሁ። ዘኬዎስን የት ማግኘት እንደምችል ጠየቅኩና ወደ ቤቱ ገሠገሥኩ። በሉቃስ መንደር ቁጥር 19 መንገድ ይኖራል። የተንጣለለ ግቢ ነው። ከመንገዱ ዳር ያች የዋርካ ዛፍ ዛሬም ትታያለች። የአካባቢው ሰዎች እየመሩኝ ከሠረገላዬ ወርጄ ወደግቢው ተጠጋሁና አንኳኳሁ አንድ አሽከርም ሮጦ መጣና ከፈተልኝ። ዘኬዎስን እንደምፈልግ ከገለጽኩለት በኋላ ወደ ውስጥ ይዞኝ ገባ። ድንክዬው ዘኬዎስ ጐልመም እያለ ወደእኔ መጣ። የደስ ደስ ያለው አጭር ነው። ሰላምታ ተለዋወጥንና የመጣሁበትን ጉዳይ ገለጽኩለት። እየሳቀ ወደ እንግዳ መቀበያው ወሰደኝ። የቀረበልኝን ምሳ በልቼ ውይይታችንን ጀመርን።

ተርቢኖስ — እስቲ ስለቀሮህ አውጋኝ?

ዘኬዎስ — የምኖረው በኢያሪኮ ከተማ መሐል እንደምታየው ነው። ሥራዬም የቀራጮች አለቃነ ነው። ቀረጡ ለሮማውያን የሚገባ ስለሆነ አገር በዝባዦች ቀማኞች እየተባልን በሕዝቡ እንሰደባለን የተጠላንም ነን ማንም አይቀርበንም።

ተርቢኖስ — እንዴት ነበር ከጌታችን ጋር ለመገናኘት የበቃኸው?

ዘኬዎስ — (ፈገግ ብሎ) ብዙ ጊዜ ላየው እንደማቴዎስ እኔም እቤቴ ልጋብዘው እመኝ ነበር። ታዲያ አንድ ቀን የመጨረሻውን ጉዞ ወደ ኢየሩሳሌም ሲያደርግ ወደ ኢያሪኮ ከተማግባ። በዚህ ጊዜ በጣም የሚገርመኝ በእኔ ቤት አጠገብ ወዳለው መንገድ አመራ። እኔም ሰው ምን ይለኛል ሳልል እንደ ዝንጀሮ ተንጠላጥዬ ሾላዋ ዛፍ ላይ ወጣሁና የናፈቅኩትን ክርስቶስ አየሁት። እርሱም ዘወር ብሎ አየኝና ወደኔ ሲመጣ ገረመኝ ከዚያም ከዛፉ ሥር ቆሞ «ዘኬዎስ ሆይ ዛሬ በቤትህ እውል ዘንድ ይገባኛልና ውረድ» አለኝ። ባየሁት ስል ቤቴም ሊገባ ነው ሮጬ ገብቼ እልፍኙን አዘጋጀሁ። ብዙ ሰዎች ግን ከኃጢአተኛ ጋር ሊውል ገባ እያሉ ሲያጉረመርሙ ሰማኋቸው። እርሱ ግን አልናቀኝም እኔም የሠራሁትን ሳልደብቅ ዘረዘርኩለት። ከዚያ ቀጠል አድርጐ «ዛሬ ለዚህ ቤት መዳን ሆኖለታል» ብሎ አበሠረኝ። ከሰውም ጋር እኩል አደረገኝ።

ተርቢኖስ — ከዚህ ካንተ ገጠመኝ ምን እንማራለን ዘኬዎስ ?

ዘኬዎስ — አንተ እግዚአብሔርን ለመቅረብ ከፈለግህ የሚያግድህ ምንም ነገር የለም። እርግጥ ሾላ ላይ መውጣት በእኔ ዕድሜ ላለ ሰው ያሳፍራል የልጅ ሥራ ነው። ነገር ግን ተዋርደንም ይሁን ተንቀን ለፕሮቶኮላችን፥ ለሥልጣናችን፥ ለውበታችን ካልሳሳን በስተቀር ማግኘቱ ቀላል ነው። ነገር ግን የዓለምን የክብር ደረጃ ላለማጣት ስንጠነቀቅ በራችን ላይ ያለው ክርስቶስ አልፎን እንዳይሄድ ወደ ቤት ጋብዘነው ማዳኑን ሊገልጽልን ሲወድ ሾላ ላይ መውጣትን ንቀንና ተጸይፈን እንዳንሸሸው ያስፈልጋል። እርሱ ሰው አይንቅም ወደጋበዙት ሁሉ ይመጣል የወደቁትን ያነሣል፥ የተረሱትን ያስታውሳል። የተጠሉትን ያፈቅራል። እናም ይኼን አምነን ምንም ይሉኝታ ሳይገድበን ክብረ ዓለም ሳይገታን እንውደደው ይመጣል። የልባችንንም ገልጸን እንንገረው ማዳኑን ያበራልናል። ልጆቼም ይለናል።

ከዘኬዎስ ጋር ተሰናብቼ ወደ ቤተፋጌ ሄጄ እነዝያ አህዮች የታሠሩበትን ቦታ ጐበኘሁ። ከዚያም ወደ ቢታንያ ገባሁና እነ ማርታን ሰላም ብየ ወደ ኢየሩሳሌም አቀናሁ። ምእመናን ወገኖቼ ሆይ ክርስቶስ ያዳናቸው ከማዕበል ያተረፋቸው፥ ከስቃይ የፈወሳቸው፥ ከመከራ የነጠቃቸው፥ ብርሃን የገለጸላቸው እጅግ በጣም ብዙ ናቸው። ነገር ግን «ለጠቢብ አንዲት ቃል ትበቃዋለች» ነውና ለማመን እነዚህ በቂ ናቸው። ሕይወታችንን በሰባቱ ሰዎች መስታወት እንየው ራሳችንን እንመርምረው ወደ እግዚአብሔር አልቀረብን ከሆነም ማናቸውም ፈተና ሳይገድበን ዛሬውኑ ወደ ሾላዋ ዛፍ ወደቅድስት ቤተ ክርስትያን እንሂድ ጌታን ታሳየናለች። አግኝተነው ውለታ ቢሶች ሆነን ከሆነም ዳግም በይቅርታ እንቅረበው እንደ ጥብርያዶስ ደቀ መዛሙርት ልጆቼ እያለ ይከተለናል። በሉ ለሁሉም የልዑል እግዚአብሔር ፍቅር የእመቤታችን አማላጅነት አይለያችሁ ደናህ ሁኑልኝ።

ተርቢኖስ ነኝ ከኢየሩሳሌም የቀራንዮ ቴሌቭዥን ጣቢያ ✣

ደብረ መድኃኒዓለም

## መፍቻ

መንደር ፥ ክፍለ ከተማ :- የሚሉት በወንጌል ውስጥ ታሪኩ የሚገኝበትን ወንጌላዊ ያመለክታሉ።

ከፍተኛ ፥ ቁጥር:- የሚሉት ምዕራፉን ያመለክታሉ።

ቁጥር መንገድ፥ ቀበሌ :- የሚሉት ቁጥሩን ያመለክታሉ።

## ዋቤ


የቦታዎች ገፅታና ታሪኩ :- የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፥ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፥ አዲስ አበባ

ቅድስት ሀገር በአዲስ ኪዳን ዘመን፥ የምሥራች ድምፅ፥ ዓ.ም. አዲስ አበባ

ጉዞ ወደ ኢየሩሳሌም፥ መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ፥ የተቀዳ የካሴት ትምህርት፥ አዲስ አበባ ሥላሴ ካቴድራል።

የቅዱስ ወንጌል ትርጓሜ፥ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፥ 1966፥ አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ምእመናን መታሰቢያ ድርጅት ሕንፃ ምረቃ መታሰቢያ መጽሐፍ፥ ድርጅቱ ያሳተመው፥ አዲስ አበባ





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# እናስተዋውቃችሁ

በዚህ ዓምድ ገዳማትን አድባራትን ታሪካዊና ተአምራዊ ቦታዎችን የቤተክርስቲያን አባቶችን እናስተዋውቃለን።

## የጣና ሐይቅ ዕንቁዎች

ክፍል 1

ከሐመር ዘጋቢ

ታሪካዊና መንፈሳዊ ቦታዎችን ለምእመናን ገሐድ አውጥታ የምታስተዋውቀው የዛሬዋ ሐመር ዛሬም በጣና ሐይቅ ላይ መንሳፈፍዋን ተያይዛዋለች። በጣና ሐይቅ ውስጥ ያሉትን ታሪካዊ ገዳማት ለምእመናን ዕይታ ለማብቃት። ራሳቸውን በሐይቁ ሽፍነውና ሰውረው የሚገኙት እነዚህ ገዳማት በውስጣቸው አቅፈውና ደግፈው የያዙዋቸው ጥንታውያን ንዋየ ቅድሳት እና ቅርሶች የቤተ ክርስቲያንዋ መታወቂያ ከመሆናቸውም በላይ የማንኛውም ኢትዮጵያዊ የማንነት መግለጫ አንጡራ ሀብቶች ናቸው። ከሰባት መቶ ዓመት ዕድሜ በላይ እንዳላቸው የሚነገርላቸው ገዳማት በዚሁ ሐይቅ ባሉት ደሴቶች ውስጥ ይገኛሉ።

እነዚህን የረዥም ዕድሜ ባለጸጐች የሆኑትን የጣና ደሴት ገዳማት በዓይኑ ዓይቶ ለመረዳት ቆርጦ የተነሣ ቁጥሩ በርካታ የሆነ የባሕር ዳር ምእመን ጥር 14/1986 ዓ.ም. «የጣና ነሽ» በተባለችው ትልቅዋ የባሕር ትራንዚት መርከብ ወደ ጣና ደሴቶች ጉዞ አድርጐ ነበር። በዚሁ ዕለት እኔም ይኽን አጋጣሚ በመጠቀም ወደ ባሕር ዳር ተጉዤ ነበር።

ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ከሃያ አምስት ደቂቃ ላይ የተሣፈርንባት መርከብ «የጣና ነሽ» የጥሩምባዋን ጩኸት አስተጋባች። የጉዞ መጀመሪያ ማመልከቻ መሰለኝ ወዲያው ሞተርዋን አሟሙቃ በሾለ አፍንጫዋ የጣናን ባሕር ለሁለት እየከፈለች ጉዞዋን ወደ ደሴቶቹ አደረገች።

ጉብኝቱን ያዘጋጀው ክፍል የፈተልን የመዝሙር ካሴት የያሬድን ጥዑም ዜማ ከባሕሩ ተነስቶ በቅዝቃዜ ሰውነታችንን ዳበስ አድርጐት ከሚያልፈው ቀዝቃዛ ነፋስ ጋር አዋሕዶ ልብን በተመስጦ ሰማየ ሰማያት የሚያመጥቅ ዓይነት ነበር።

በዝና በጽሑፍ የማውቀውን ደቅ ደሴትን ዛሬ በዓይኔ ላየው ነው። መርከብዋ በባሕሩ ላይ እየተንሣፈፈች ነው። የደቅ ደሴት በጣም ርቆ ይታያል። መርከብዋ በረንዳ ላይ ሆኜ የራቀውን አቅርቦ በሚያሳየው የመርከበኞች መነፅር ደሴቱን እያየሁ ለጊዜው እንድጽናና ብሎ ይመስላል ከበዓሉ አዘጋጅ አንዱ መነፅሩን አመጣልኝ። እኔም ማንገቻውን በአንገቴ አጥልቄ ከሩቅ እንደ ሕልም የሚታየውን ዳጋን በመነፅሩ ማየት ጀመርኩ። ከደቅ ደሴቶች አንዱና ዋነኛው የሆነውን ዳጋ እስጢፋኖስን ፊት ለፊቴ ገጭ ብሎ አየሁት። በዕፀዋት የተሸፈነ ደናማ መሆኑን ከወዲሁ ገመትኩ።

ገዳመ ዳጋ ስሜቱን ይበልጥ ሳበው መርከብዋ የኋሊት የምትጓዝ እንጂ ወደ ፊት የምትሄድ አልመስልህ አለኝ። መቼም የማይደረስበት የለም ደረስን። መርከብዋም መውረጃዋን ወደ ወደቡ አዞረች። የመርከብዋ ሠራተኞችም በወደቡ ላይ ከተተከለው ችካል ጋር መርከብዋን በገመድ ወጥረው አሠሩ። ጉዞ ወደ ዳጋ እስጢፋኖስ በአንስተኛና ዝግተኛ ጀልባ። ከባሕር ዳር በሁለት ሰዓት የሚደረስበት መሆኑን አረጋግጫለሁ። ዳጋ ከባሕር ዳር ምዕራብ ከሚገኙ ደሴቶች መካከል አንዱ ነው። አቀማ መጡ እንደ ትእምርተ መስቀል ያለ ሆኖ በመካከሉ ርዝመት አለው። በጐኑ ከሚገኘው ከደቅ ጋር ተመሳሳይ ቅርፅ አላቸው።

የዳጋ ቁመት ከደቡብ ሰሜን አምስት ኪ.ሜ ያህል ይረዝማል ከራስጌው ትንሽ ሠፋ ይልና እስከ ግርጌው እየቀጠነ ይሄዳል።

በዚህ ገዳም ውስጥ የማይበቅል የዕፀዋት ዓይነት የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም። በውስጡ የሚገኙ ዋርካዎች በኢትዮጵያ በግዝፈታቸው አሉ ከሚባሉት ዕፀዋት በሦስት እጥፍ የሚተልቁ እንደሆኑ ተረጋግጧል። ደሴቱን ዕፀዋት እንደ ጋቢ ጀቡነውታል።

ከመርከቡ ከወረዱ በኋላ ሩብ ሰዓት ያህል የሚወስድ የእግር መንገድ ሲኖረው እንደ ቀራንዮ ኮረብታ ዳገታማ ነው። ቤተ ክርስቲያኑ ያለው ከደሴቱ አናት ኮረብታማ ሥፍራ ላይ ነው።

በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ አካባቢ ሎሚና የሙዝ ተክል የመሳሰሉ ዕፀዋት እጅብ ብለው ይታያሉ። በደሴቱ አካባቢ የሚነፍሰው ነፋስ ሕይወትን የሚያድስና መንፈስን በሐሴት የሚያሰክር ነው። ገዳማውያኑ እንደሚሉት ከሆነማ በጎንደር የነገሡት ነገሥታት ሁሉ ይህን ገዳም ጎብኝተው ከሰው ተለይተው ሦስት ሱባዔ አራት ሱባዔ ያህል ይይዙበት



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ነበር። ገዳሙንም አምሳለ ገነት ብለው ይገምቱት እንደነበርና እሑድ እሑድ የገነት ነፋስ ይነፍስበት ነበር ይላሉ። በእርግጥም የገዳሙን መሬት የረገጠ ሁሉ አምሳለ ገነት ነው ብሎ ከመናገር ወደ ኋላ አይልም። ነገሥታቱ በደሴቱ ውስጥ በሕይወተ ሥጋ እያሉ ብቻ ሳይሆን ከሞቱም በኋላ የዳጋ አየር አይልቀቀን ብለው አጽማቸው ያረፈው በዚሁ በዳጋ ነው።

ገዳሙን ያቀኑት አባት አቡነ ኂሩተ አምላክ የተባሉ የአፄ ይኩኖ አምላክ የወንድም ልጅ ናቸው። ገዳመ ዳጋ እስጢፋኖስ የተመሠረተው በ1268 ዓ.ም. በአፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት እንደሆነ ይነገራል። የገዳሙ አቅኚ አባ ኂሩተ አምላክ እና አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከአባ ኢየሱስ ሞዓ በሐይቅ ሥርዓተ ምንኩስና ሲማሩ ኖረዋል። ከዚያም አፄ ይኩኖ አምላክ አባ ኢየሱስ ሞዓን ለመገናኘት ሄደው ሳለ አባ ተክለ ሃይማኖትን ሊቀካህናት ብለው ሹመው አባ ኂሩተ አምላክን ዐቃቤ ሰዓት አድርገው ብለው አባ ኢየሱስ ሞዓ ለአፄ ይኩኖ አምላክ ስለነገሯቸው ወዲያው አባ ተክለሃይማኖትን በመላው ኢትዮጵያ



አስጎብኝዎቻችን

ሊቀ ካህናት ብለው ሲሾሙ እሊህ አባትም (አባ ኂሩተ አምላክ) ጥቂት ጊዜ በዐቃቤ ሰዓትነት ማዕረግ ካገለገሉ በኋላ ቅዱስ ጳውሎስ አሁንም ወደ እሱ ከከተማው እንውጣ ተግዳሮቱን ተሸክመን» ዕብ.13፥13 ያለውን በመያዝ በዓለም በከተማ ተቀምጦ እግዚአብሔርን ከማገልገል ከከተማ ወጥቶ ከሰው ተለይቶ እግዚአብሔርን ማገልገል ይበልጣል ብለው ከአፄ ይኩኖ አምላክ የተቀበሉትን ማዕረገ ሹመት ንቀው አልባሌ መስለው ተርታ ልብስ ለብሰው ታቦተ እስጢፋኖስን ከሐይቅ ይዘው ከአንዱ ገዳም ወደ ገዳም ሲዘዋወሩ በእግዚአብሔር ፈቃድ ዳጋ ወደተባለው ደሴት ደርሰዋል። «ከታንኳም ወርደው» ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም» ትርጓሜው «ይህች የዘለዓለም ማረፊያዬ ናት» ብለው ጥቂት ሰዓት እረፍት አድርገዋል። ያረፉበትም ቦታ በማዕረግ ስማቸው ዐቃቤ ሰዓት ተብሎ ይጠራል። ከወደቡ እስከ ቤተ ክርስቲያኑ ባለው የእግር መንገድ መሐል ዳገቱ ላይ ጫካው ውስጥ የፃድቃን ማረፊያ የተባለ ቦታ አለ። በዚህ ቦታ ላይ ወደ ገዳሙ ሲመጡ በባሕሩ ላይ እያንሳፈፈ ያመጣቸው እንደ መርከብ ጐድጐድ ያለ ጥቁር ድንጋይ ይገኛል። ይህ ድንጋይ እንደ ታንኳ ተጠቅመውበት የመጡበት እንደሆነ መነኮሳቱ ይናገራሉ። ምናልባት የፃድቃን ማረፊያ የተባለው ሥፍራ ጻድቁ ጥቂት ሰዓት ያረፉባት ሳይሆን አይቀርም።

በዚሁ ገዳም በአብርሃ ዘመነ መንግሥት በቅድስት ድንግል ማርያም ስም ቤተክርስቲያን ታንፆበት ስለነበር እሊህ ጻድቅ ታቦተ ማርያምን እያጠኑ የተባሕትዎ ሥራ እየሠሩ እስከ አፄ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ቆይተው በአፄ ዓምደ ጽዮን ፈቃድ ታቦተ ማርያምን በደቅ ውስጥ ኮታ በሚባለው ቦታ ተክለዋል። ታቦተ ማርያም ወደ ኮታ ከሄደች በኋላ ግን ታቦተ እስጢፋኖስ ተብሎ ሲጠራ ይኖራል።

ቤተ ክርስቲያኑ የተሠራው በአፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት ቢሆንም በጥንት ጊዜ የታነፀው ቤተ ክርስቲያን በድጋሚ ታንፅዋል። በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ፥ በአፄ ሱስንዮስና በአፄ ፋሲል ዘመነ መንግሥት የተለያዩ የመሠረትና የዕድሳት ዕድሎች እንዳገኘ ይነገራል። የቤተ ክርስቲያኑ የሣንቃ መዝጊያዎች ፍጹም ግዙፍና ወፍራም ናቸው። አንዱ ሳንቃ የአምስት ሜትር ቁመትና የሦስት ሜትር የወርድ ስፋት አለው። በውስጡ በአፄ ፋሲል ዘመን የተሠሩ የቅዱሳን ሥዕሎች ይገኛሉ።

ወደ ዕቃ ቤቱ ጐራ ባልን ጊዜ እጅግ የሚያስደንቅ ትእይንት ነበር የገጠመን። በዚሁ ደሳሳ ጐጆ በሆነ ዕቃ ቤት የሚገኙት ንዋየ ቅድሳት እና ቅርሶች በገንዘብ ሊተመኑ የማይችሉ ናቸው። በቁጥር በርከት ያሉና በመጠናቸው ግዙፍ የሆኑ በጥንት ጊዜ የነበሩት ቅዱሳን አበው ቀለም በጥብጠው ብራና ዳምጠው የጻፉዋቸው የብራና መጻሕፍት ለዓይን ይታክታሉ። አብዛኛዎቹ በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ፥ በአፄ ሱስንዮስና በአፄ ፋሲል ዘመነ መንግሥት የተጻፉና የተጠረዙ ናቸው።

እንዲሁም ልዩ ልዩ ረዥም ዘመን ያስቆጠሩ ንዋየ ቅዱሳት፥ የነገሥታት ቅርሶችና የታላላቅ ሰዎች የወግ ዕቃዎች ይገኙበታል።

ለምሳሌ ከአፄ ዘርዓ ያዕቆብ የተበረከቱ የብረት፥ የወርቅና የነሐስ መስቀሎች። ከአፄ ዳዊት የተበረከቱ የሚከፈትና የሚዘጋ የነሐስ መስቀልና ሌሎች መስቀሎች እንዲሁም ንዋየ ቅዱሳት። ከአፄ ዳዊትና ከአፄ ዘርዓ ያዕቆብ የተሰጡ ልዩ ልዩ የመላእክትና የጻድቃን ምስሎች ያሉባቸው የነሐስ መስቀሎች፥ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል የተሳለባቸው መስቀሎች «ወነበ ከመ ያንዝር» የሚል ጽሑፍ ያለው ከአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ለገዳሙ የተሰጠ የግል ሰይፋቸው ትልቅና ብዙ ሥዕሎች ያሉት የዓመቱ ገድለ



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ሰማዕታት የብራና መጻሕፍት በአፄ ይኩኖ አምላክና በአፄ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት የተበረከቱ አንድ ሰው ሊሸከማቸው የማይችል ግዙፍ የፋሲል አልጋ፥ እግሮችና መገጣጠሚያዎች፥ የፋሲል ካባዎችና ሌሎች ንዋየ ቅድሳትና ታሪካዊ ቅርሶች በብዛት ይገኛሉ።

ከንዋየ ቅዱሳቱና ከብራና መጻሕፍቱ እንዲሁም ከነገሥታቱ ዘውድና ካባ በተጨማሪ የአራት ነገሥታት አፅም በመስታወት ሣጥን ገብተው ተጠብቀው ይታያሉ። በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም አፅማቸው የሚገኘው ነገሥታት ስምና የንግሥስና ዘመናቸው ተጽፏል።

- አፄ ዳዊት የነገሡበት ዘመን ከ1382–1430 ዓ.ም።
- አፄ ዘርዓ ያዕቆብ የነገሡበት ዘመን ከ1434–1468 ዓ.ም።
- አፄ ሱስንዮስ የነገሡበት ዘመን ከ1607–1632 ዓ.ም።
- አፄ ፋሲል የነገሡበት ዘመን ከ1632–1667 ዓ.ም።

በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ሴቶች እንዳይገቡ የሚከለክል ሕግ አለ። የዳጋ እስጢፋኖስን ደንብ በመጣስ እቴጌ ምንትዋብ ሱሪ አድርገው ከወደቡ አንሥተው ምንጣፍ አስነጥፈው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ በሚጓዙበት ጊዜ መሐል ሲደርሱ እግራቸው ተሰንጥቆ ደም በደም እንደሆኑ ይነገራል። በዚህም የተነሣ በደቅ ደሴት ውስጥ «ናርጋ ሥላሴ» የሚለውን እንዳስተከሉ ትርጉሙም «በሥላሴ ፈቃድ እንርጋ» ያልተፈቀደልን ቦታ አንገባ ብለው እንደሆነ ይተረካል።

ዳጋ የሚለውን ስም እንዴት ሊያገኝ ቻለ የሚለው ጥያቄ የአንባቢያን ጥያቄ እንደሚሆን እርግጠኛ ነኝ። ለዚሁም የሚነገረው ነገር ቀደም ተብሎ ከላይ እንደተጠቀሰው ከወደቡ እስከ ቤተ ክርስቲያኑ ባለው የእግር መንገድ መሐል ዳገቱ ላይ ጫካው ውስጥ የጻድቃን ማረፊያ የተባለ ቦታ እንዳለና ወደ ቤተ ክርስቲያኑ የሚወጣ ሰው ሁሉ እዚያ ጥቂት ሳያርፍ አይጓዝም።

በኑዛዜያቸው መሠረት ይህ ቦታ የአፄ ዘርዓ ያዕቆብ አስከሬን «ዳ» በሚል «ሆሄ» የሚጀምር ሥፍራ ሲፈለግ፥ ዳቦት፥ ዳሞት ሳይቀር ሲንከራተት ቆይቶ እዚህች ሥፍራ ላይ ሲደርስ «ዳጋ» የሚል ድምፅ ይሰማና ለጥቂት ጊዜ ያርፋል። ከዚያም አሁን ከሚገኝበት ከገዳሙ ይገባል።

ዳጋ የተባለበትም ምክንያት በዚህች ቦታ በተሰማ ድምፅ ሲሆን ሙሉ መጠሪያው ዳጋ እስጢፋኖስ ነው። ዳጋ ማለት ዳገት ኮረብታ ማለት ሲሆን እስጢፋኖስ በሐዋርያት ሥራ በም.7 ላይ በአይሁድ ዘንድ ስለ ጌታችን ሲመሰክር በድንጋይ ተወግሮ የሞተውን ቀዳሜ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስን የሚያመለክት ነው። ምናልባት የገዳሙ አቅኚ አባ ሂሩተ አምላክ ከሐይቅ ይዘውት በመጡት ጽላተ እስጢፋኖስ የተነሣ ስያሜውን ያገኘ ይሆናል የሚል ግምትም አለ።

በዳጋ እስጢፋኖስ ያሉት መነኮሳት ከ150 በላይ እንደሚሆኑ አስጐብ?ኛችን መሪጌታ ዘርዓ ዳዊት እንግዳው ገልጸውልኛል። የደሴቱ የተፈጥሮ ጸጋና መስሕብ ብቻ ሳይሆን በውስጡ ያሉት መነኮሳት መንፈሳዊ ሕይወትም በአድናቆት አውታር ስሜትን ወጥሮ እዚያው ቅሩ ያሰኛል። ትሕትናቸው ታማኝነታቸው ጌታ እኔን ምሰሉ ያለውን በተግባር የተረጐሙ እንደሆኑ ያስገነዝባል።

ጉብኝቱ አብቅቶ ወደ ወደቡ ሳመራ የዳጋን ደሴት ወደ ኋላዬ ዘወር ብዬ ለመሰናበቻ አየሁት ግርማ ሞገስን ተጐናጽፎ በዓይኔ ላይ ገዝፎ ታየኝ። ገነታዊ አየሩም ልቤን መሰጠው።

በዚያች ቅድስት ቦታ አንድ ምዕራባዊ ጸሐፊ ተናገረ የተባለው ነገር በህሊናዬ አስተጋባ «ገነት የምትባል ልዩ ቦታ ኖራ ከነበርና አሁንም ካለች ያለምንም ጥርጥር ገነት ማለት ኢትዮጵያ ነች ያችውም ጣና ነች» ነበር ያለው።

በእርግጥ ይህ ጸሐፊ ጥሩ አስተዋይ ልቡና እንዳለው አረጋገጥኩለት። እውነትም አምሳለ ገነት። የዳጋ ገነት ነፋስ ነፈሰ ዳጋ እስጢፋኖስ በህሊናዬ የናፍቆት እሳት ጥሎ ወደ ኋላ ሸሸኝ።

የጣና ነሽ ጥሩንባዋን ነፍታ የተሲዓት ፀሐይ አርፎባት እንደ ፈርጥ የሚንቦገቦገውን የጣናን ባሕር በዚያ ስንደዶ መሳይ አፍንጫዋ እየከፈለች ጉዞዋን ወደ ዘጌ ሐይቅ ቀጠለች ዳጋ የመላእክት ባሕርይ ከተላበሱት መነኮሳቱ ጋር ወደ ኋላ ቀረ። አካሌ የጣና ነሽ ላይ ቢሳፈርም መንፈሴ ግን አሁንም ከዳጋ አልወጣም ነበር። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የቅርስ ግምጃ ቤት መሆንዋን በበለጠ ልረዳ የቻልኩት ዛሬ ነበር። ትምክህቱ ኢስፈላጊ ቢሆን ኖሮ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ልትመካ ይገባት ነበር አልኩ።

የጣና ነሽ ከሐመር ጋር በአንድነት ገመድ ተሳሥራ የጣና ሐይቅ በጉያዋ ሰውራ የያዘቻቸውን ዕንቁዎች ለዓለም ልታሳይና ልታበራ ወገብዋን ጠበቅ አድርጋ የተነሣች ይመስላል። ጉዞዋን ወደ ዘጌ ተያይዛዋለች።

መሪጌታ ዘርዓ ዳዊት ስለ ዳጋ ያለኝን የአድናቆት ስሜት ስገልጽላቸው «ገና ምኑን አይተህ ዘጌ ላይ ያለው ንዋየ ቅድሳትና ቅርስ የዳጋን ሁለት እጥፍ ያህላል ሲሉኝ» ጓጓሁ በሐሴት ሰከሬ ዘጌ ላይ እንዳልቀርፈራሁ። አቅርቦ የሚያሳየውን መነፅር ከአንዱ ወንድም ተቀብዬ ዘጌን ከሩቅ አየሁ። በስሜት ፈረስ ተፈናጥጬ በባሕሩ ላይ እየጋለብኩ ዑራ ደረስኩ። ዑራን በመነፅር ቀርባ አየኋት የጣና ነሽም ወደ ወደቡ እየቀረበች ነው። የመርከቡ ካፒቴን መርከብዋን ሊያቆም እየታገለ ነው። ሌሎች የመርከቡ ሠራተኞች የመርከብዋን ማሠሪያ ገመድ ወደ ወደቡ በመወርወር ላይ ናቸው። ✣

ይቀጥላል



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# አባ ሳሙኤል — ዘደብረ ቀልሞን

ታኅሣሥ 8

የተወለደው በደቡብ ግብፅ ዲክሉባ በሚባል ቦታ ነው። ወላጆቹ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ቤተክርስቲያንን የሚያከብሩ ነበሩ።

አባ ሳሙኤልም ከልጅነቱ ጀምሮ በቅዱሳት መጻሕፍት ተኮትኩቶ ስላደገ የምንኩስናን ሕይወት በእጅጉ ይመኝው ነበር። ከዕለታት በአንድ ቀን አመካኝቶ ከቤቱ ወጣና ወደ ገዳመ አስቄጥስ ለመሄድ ልቡን አነሳ። ነገር ግን ከአካባቢው ወጥቶ ስለማያውቅ የገዳሙ መንገድ ጠፍቶት ቆሞ ሳለ የልዑል እግዚአብሔር መልአክ በመነኩሴ ተመስሎ ወደሱ መጣና «ልጄ ወዴት ትሄዳለህ» ሲል ጠየቀው አባ ሳሙኤልም «እኔስ ወደ ገዳመ አስቄጥስ ልጓዝ ፈልጌ ነበር» አለው። እኚያም መነኩሴ «እኔም ወደ ዚያው እየሄድኩ ነው» ብለው ይዘውት ሄዱ። መቼም እግዚአብሔር የለመኑትን የሚሰማ ነውና የዚያን ሕፃን ልቦና ተመልክቶ በመልአኩ መሪነት ወደ ገዳመ አስቄጥስ አደረሰው።

በዚያም ገዳም አባ አጋቶን የተባለ አረጋዊ አባት ነበር። መልአኩ «ይህንን ሕፃን ተቀብለው÷ የምንኩስናንም ልብስ አልብሰው ካንተም በኋላ የሚተካህ እርሱ ነውና ልጄ በለህ አስተምረው።» ብሎ አስረከበው። አባ አጋቶንም በታላቅ ደስታ ሳሙኤልን ተቀብሎ «አመጣጥህ መልካም ናት÷ በእርጅናየ ዘመን እግዚአብሔር አንተን ልኮልኛልና።» በማለት ወደ ቤተ ክርስቲያን አስገብቶ ጸለየለት የምንኩስናንም ልብስ አለበሰውና «የአባቶቼ የአባ አንጦንስና የአባ መቃርስ አምላክ ካንተ ጋር ይሁን» አለው ሳሙኤልም «አባቴ ሆይ እግዚአብሔር ፈቃዱን ለመፈጸም ያበቃኝ ዘንድ አስበኝ» አለው።

ከዚህ በኋላ ከአባ አጋቶን እግር ሥር እየተማረ ለ3 ዓመት ከኖረ በኋላ አባ አጋቶን አረፈና ወደ አባቶቹ ተደባለቀ። አባ ሳሙኤልም በቤተ ክርስቲያኑ ያገለግል ዘንድ በክህነት ተሾመ።

ከጥቂት ጊዜም በኋላ የከሃዲው የልዮን መልእክት ወደ ገዳሙ መጣች። ያችም እውነተኛውን እምነት አጥፍታ ክህደትን እመኑ የምትል ነበረች። አረጋውያን አባቶቻችንም ነገሩን በሰሙ ጊዜ በእጅጉ አለቀሱ። አባ ሳሙኤል ግን ልቡ ለሃይማኖቱ በጣም ስለተቃጠለበት በንጉሡ መልእክተኛ ፊት ደብዳቤውን ቀደደው። መልእክተኛውም ይኼን ባየ ጊዜ በእጅጉ ተቆጣ። አባ ሳሙኤልንም ከግ ንድ ጋር አሥሮ አስደበደበው ከገዳ ሙም አስወጥቶ አሳደደው።

ከገዳሙ ወጥቶ ሲሰደድ መልአከ እግዚአብሔር አገኘውና ወደ ደብረ ቀልሞን መራው። በዚያም ምእመናንን ሁሉ በሃይማኖታቸው እንዲፀኑ እያስተማረ ጥቂት ጊዜ ተቀመጠ። ይኼንን ሠናይ ምግባሩን መቆዘዝ የተባለ የሃገሩ መኰንንና ሃይማኖቱን የካደው ሊቀጳጳሱ ሰሙ። ከሃዲያንም ሁሉ አንድ ሆነው መጡና ከደብሩ በድጋሚ አሳደዱት ከዚያ ወጥቶም በዚያው ሃገር ወዳለች ሌላ ቤተ ክርስቲያን ገባ።

በዚህ ዘመን በርበር የተባሉ የሰሜን አፍሪካ ዘላን ጐሳዎች (አረማውያን) ወደ ደብሩ መጡና አባ ሳሙኤልን አሥረው በግመል ላይ ጫኑት። ግመሏ ግን አባታችንን ተሸክማ ልትንቀሳቀስ አልቻለችም እንደ በለዓም አህያ ብዙ ጊዜ ቢገርፉአትም ተቀምጣ ዝም አለች። በርበሮችም ነገሩ እንዳልተሳካላቸው ባዩ ጊዜ ትተውት ሄዱ። አባሳሙኤልም ወደ ደብሩ ተመልሶ ተጋድሎውን ቀጠለ።

በሌላ ጊዜም እኚሁ አረማውያን ደግመው ወደ ደብሩ መጡ አባ ሳሙኤልም እግዚአብሔር ከእነዚህ አሕዛብ እንዲሰወረው አብዝቶ ለመነ። በዚህም ጊዜ «ሳሙኤል ሆይ አትፍራ ነገር ግን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ገብተህ ተቀመጥ ዝም በል ምንም ቃል አትተንፍስ እኔም ከእጃቸው አድንሃለሁ» የሚል የእግዚአብሔር ቃል ወደርሱ መጣለት። እንደተነገረውም ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ገብቶ ተደበቀ።

በርበሮቹ የጦር መሣሪያቸውን እንደ ታጠቁ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ገብተው ንዋያተ ቅዱሳቱን ማተራመስ ጀመሩ። በተቀደሰው ሥፍራም የማይገባ ኃጢአትን አደረጉ። አባ ሳሙኤልም አላስችለው አለ ነገር ግን «አትናገር ዝም በል» የሚለው ኢያሪኰን ለሚዞሩ እሥራኤላውያን የተነገረው ቃል ለርሱም መነገሩ ትዝ አለው አረማውያኑ የሚሠሩትን እያየ ሊታገሥ ባለመቻሉ «እናንተ ፈሪሃ እግዚአብሔር በልባችሁ የሌለ አረማውያን በዚህ በተቀደሰ ሥፍራ ገብታችሁ ምን ትሠራላችሁ» ብሎ ተናገረ እነርሱም «እኛስ የምንፈልገው አንተን ነበር ለካንስ ተደብቀሃል» ብለው ከምሰሶው ጋር ግጥም አድርገው በማሰር ለሞት እስኪደርስ ገረፉት። ደሙንም እያፈሰሱ ወስደው በግመል ጫኑት።

አባ ሳሙኤል ሕመሙ ስላሳቃየው ይጮኸ ጀመር። በዚህ ሰዓት የተቀመጠባት ግመል በልሳነ ሰብእ– በሰው ቋንቋ «ሳሙኤል ሆይ ላንተ መገረፍ ብቻ ሳይሆን መሞትም ይገባሃል፤ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አፍርሰህ ማን ጩህ ብሎሃል» አለችው። አባ ሳሙኤልም ይኼንን በሰማ ጊዜ የአምላኩን ቃል መጣሱ ትዝ ብሎት መሪር ዕንባ አለቀሰ «በእውነት እግዚአብሔርን በድያለሁ» እያለ ልቡ በሐዘን ተሰበረ።



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ከዚያ በኋላ በግመሏ ጭነው ወደ ሃገራቸው ወሰዱት። አባ ሳሙኤልን የገዛው ሰው ፀሐይን የሚያመልክ ነበረ። ሰይጣንም በሰውየው ልቦና ገብቶ አባታችንን ይፈትነው ዘንድ ወደደ። ጌታውም በዝሙት አባ ሳሙኤልን ሊጥለው ስላሰበ ከአንዲት ሴት ባርያ ጋር እግሩን አሥሮ ወደ በረሃ ግመል ጥበቃ ላከው። አባ ሳሙኤል ግን ወደ እግዚአብሔር እየጸለየ ፈተናውን በመቋቋም ልቡ በእምነቱ ፀና።

የጌታው ጤንነትም መታወክ ጀመረና የበረታ ደዌ ወደቀበት። የሃገሩ መድኃኒተኞችም ሊያድኑት ባለመቻላቸው ነፍሱ ተስፋ ቆረጠች። አባ ሳሙኤልም ነገሩን እንደሰማ ወደ ጌታው ቀርቦ ጸለየለት። በዚህም ጊዜ ከጠና በሽታው ተፈወሰ። ጌታውም በእጅጉ ተደንቆ በአባ ሳሙኤል እግር ሥር ተንበረከከና «የበደልኩህን ሁሉ ይቅር በለኝ» እያለ አለቀሰ። ከእግሩም ሥር ወድቆ «የምትፈልገውን ሁሉ ንገረኝ አደርግልሃለሁ» ይለው ጀመር።

በዚያ ሃገር የነበሩ ድውያን ሁሉ ይኼንን ድንቅ ተአምር ሲሰሙ ወደ አባ ሳሙኤል መጡ እርሱም ዘይት እየቀባ በጸሎቱ ይፈውሳቸው ነበር። ከዚያ በኋላ አባ ሳሙኤል ወደ ገዳሙ ለመመለስ ተነሳ። ጌታውም ለገዳሙ መርጃ የሚሆን ብዙ ገንዘብ ሰጥቶ ሸኘው።

ወደ ደብረ ቀልሞን በደረሰም ጊዜ የመንፈስ ልጆቹ ሁሉ በደስታ ተሰባሰቡ እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በዚያ ተገለፀችላቸውና «ይኼ ቦታ ለዘለዓለም መኖሪያዬ ይሆናል» ብላ የምሥራች ነገረቻቸው ከዚያች ዕለት ወዲያ አረማውያኑ በድጋሚ አልመጡም። አባ ሳሙኤልም እጅግ የበዙ ድርሳናትና መጻሕፍት ቅዱሳትን ጻፈ። ጊዜ ፍልሰቱም በደረሰ ጊዜ ልጆቹን ሰብስቦ «እግዚአብሔረን ፍሩ ትዕዛዛቱንም አክብሩ» እያለ አስተማራቸው። በመጨረሻም ታኅሣሥ 8 ቀን በሰላም ዐረፈ። ፀሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን። ✣

(ስንክሳር ታኅሣሥ 8)

# በመገለጥ ላይ መገለጥ

ከግርማ ወ/ሩፋኤል

እግዚአብሔር ለመረጣቸውና ለወደዳቸው እርሱን ደስ በማሰኘት በፊቱ በእምነት ለተጓዙት በጸጋ ላይ ጸጋን ይሰጣቸዋል። ከክብርም ወደ ክብር ያሸጋግራቸዋል አብርሃም ተጠራ በእምነትም ጥሪውን ተቀበለ፥ ወደ ማያውቀው አገር ተሰደደ ለእግዚአብሔርም በሁሉ በኩል ታዘዘ ለዚህም እግዚአብሔር ሃብትን፥ ዘር በነጠፈበት ሰዓት ልጅን፣ በጠላቶቹም ፊት ሞገስን ሰጠው አሕዛብም በእርሱ እንዲባረኩ የአሕዛብ ሁሉ አባት አደረገው። በክብር ላይ ክብር በጸጋ ላይ ጸጋ ማለት ይኼ ነው። ሌሎችም ብዙ የእግዚአብሔርን ጥሪ የተቀበሉና በፈቃዱ የተመሩ ቅዱሳን ከክብር ወደ ክብር ተሸጋግረዋል፥ በጸጋም ላይ ጸጋን አግኝተዋል።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር በተመላለሰባቸውና የማስተማር ሥራውን በፈጸመባቸው ወራት፥ ከቦታ ቦታ ሳይመርጥ ፈቃዱ በሚፈጸምበት ሥፍራ ሁሉ እየተገኘ እውር ሲያበራ፥ ጐባጣ ሲያቀና፥ ሙት ሲያስነሳ፥ ሰዎችን በችግራቸው፣ በሃዘናቸውና በደስታቸው ጊዜ ሁሉ እየተገኘ ሲረዳቸው ነበር። አንድ ጊዜ ከገሊላ ባሕር በስተሰሜን የጴጥሮስ የእንድርያስና የፊልጶስ አገር ወደ ሆነች አነስተኛ ከተማ ከደቀመዛሙርቱ ጋር መጥቶ ዕውር አበራ። ይህ ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ዕውር የነበረ ሰው እስከዚያች ሰዓት አጥቶት የነበረውን ብርሃን ሲያገኝ በመገለጥ ላይ መገለጥ ደረጃ በደረጃ ነበር። (ማር.8፥22–26) ለዚህም የመጀመሪያው ደረጃ:-

1ኛ. ከመንደር መውጣት

«...እውርም አመጡለት እጁንም ይዞ ከመንደር ውጭ አወጣው» የዚህች ትንሽ ከተማ ቤተሳይዳ ነዋሪዎች ለጌታ እንደፍላጐቱ ትልቅ ስጦታን አመጡለት። «እናንተ ሸክማችሁ የከበደ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ (ማቴ.11፥28) የሚለውን ጥሪ ሰምተው ስለነበር ዓይነ ሥውር አቀረቡለት። ጌታ ወገናችንን ያድንልናል ከሸክሙም ይገላግለዋል፥ የብርሃን አምላክ ነውና ብርሃን ይሰጥልናል ነበር የቤተሳይዳ ሰዎች እምነትና ሃሳብ ስለዚህም ገና ከተማዋን እንደረገጣት ተሽቀዳድመው የሚዳስሰውን አመጡለት።

ዛሬ በየቤታችን ዓይናቸው ኃጢአትንና ጽድቅን መለየት አቅቶት የታወረባቸው፥ እግራቸው ወደ ቅድስና ሥፍራ (ቤተ ክርስቲያን) መራመድ ተስኖት ሽባ የሆነባቸው፥ አንደበታቸው እውነትን መናገር አቅቶት ዱዳ የሆነባቸው፥ ልቦናቸው ክፋትንና ተንኮልን በማሰብ የደነደነባቸው ስንት በሽተኞች አሉን? በንስሐው፣ ብደበሉ፣ በእምነቱ፣ በቁርባኑ በወንጌሉ ሲገባን ዝም ብለናቸዋል። ነገር ግን አምላካችን የብርሃን አምላክ ነውና እውራንን ይፈልጋል (ዮሐ.1፥4–9)፥ የሰላም አምላክ ነውና ሰላም ያጡትን ይፈልጋል (ዮሐ.14፥27)። ነፃነትን የሚሰጥ የነፃነት አምላክ ነውና በኃጢአት ባርነት የተያዙትና የታሰሩትን ይፈልጋል (ሉቃ.4፥7)። ለዚህም ነው ጌታ በቤተ ፋጌ የታሰሩትን አህዮች እንዲያመጡለት ደቀመዛሙርቱን ሲልክ «ሂዱና የታሰሩትን አህዮች አምጡ። ለምንድነው ብለው ሰዎች ቢጠይቋችሁ ለጌታ ያስፈልጉታል» በኋቸው ያለው (ማቴ.21፥1–3።)

መድኃኒታችን የቤተሳይዳውን አይነሥውር ሲያድነው እጁን ይዞ እየጐተተ ከመንደር አወጣው ብዙው ጊዜ ሰዎች እውነተኛ ብርሃንና መዳን በዚያችን በኃጢአት መንደር ከኃጢአት ጋር የሚገኝ እየመሰላቸው ይሳሳታሉ። ከእግዚአብሔርም የሚቀርብላቸውን የነፃነት ጥሪ ሲቃወሙት ይሰማሉ ይታያሉም። በተለያዩ የሱሶች፥ የስካርና የዝሙት መንደር ውስጥ በባርነት ሆነው ሲያምልኩ ይፈልጋሉ። እግዚአብሔር ግን እጅግ ጐትቶ ነፃ ካወጣ በኋላ በነፃነት የሚመለክ አምላክ ነው። ከኃጢአት መንደር ወጥተን የተለየን ሆነን እንድናመልከው ይፈልጋል። ያማ ባይሆን አብርሃም ከወገኖችህ ተለይተህ ውጣ ባልተባለ፥ እሥራኤላውያን የግብጽን የኃጢአት ጭቃ እያቦኩ በዚያው እያሉ ማደሪያ ድንኳን ስራ ባላቸውና እንዲያው ከግብጽ ሊያወጣቸው ለአርባ ዓመታት በምድረ በዳ ባላንከራተታቸው ነበር። እናም የእግ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ዚአብሔርን ብርሃን ለማግኘት ከኃጢአት መንደር መውጣት ይገባል።

ምን ይታወቃል በእግዚአብሔር ቤት ያለንና በአገልግሎቱ ላይ የተሰማራንም ሰዎች በራሳችን ሥልጣንና ፈቃድ የመጣንና እያገለገልን ያለን ይመስለን ይሆናል? ነገር ግን አይደለም። ተሳስተናል። የቅዱሳንን ልመና ሰምቶ አምላካችን ከመንደር ጐትቶ አወጣን ለዚህም አበቃን። እናም በሥልጣናችን ምንም ማድረግ ስለማንችል ይህ ያወጣን አምላክ በሕይወታችን ምን እንደሚያደርግልን አናውቅምና እሥራኤላውያን የኢያሪኮን ግንብ ለማፍረስ ዝም ብለው 13 ጊዜ እንደዞሩት ዝም ብለን በእምነት የእግዚአብሔርን ሥራ እንመልከት።

2ኛ የመጀመሪያው መገለጥ

«...በዓይኑም ተፍቶበት፥ እጁንም ጭኖበት አንዳች ታያለህን? ብሎ ጠየቀው አሻቅቦም ሰዎች እንደዛፍ ሲመላለሱ አያለሁ» አለ።

ይህ ዓይነ ስውር ታዛዥ ሆኖ ከመንደር ስለወጣ የመጀመሪያው ዳበሳ ተፈጸመበት። በጌታ እጅ ተዳበሰ። እግዚአብሔር በቤቱና በእጁ ያሉትን ሁልጊዜ ይዳብሳቸዋል። ዓይነሥውሩም ዓይኑ ተገለጠለት። ነገር ግን አንድ ጊዜ ብቻ ስለተዳበሰ የደበዘዘ ዕይታ ታየው፥ ዛፍና ሰዎችን መለየት ተሳነው። በዘመናችንም ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ከመንደሩ ካወጣቸው በኋላ ጥቂት ጊዜ ብቻ በቃሉ ስለተዳበሱ አብዛኛውና የሚያዩት ነገር የደበዘዘ ነው። ኃጢአትንና ጽድቅንም መለየት ተስኗቸዋል። ጉቦ መቀበሉ፥ በሐሰት መመስከሩ፥ ሰነድ መሰረዝና መደለዙ፥ በትዳርና በኑሮ ላይ በዝሙት፥ በስካርና በቅናት ችግር መፍጠሩ ስለደበዘዘባቸው የጽድቅ ሥራ ይመስላቸዋል። አንዳንዶቹ ደግሞ በሚገባ በእግዚአብሔር ቃል ስላልተዳበሱ። የሚያመልኩት ጌታ ፍጡር የሁን ፈጣሪ፥ አማላጅ ይሁን ተማላጅ ጠፍቶባቸዋል። ታዲያ በዚህ በደበዘዘ የዕይታ ወቅት ነበር ዘወትር በቤተ ክርስቲያን እየተገኙ በእግዚአብሔር ቃል ተደጋግሞ መታሸት ለሁለተኛም መገለጥ መብቃት።

3ኛ ሁለተኛ መገለጥ

«...ከዚያም በኋላ ደግሞ እጅን በዓይኑ ላይ ጫነበት፥ አጥርቶም አየ ዳነም። ከሩቅም ሳይቀር ሁሉን ተመለከተ።»

ከፍፁም ዕውርነት ለደበዘዘ እይታ የበቃው ሰው በጌታ እጅ በመቶየቱና ማየት አለማየቱን ሲጠየቅ እንደደበዘዘበት ስለተናገረ ለሁለተኛ ዳበሳ በቃ። በዘመናችን ሰዎች በእግዚአብሔር ቤት ለመቶየት ትዕግስቱን ያጣሉ። ትንሽ ፈተና ሲገጥማቸው ገና አንድ ጊዜ ብቻ እንደተዳበሱ በርግገው ይጠፋሉ። በቤቱ እየኖሩ በጌታ እጅና ቃል ተደጋግሞ መታሸት ምንኛ መታደል ነው። ተደጋግመው በእግዚአብሔር ቃል የታሹ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር በሰማይ ለክብራቸው ያዘጋጀላቸው ስለሚታያቸው በዚህ ምድር ያለው ኃላፊና ጠፊው ምናቸውም አይደለም። ዘወትር በፊታቸውም በቀራኒዮ የተሰቀለው ጌታ ስለሚታያቸው ኃጢአትን ለመስራትና ለማየት ጊዜና ቦታ የላቸውም። እዚህቹ ቅርብ ምድር ላይ ያለው ብቻ የሚታያቸው ደግሞ ዘለዓለማዊውና የማያልፈው ክብር ስለማይታያቸው እርስ በርሳቸው ይቀናናሉ፥ ለሚያልፍ ሥልጣንና ለሚጠፋ ገንዘብ ራሳቸውን ይሸጣሉ። ፈጣሪያቸውንም እስከመካድ ይደርሳሉ።

አንዳንዶች በተለይም በእግዚአብሔር ቤት የቆዩና በአገልግሎት ላይ የተሰማሩ ሰዎች ራሳቸውን እንደተልቅ ስለሚቆጥሩና እንደደበዘዘባቸው መናገር ስለሚከብዳቸው ለሁለተኛው ዳበሳ አይበቁም። በሕይወታቸውም ላይ ለውጥ አይታይም። ለዚህም ነው በሩቅ ያለውና እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸው አክሊል ስለማይታያቸው ለምድራዊ ሥልጣንና ክብር የሚሮጡት። (ማር.10፥37)። እግዚአብሔር አምላካችን በቤቱ ሳለን ያልሆነውን ነኝ እንድንለው ሳይሆን እኛነታችንን እንድንገልጽለትና ትንሽነታችንን እንድናስታውቀው ይፈልጋል። ጌታ ሆይ፥ የወይን ጠጅ አልቋልና ሙላልኝ (ዮሐ.2፥1–10።) ደካማ ነኝና አበርታኝ፥ ታምሜያለሁና ፈውሰኝ፥ ኃጢአተኛ ነኝና አንፃኝ እንድንለው ይፈልጋል። ይህማ ባይሆን ኖሮ ንስሐና ጸሎት ባላስፈለገም ነበር።

4ኛ ከመገለጥ በኋላ ያለ ህይወት

«...ወደ መንደርም አትግባ በመንደሩም ለማንም አንዳች አትናገር»

ብዙው ጊዜ በንስሐ በመታደስ፥ ሕይወቱም በመለወጥ ላይ ያለ ክርስቲያን አይወድቁ ውድቀት የሚወድቀው ገና በእግዚአብሔር ቃል ጠንክሮ በሁለት እግሩ ሳይቆም በዚያች በኃጢአት መንደር ውስጥ ያሉትን አወጣለሁ ብሎ ቀድሞ ይውልባቸው ወደነበሩት ሥፍራዎች ሲመለስ ነው። ሌሎችን አወጣለሁ ብሎ ለራሱ በዚያው ቀልጦ መቅረት ይመጣልና «የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች» እንዳይሆንብን መጠንቀቅ ይገባናል። ለዚህ ነው ጌታ ሌላውን በመንደር ያለውን ከጨለማ ሕይወት ለማውጣት የበቃህ አይደለህምና ለራስህ አትግባ በዚያም ለማንም እንዳትናገር ያለው እርሱ ሳይፈቅድና «ሂዱ ተናገሩ» ሳይለን አንዳች ማድረግ አንችልምና እስቲ በመጀመሪያ እኛ እንቁም።

እግዚአብሔር በሕይወታችን እጅግ የሚያዝነው ወደመጣንበት መንደር ስንመለስና የቀደመውን የጨለማ ህይወት መኖር ስንጀምር ነው። ሎጥና ቤተሰቦቹ ከሰዶም ሲወጡ ወደዚያች ኃጢአት ወደበዛበት ከተማ እንዳይመለከቱ ታዘዙ። እግዚአብሔርም «ራስህን አድን፥ ወደ ኋላህ አትይ በዚህም ዙሪያ ሁሉ አትቁም እንዳትጠፋም ወደ ተራራው ሸሽተህ አምልጥ» (ዘፍ.19፥17) አለው። የሰዶምና የገሞራ ቃጠሎ ወላፈን እንዳይነካው ፍፁም ለመዳን በዙሪያው መቆም እንደሌለበትና መሸሽ እንዳለበት አዘዘው። እርሱ ትዕዛዝ አክብሮ ወደፊት ገሠገሠ። ሚስቱ ግን ወደኋላዋ አየች የጨውም ሐውልት ሆና ቀረች። ወደመጡበት መንደር መመለስ በአካባቢውም መቆም ውጤቱ ይኼ ነው። እናም ፍፁም ለመዳን መጀመሪያ እንውልባቸው የነበሩትን ቦታዎች መለወጥ ይገባናል። ለዚህም ከሁሉም በላይ አቅም አውቆ መሸሽ ጠቃሚ ነው። በአካባቢው ብንቆም በመጀመሪያ ከኃጢአት አውቆ መሸሽ ጠቃሚ ነው። በአካባቢው ብንቆም በመጀመሪያ ከኃጢአት ታዛቢ ብንመስልም ተሳታፊ ለመሆን ጊዜ አይፈጅብንም። ለሁሉም «አንተ ግን የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ ከዚህ ሽሽ ጽድቅንና እግዚአብሔርን መመሰል፥ እምነትንም ፍቅርንም መጽናትንም የዋህነትንም ተከታተል» 1ጢሞ.6፥11 ❖



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ዓምደ ወራዙት

(የወጣቶች ዓምድ)

በዚህ ዓምድ ለመንፈሳውያን ወጣቶች የሚጠቅሙ ማናቸውንም ዓይነት ትምህርቶች፥ ምክሮችና አስተያየቶች እናስተናግዳለን።

ይህንን የቅዱስ ጳውሎስ ቃል ስናነሣ የፈረንጆቹ አባባል ትዝ ይለናል። «ጓደኛህን ንገረኝና አንተ ማን እንደሆንክ እነግርኻለሁ» ይላሉ። የሀገራችንም ሰው «ከአህያ የዋለች ጊደር...» ብሎ መተረቱም ጓደኛ በሰዎች ሕይወት ላይ ያለውን ተጽእኖ ለማሳየት ነው። ክቡር ዳዊትም በመዝሙሩ

«ከቸር ሰው ጋር ቸር ሆነህ ትገኛለህ ከቅን ሰው ጋር ቅን ሆነህ ትገኛለህ ከንጹሕ ጋር ንጹሕ ሆነህ ትገኛለህ፥ ከጠማማም ጋር ጠማማ ሆነህ ትገኛለህ፥ መዝ.17፤18–25። ብሎ መናገሩ ይህንን ዐቢይ ቁም ነገር የሚያመለክት ነው።

የቤተ ክርስቲያን ብርሃን የተባለው ቅዱስ ጳውሎስ በ2ቆሮ.6፥14–15 ላይ «ብርሃን ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው» ብሎ እንደተናገረው ፀሐየ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ የዋጃቸው ክርስቲያኖችም ብርሃን ናቸውና ማቴ.5፥14። የጨለማን (የኃጢአትን) ሥራ ከሚሠሩ፥ በእምነት ከማይመስሏቸው ጋር ጓደኝነትን ሊፈጥሩ አይገባቸውም። ምክንያቱም ዲያብሎስ መርዙን ለመርጨት የማያምኑ ሰዎችን ለመጠቀም ወደ ኋላ አይልምና።

1. የሔዋንና የእባብ ጓደኝነት፤ ዘፍ.3፥4–8።

የማይገባ ግንኙነት ከማይገባ ሰው ጋር ማድረግ መጨረሻው ሞት ነው። ሔዋን የአዳምን ድምፅ እየሰማች ረዳቷ እርሱ ብቻ መሆኑን እያወቀች እግዚአብሔርን እያመሰገነች ትኖር ዘንድ ታዘዘች። እንዳትበላ የተነገራትን ዕፀ በለስን ሁልጊዜ ብታያትም ተመልክታት አታውቅም ነበር። አበው «አይን ሳይሆን ልብ ነው የሚያየው» የሚሉት ለዚሁ ነው።

አንድ ቀን የቀን ጉደሎ፥ ሔዋን ሌላ ትምህርት ሰማች፥ ሌላ ምክር ተቀበለች፥ መስማት የማይገባትን ድምፅ ሰማች ማየት የማይገባትን (ዕፀ በለስን) አየች፥ መሄድ ወደማይገባት ሄደች፥ የማይገባትን ቀጠፈች፥ የማይገባትን አላመጠች ዋጠች የሔዋን ሰውነት በሙሉ በደለ፥ ጆሮ፥ ዐይን፥ እግር፥ አፍ፥ ሆድ በሙሉ በደለኞች ሆኑ። ሔዋን የወደቀችው ገና የእባብን ድምፅ በሰማች ጊዜ ነው።

## ከፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል

ከኤፍሬም እሸቴ

ውድ አንባብያን!

ከማን ጋር እንደምትውሉ፥ ምን እንደምትሰሙ ምረጡ። ብዙ ሰዎች በእምነት ከማይመሳሰሏቸው ጋር ጓደኝነት ይመሠርታሉ። ውኃ ሲወስድ አሳስቆ እንዲሉ በዚያው ቀልጠው የቀሩ፥ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን የተለዩ አያሌ ናቸውና ጓደኝነታችንን እንመርምር።

2. የዲና እና የአሕዛብ ልጆች ጓደኝነት። ዘፍ.34፥1–31።

የመፍቀሬ እግዚአብሔር ያዕቆብ ልጅ የነበረችው ዲና በአንድ ወቅት እግዚአብሔርን ከማያምኑ ካልተገረዙት ጣዖታውያን ከነበሩት ወገን ሄዳ ጓደኝነትን ጀመረች። «ብርሃን ከጨለማ ጋር የሌለውን ኅብረት ልትመሠርት ሞከረች። በመጨረሻም ሴኬም የተባለው አሕዛብ ከእርሷ ጋር ተኛ፥ አስነወራትም። ሁለተኛ ልታገኘው የማትችለውን ንጽሕናዋን ሜዳ ላይ አጣች። በእግዚአብሔርም በሰውም ዘንድ የተናቀች ሆነች። በእርሷም ምክንያት ብዙ ደም ፈሰሰ። ይህ ሁሉ የደረሰው የማይገባ ግንኙነት (ጓደኝነት) በመመሥረቷ ነበር።

ብዙ ወጣቶችም ዛሬ ይህን ነገር ሲፈጽሙ ይታያል። በየዳንስ ቤቱ፥ በጫት መቃሚያ ኪዮስኮች የሚደፈሩ ወጣት ልጃገረዶች ቁጥር አሁንም ጥቂት አይደለም። የደቂቃ ኃጢአት ለዓመታት ጠባሳው አይሽርምና የማይገባ እርግዝና ያመጣል ወይም ከዚያ ለመሸሽ በሚደረግ ውርጃ የብዙ እህቶች ለጋ ሕይወታቸው ይቀጠፋል። ከዚህ ሁሉ በፊት ግን ክርስቲያን ወጣቶች በተለይ የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች ሊኖራቸው ስለሚገባው ጓደኝነት ሊያጤኑ ይገባል። በእምነት ከማይመስሉን ጋር ጓደኛ መሆን የዲናን ታሪክ ይደግማልና እንጠንቀቅ።

3. የአምኖንና የኢዮናዳብ ጓደኝነት። 2ሳሙ.13፥1–39።

አምኖን የክቡር ዳዊት ልጅ ነው። ትዕማር የምትባል ውብ እህፅ ነበረችው። በአባት አንድ ሲሆኑ በእናት ግን የተለያዩ ነበሩ። እሳት የሆነ ወጣትነቱ ገፋፋውና ትዕማርን እጅግ በጣም ወደዳት፥ ታመመ፥ ከሳ። ይህን የሰማ ጓደኛው ኢዮናዳብ ምክር መከረው። በዘዴ እህቱን እንዲደፍራት ገፋፋው።

አምኖንም የጓደኛውን ምክር ሙሉ በሙሉ በተግባር አዋለ ትዕማርን በጉልበቱ አስነወራት። ነገር ግን እንዳልታመመላት፥ እንዳልከሳላት ሁሉ አሁን በጣም ጠላት። በዚህም ምክንያት የትዕማር ታላቅ ወንድም አቤሴሎም በሠይፉ የአምኖንን



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

አንገት ቀንጥሶ ጣለው። የክፉ ጓደኛ አይዞህ ባይነት

አምኖንን ለመቀላት አደረሰው።

ለአምኖን ሞትን የገዛለት ጓደኛው ነው፥ በእኩይ ምክሩ። ዛሬም የኢዮና ዳብን ምክር የሚመክሩ ብዙ ሰዎች አሉ።

- ሲጋራ አጢያጤስ፥
- ጫት አቃቃም፥
- ዳንስ አደናነስ የሚያስተምሩ ጓደኞቻችን በሙሉ የሕይወታችን ፀሮች ናቸው።

በጓደኞቻችው መካከል «ያልሠለጠነ» ላለመምሰል፥ ኃጢአትን እየተለማመዱ ከእግዚአብሔርና ከቤተክርስቲያን የተለዩ ብዙዎች ናቸው።

ክርስቲያኖች ምርጫችሁን አስተካክሉ የሰዎች ምክር ከቤተክርስቲያን የሚለያችሁ ከሆን መተዉ ይመረጣል። አምኖንን አስቡት፥ ክፉ ጓደኞች እንዳሉ ሁሉ የሰውን ነፍስ የሚያድኑ፥ ከእግዚአብሔር የተጣላን ሰው የሚያስታርቁ፥ በጨለማ (በኃጢአት) የነበረውን ወደ ብርሃን (ጽድቅ) የሚመልሱም አያሌ ናቸው።

«የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና» ማቴ.5፥9

1. የዮናታንና የዳዊት ጓደኝነት

«ዮናታንም ዳዊትን...እነሆ እኛ ሁለታችን በእኔና በአንተ በዘሬና በዘርህ መካከል ለዘላለም እግዚአብሔር ይሁን ብለን በእግዚአብሔር ስም ተማምለናል አለው።» 1ሳሙ.20፥42። ዮናታን የንጉሥ ሳኦል ልጅ ነው። አባቱ ሳኦል ዳዊትን ዐይኑ በጠላው ጊዜ ያዳነው ልጅ ዮናታን ነው። ለአባቱ አድልቶ፥ ክፉ ሥራውን ደግፎ ሳይረዳው የዳዊትን ነፍስ ያዳነው ዮናታን ነው። መሐላውን የጠበቀ እውነተኛ ጓደኛ ነው። ዛሬ መሐላቸውን የማይጠብቁ ብዙ ጓደኞዎች አሉ። አብረው ያወሩትን ምሥጢር በአደባባይ የሚያውጁ አያሌ ናቸው።

2. የናትናኤልና የፊልጶስ ወዳጅነት ዮሐን.1፥46።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማስተማር በጀመረ ጊዜ ፊልጶስን ይከተለው ዘንድ ጠራው ለናትናኤልም እውነተኛውን መድኃኒት ያሳየው ወደ ዓለም የመጣውን ብርሃን ያስተዋወቀው ጓደኛው ፊልጶስ ነው።

ክርስቲያኖች ወንድሞቻችሁንና እኅቶቻችሁን ክርስቶስ ወደሚገኝበት ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጡ ዘንድ አመልክቷቸው፤ ወደ መጠጥ ቤት፥ ወደ ፊልምና ዳንስ ቤት፥ ወደ ምሽት ክበብ ሰዎችን ከመገፋፋት ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥራት ፊልጶስን መሆን ነው።

በማታ የቤተክርስቲያን ጉባዔዎች በሰ/ት/ቤቶች ቃሉን መስማት የጀመራችሁ፥ በክህነት የምታገለግሉ አገልጋዮች በሙሉ የዚህ ባለዕዳዎች ናችሁ።

3. የኤማሁስ መንገደኞች። ሉቃ.24፥13–35።

የጌታችን ትንሣኤ የጌታ መነሥት በደቀመዛሙርት መካከል ትልቅ የመነጋገሪያ ነጥብ በነበረበት ወቅት ከደቀመዛሙርት መካከል ሁለቱ ኤማሁስ ወደምትባል ቦታ ይጓዙ ነበረ። ያወሩት የነበረው ወሬ ስለ ጌታ ትንሣኤ ነበረ። እርሱ እንደመንገደኛ አብሮዋቸው ይሄድ ጀመረ። ከነቢያት ጀምሮ ስለእርሱ የተነገረውን ነገር እያነሣ ይተነትንላቸው ነበረ፤ ነገር ግን አላወቁትም ነበረ። ጊዜው በመምሸቱ ወደቤታቸው ገብቶ ያድር ዘንድ ለመኑት ገበታ ቀርበው የተባረከውን እንጀራ በበሉ ጊዜ ዐይናቸው ተከፈተ ዐወቁትም። በዚህ ጊዜ ከእነርሱ ተሰወረ።

ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ሲናገር «...ከአብ ዘንድ የነበረውን ለእኛም የተገለጠውን የዘላለምን ሕይወት እናወራላችኋለን» 1ዮሐ.1፥2። ብሎ ክርስቲያኖች የሚያወሩት ምን እንደ ሆነ ይናገራል። የኤማሁስ መንገደኞች የፈጸሙት ይህንኑ ነው። ወሬያቸው በቀራንዮ የተሰቀለው በሦስተኛው ቀን የተነሣው ኢየሱስ ክርስቶስ ነበረ።

ወጣቶች ሲገናኙ ዛሬ ስለምንድን ነው የሚያወሩት? እውነተኛ ጓደኛ ስለክርስቶስ ስለቤተክርስቲያን፥ ስለቅዱሳን አባቶቻችን ያወራልናል። ስለዚህ አፋችን የሚያወራውን ጆሮአችንም የሚሰማውን እንምረጥ።

የተወደዳችሁ አንባብያን!

ወጣትነት የእሳትነት ወቅት ነው። ሁሉ ነገር ውብና መልካም መስሎ የሚታይበት ወቅት ነው። በዚህ ወቅት ሁለት ዓይነት ኃጢአት ወጣቶችን ይጠብቃቸዋል።

1. የድፍረት ኃጢአት፥

«የድፍረት ኃጢአት እንዳይገዛኝ ባሪያህን ጠብቅ። መዝ.18፥13

በጓደኞቻቸው ግፊት ብዙ ጊዜ በድፍረት ኃጢአትን ሲፈጽሙ ይታያሉ። ድብድብ፥ ትዕቢቱ፥ ዝሙቱ፥ ስካሩ ለቤተሰብ፥ ለቤተክርስቲያን፥ ለአባቶች አለመታዘዙ በሙሉ የዚህ ውጤት ነው።

ሁላችንም ግን የፀፀት ጸሎት መጸለይ ይገባናል።

«የድፍረት ኃጢአት እንዳይገዛኝ ባሪያህን ጠብቅ።»

2. የልጅነት (የዐለማወቅ) ኃጢአት።

«የልጅነቴን ኃጢአትና መተላለፍ አታስብብኝ» መዝ.24፥7።

ብዙ ወጣቶች ጓደኞቻቸው የመከሯቸው በዓይናቸው የሚመለከቱት ነገር በሙሉ መልካም ስለሚመስላቸው በማይወጡበት የኃጢአት ማጥ ውስጥ ሲዘፈቁ ይታያሉ። ለዚህ ነው በዓለም ከሚፈጸሙት ብዙ ግድያዎች መካከል አብዛኛዎቹ የሚፈጸሙት በወጣቶች የሆነው። ለዚህም የሚገፋፉቸው አብዛኛዎቹ የሃሺሽ የኰኬይንና የሌሎችም አደንዛዥ ዕፅዋት ጥገኛ መሆናቸው ነው።

አንባብያን!

ዐለማወቅ (ልጅነት) ከእግዚአብሔር ቅጣት አያድንምና ወደ ቤተክርስቲያን መመለስ ይገባል። እንግዲህ እግዚአብሔር ሊጠቀምበት የሚገባውን ለጋ ዕድሜ፥ መልካም ዕውቀት ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርገን አቅርበን፥ ሰውነታችንን ቀድሰን በወጣትነታችን እግዚአብሔር ተደስቶ የክብሩ ወራሾች ለመሆን እንድንችል እግዚአብሔር ይርዳን። ✣

ይቆየን።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ምክንያተኝነት

ብዙዎቻችን ንስሐ ላለመግባታችን የምናቀርባቸው ምክንያቶች

1. ሁሉም የሚኖረውን የኃጢአት ኑሮ ነው የምኖረው፤ ከዚህ ሁሉ የኃጢአት ኑሮ መሐል ተለይቼ እንዴት ብቻዬን ልለወጥ እችላለሁ?

ኖኅ ኃጢአት ከበዛበት ዓለም ተለይቶ በቅንነትና በፍጹምነት ኖረ እንጂ አካባቢውን አልመሰለም። ዘፍ.7፥23።

ይህንን ዓለም አትምሰሉ ሮሜ.12፥2።

ዮሴፍ በግብፅ ሀገር ብቸኛ እግዚአብሔርን አማኝ ሆኖ ኖረ እንጂ የግብፅን አማልክት አላመለከም ዘፍ.18፥32።

ነቢዩ ዳንኤልና ሠለስቱ ደቂቅ በባቢሎን ሀገር እግዚአብሔርን አመለኩ እንጂ ለንጉሡ ጣዖት አልሰገዱም (ዳን.1፥8።)

አንተም እንዲሁ ኑር።

2. ችግር በዝቶብኝ ነው፤ አልመቸኝ እያለኮ ነው፤

- የቅፍርናሆም ሰዎች ሽባውን ወደጌታ የሚያስጠጉበት መንገድ ቢያጡ የቤቱን ጣራ አንሥተው አስገቡት እንጂ መንገድ የለም ብለው አልተመለሱም። ማር. 2፥1–9። አንተም የችግርህን ጣራ አንሣ።
- ካንጀት ካለቀሱ ዕንባ አይገድም።
- ዘኪዎስ ቁመቱ ጌታን ከማየት ቢያግደው ‹አጭር ነኝና ምንም አይለኝ› ሳይል ዛፍ ላይ ወጣ።

አንተም ለራስህ ራስህ የምታቀርበውን ምክንያት አትቀበል። ራስህን አሸንፈህ ወደ ንስሐ ቅረብ እንጂ።

3. ሳልበድል መኖር አልችልም፤ ኑሮዬ ራሱ ከኃጢአት አያርቅም፥ እኔ እምቢ ብል ሌላው እሺ አይልም።

- ዮሴፍ አገልጋይ ነው። እመቤቱ የምታዝዘውን ሁሉ መፈጸም ነበረበት። ለዝሙት ስትጋብዘው ግን በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአትን አልሠራም አለ። ዘፍ.39፥9።
- ዳዊት በቅንአት ያሳድደው የነበረውን ንጉሥ ሳኦልን በአንድ ወቅት በእጁ ሲወድቅለት ልግደለው አላለም ጋሻ ጃግሬዎቹ እንኳን እንግደለው ቢሉት። ነገር ግን «እግዚአብሔር የቀባው ነውና እጄን አልጥልበትም» አለ። 1ሳሙ.24፥4። ቆራጥ ከሆንክ ማንም ወደ ኃጢአት አይመራህም።

4. ሕገ እግዚአብሔርን መፈጸም ከባድ ነው። እኔ ደግሞ ደካማ ነኝ።

- ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ። ፊልጵ.4፥13።
- ዳዊት በጐልያድ ፊት ሲቀርብ ወታደር አልነበረም ምግብ ሊያደርስ የመጣ እንጂ። ነገር ግን በእግዚአብሔር ተማመነ ጐልያድንም አሸነፈ። 1ሳሙ.17፥41–32።
- አባታችን አብርሃም «ልጅህን ሰዋልኝ» የሚለው ትእዛዝ ሲመጣ አልችልም አላለም በእምነት ጸና እንጂ። ዘፍ.22፥2።
- እኔ ካንተ ጋር ነኝና ከፊታቸው አትፍራ። ኤር.1፥8።

5. ወደፊት ንስሐ እገባለሁ ዛሬ ደስ ይበለኝ

- የተኛችው ሙሽሪት እግዚአብሔር በሩን ሲያንኳኳ ምክንያት እየደረደረች አሳለፈችው በኋላ ነቅታ ብትፈልገው ግን አጣችው ውጪቷም መደብደብና መደፈር ሆነ። መኃልይ 5፥6።
- አስተዳዳሪው ፊሊክስ ቅዱስ ጳውሎስ አጠገቡ ቆሞ ንስሐ እንዲገባ ሲነገረው በተመቸኝ ጊዜ ልኬ አስጠራኻለሁ ብሎ ዕድሉን አሳለፋት። ከዚያ በኋላ ግን ንስሐ ገባ የሚል ታሪክ የለውም። የሐዋ.24፥24–27።
- ይሁዳ አስቀድሞ ሲነግሩት አልሰማ ብሎ ክርስቶስን ከሸጠ ካስሰቀለ በኋላ ተፀፀተ ነገር ግን ውጤቱ ታንቆ መሞቱ ሆነ። ማቴ. 27፥1–5።

ስለዚህ ወንድሜ ሆይ አንተስ «የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ እንደ መራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግሥቱን ባለጠግነት ትንቃለህን? ሮሜ.2፥4። ✣

ከብፁዕ ወቅዱስ አብነ ሺኖዳ
ከRepentance and Purity
መጽሐፍ የተወሰደ

## መጽሐፈ ጨዋታ

- የአንበሳ ልጅ ክርስቶስ በበረት ከከብቶች ጋር ሲተኛ ምነው ሳይበረግጉ ቀሩ። ዳሩ ለምደውታል በሰማይ ዙፋኑን ተሸክመው የሚኖሩ እነዚሁ አይደሉ?
- አቁማዳን ገዝቶ አህያን፥ አህያን ገዝቶ አቁማዳን ከመለመን ቶማስ ሐዋርያን መግዛት ይሻላል እርሱ ሁሉንም ሆኖአልና።
- ጌታችን በደብረ ታቦር ለምን ኤልያስን ጠራው አብ በደመና እንደሚመጣ እያወቀ። ደመናና ኤልያስ ደግሞ ቂመኞች ናቸው – 3ዓመት ከ3 ወር ለጉሞት እሱም ይችን ዐውቆ አብ በደመና ሲመጣ ታቦርን ጥሎ ሸሸ።
- እኒህ ነቢያት እንዴት አድርገው በመንፈስ ቅዱስ ጠጅ ሰከሩ። በምሳሌ አዳራሽ ተሳሳቁ እኰ ያ ዳንኤል ድን ጋይ ከረዥም ተራራ አንሥቶ ሊፈጃቸው! ደግሞ የኤልሳዕ ይግረም ገንቦውን ይዞ መሮጡ። እኒያ እሴይና አሮን በትር ቢማዘዙ ብልጡ ሕዝቅኤል ደጁን ዘግቶ ጠፋ።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# መዳን በክርስቶስ ነው እንዴት?

ከዲ. ተክለ ወልድ

ባለፉት እትሞቻችን አንዳንድ የኑፋቄን እንክርዳድ የሚዘሩ መናፍቃን በበራሪ ጽሑፎቻቸው ላይ ያሰፈሩትን አግባብ ያልሆነ ትምህርት በመመልከት በቃሉ ምእመናን እንዳይሳሳቱ በማለት ቃል በቃል መልስ መስጠታችን የሚታወስ ነው። በዛሬው ጽሑፋችን ደግሞ ሀ. መዳን በመላእክት ወይም በቅዱሳን በኩል አይደለም ለ. መዳን በነቢያት አይደለም ሐ. መዳን ቅዱስ ቁርባንን ወይም ጥምቀትን በመቀበልና በመፈጸም አይደለም። በማለት ላቀረቡት ክህደት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ከቅዱሳት መጻሕፍት እየጠቀስን መልስ እንሰጥበታለን። እናስተምራለን። ስለማዳን ስንናገር የባሕርይ ማዳንና የጸጋ ማዳን ለማን እንደሆነ መለየት ይኖርብናል። የእግዚአብሔር አዳኝነት የባሕርይ ሲሆን የቅዱሳን ደግሞ የጸጋ ነው።

ሀ. መዳን በመላእክት ወይም በቅዱሳን በኩል አይደለም። ብለው የድጋፍ ጥቅስ ዕብራውያን አንድን ጠቅሰዋል። ዕብራውያን ምዕራፍ አንድ የሚያስተምረን በሥጋ የተገለጠ የመላእክት ፈጣሪያቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ከፈጠራቸው ከመላእክት እንደሚበልጥ መላእክቱ ለፈጣሪያቸው እንደሚሰግዱ መላእክቱን መናፍስት አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል ያደረገ እርሱ መሆኑን ነው። ከዚህ ውጪ መላእክትንና ቅዱሳንን የሚነቅፍ ወይም አያድኑም የሚል ጽሑፍ የለም። እንዲያውም በቁ 14 ላይ «ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?» በማለት እኛን ደካሞችን እንደሚያግዙን እንደሚራዱን በግልጥ ተቀምጧል። ሰው ደግሞ የሚያግዘውን መጥላት የለበትም። መላእክት የሚያግዙን ከሆነ በኃይልና በሥልጣን ከኛ ይበልጣሉ ማለት ነው። እግዚአብሔር እኛን እንዲያግዙን የሚልካቸው ከሆነ አንቀበልም ማለት አንችልም። መልእክተኛውን መቀበል ላኪውን መቀበል ነውና። እግዚአብሔር መላእክት እንዲያግዙን ወደ እኛ እንደሚልካቸው ሁሉ እኛም እንዲያማልዱን ወደ እርሱ እንልካቸዋለን።

ጌታ በወንጌል «እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል።» ማቴ.10፥40። ባለው መሠረት መልእክተኞቹን እንቀበላለን። እግዚአብሔር እነርሱ እንዲያድኑን ይልካቸዋል። «የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል። ያድናቸውማል።» የሚለው የሚያስተምረን ይኸንኑ ነው። መዝ.33፥7። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው ሰዎች እንዲድኑ የሚያግዙ ከሆነ የደካሞችን ጸሎት የሚያሳርጉ የእግዚአብሔርንም ምሕረት የሚያወርዱ ከሆነ መላእክትን ከሰው ልጅ የመዳን ምሥጢር ገለል ማድረግ አይቻልም።

ሐዋርያው ቅ.ጴጥሮስ በሰንሰለት ታሥሮ ወኅኒ ቤት በወቀደ ጊዜ ፈጥኖ የደረሰለት የእግዚአብሔር መልአክ ነበረ። ሰንሰለቱን ፈቶ የመጀመሪያውንና የሁለተኛውን የዘቦች ሥፍራ አሳልፎ ወደ ከተማው የሚያወጣውን የብረት መዝጊያ በተአምራት ከፍቶ አድኖታል። ቅ/ጴጥሮስ ራእይንም የሚያይ ይመስለው ነበር እንጂ በመልአኩ የሚደረገው እውነት እንደሆነ አላወቀም ነበረ። ዛሬም መላእክት በአማላጅነታቸው የሚፈጽሙት ገቢረ ተአምራት እንደ ራእይ የሚረቃቸው እንደ ህልም የሚርቃቸው አሉ። እንዲያውም መላእክት ያደረጉት ሲነገራቸው ሰይጣን ነው አስመስሎ ያደረገው ይላሉ። እግዚአብሔር በቅዱሳኑ አድሮ የሠራውን ሥራ ለሰይጣን መስጠት እግዚአብሔርን መድፈር ነው። ሰው እንዴት የእግዚአብሔርን ሥራና የሰይጣንን ሥራ መለየት ያቅተዋል። ኧረ ለመሆኑ ከሥልጣኑ የተዋረደው ርኩሱ ሰይጣን አስመስሎ መሥራት የሚቻለው ከሆነ ይልቁንማ ቅዱሳኑ በእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉን ለማድረግ እንዴት ይሳናቸዋል? ጌታ እኮ ለአገልጋዮቹ የሰጠው ጸጋ «የሚሳናችሁም ነገር የለም» የሚል ነው። ማቴ.17፥20። መላእክትም አገልጋዮቹ ናቸው።

ከቅ/ጴጥሮስ ወደ ልቡ ተመልሶ ጌታ መልአኩን ልኮ በመልአኩ እጅ ከሄሮድስ እጅና የአይሁድ ሕዝብ ይጠብቁት ከነበረው ሁሉ እንደ አዳነኝ አሁን በእውነት ዐወቅሁ አለ። ሐዋርያው ልባም በመሆኑ ዐወቀ። እንግዲህ ልብ አጥተን ዕውቀት የተሰወረብን ሁሉ ልብ ገዝተን ወደ ዕውቀት እንመለስ ዘንድ ይገባናል። በመጽሐፍ ቅዱስ የመላእክት አገልግሎት ሰፊ ነው። የሐዋ.12፥6–11።

ለ. መዳን በነቢያት አይደለም ብለው ዮሐ.1፥29ን ጠቅሰዋል። ይህ ጥቅስ የሚያስተምረን ዮሐንስ ኢየሱስ ወደ እርሱ ሲመጣ ዓይቶ «የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» በማለት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአዲስ ኪዳን በግ ሆኖ ሥጋውን በመቁረስ ደሙንም በማፍሰስ ከአዳም ጀምሮ በዘር የወረደውን ኃጢአት ለማስወገድ ወደዚህ ዓለም መምጣቱን ለሕዝቡ በዮርዳኖስ ዙሪያ ለኃጢአት ሥርየት ለተሰበሰቡት የመሰከረውን ምስክርነት ነው። በፊት ሰዎች ኃጢአት ባይሠሩም በአዳም ኃጢአት ምክንያት ይሞቱ ነበር። ዮሐንስ በአዳም ኃጢአት ምክንያት መሞትን የሚያስቀር ዳግማዊ አዳም መምጣቱን መሰከረ።

«ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና 1ቆሮ.15፥22። ቅዱስ ጳውሎስ ይኸንኑ ሲያብራራ «ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ፥ አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው ለእርሱ አምሳል ነውና» ብሏል እስከ ሙሴ ሲል ፍጻሜ የሌለው እስከ ነው። እስከ ክርስቶስ ማለቱ ነው። ሙሴ ለእሥራኤል ዘሥጋ መሪና ፈራጅ እንደነበረ የእሥራኤል ዘነፍስ መሪና ፈራጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና።

በአንድ በአዳም ኃጢአት ምክንያት ሞት ከአዳም ጀምሮ የበደሉትንም ያልበደሉትንም ገዝቶአቸው ነበረ። እነ አብርሃም እነ ኢዮብ ሞት ገዝቶአቸዋል። እንግዲህ ዮሐንስ በአዳም ኃጢአት ምክንያት መሞትን ለማስቀረት የመጣ ይህ ነው ብሎ መመስከሩ ነበረ። ሕዝቡማ በግላቸው የሠሩትን ኃጢአት በተሰጠው ጸጋ ተጠቅሞ በትምህርቱ አቅርቦ በንስሐ ጥምቀት በማስተስረይ አድኗቸዋል። ሕዝቡም ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ የተጠመቁት ለዚህ ነው። ማቴ.3፥6። ምሥጢሩ ይህ ሆኖ ሳለ ነቢያት አያድኑም ብሎ በድፍኑ የማይገናኝ ጥቅስ መጥቀስ ተገቢ አይደለም። ስለነቢያትስ ጌታ «ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል ብሏል ነቢያት የተቀበሉት ዋጋ የዘላለምን ሕይወት ነው። ነቢያት በእግዚአብሔር ጸጋ በአማላጅነታቸው የዘላለምን ሕይወት ያሰጣሉ ማለት ነው። የነቢይን ዋጋ መውሰድ ማለት ይኸው ነው። የመዳንም ምሥጢር የዘላለምን ሕይወት ማግኘት ነው። እግዚአብሔር በራሱ የፈጸመውን የማዳን ሥራና በቅዱሳኑ አድሮ የሠራውንና የሚሠራውን መለየት አቅቶን በጥርጣሬ ማዕበል እንዳንመታ ተናውጠንም እንዳንወድቅ ልንጠነቀቅ ያስፈልጋል።

ሐ. መዳን ቅዱስ ቁርባንን በመቀበል ወይም ጥምቀትን በመቀበልና በመፈጸም አይደለም። ከክርስቶስ ጋር የተሰቀለ ወንበዴ እነዚህን ሳያደርግ ድኖአል ብለው ሉቃ.23፥39–43። ያለውን ጠቅሰዋል። እስቲ ይህንን ወንበዴ በቅንነት እንመልከተው ሰዎች



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ባያውቁትም የዚህ ወንበዴ ከክርስቶስ ጋር መሰቀል በእግዚአብሔር ዘንድ አስቀድሞ የታወቀ ጉዳይ ነው። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «በቀኝና በግራ መቀመጥ (መሰቀል) ከአባቴ ዘንድ ለተዘጋጀላቸው ነው።» ብሎ ነበር ለደቀመዛሙርቱ፥ ማቴ.20፥23። ይህ ወንበዴ ተሰቅሎ የሚሞትባትን ደቂቃ እየጠበቀ ነበረ። በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነትም ያመነው በዚያች ቅጽበት ነው። የሚጠመቅበት የሚቆርብበትም ጊዜ አልነበረውም። ጌታ ሆይ በመንግሥትህ አስበኝ በማለቱ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ ብሎት ጌታ ይህ ወንበዴ ኢየሱስ ክረስቶስ ቀድሞት በመሞቱ በጦር ከተወጋ የጌታ ጐን የፈሰሰውን ውኃ በእምነት በማየቱ እንደ ጥምቀት በመስቀል ላይ የተቆረሰውን ሥጋውን የፈሰሰውን ደም በማየቱ እንደ ቆረበ ተቆጥሮለታል። ጥምቀትንም ሆነ ቁርባንን የመሠረተልን እኮ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ታዲያ እንዴት እንደቀላል ነገር አምዘግዝገን እንጥለዋለን? እሱ የመሠረተውን ትተን አዲስ ልንመሠረት ነው ወይ? ቅዱስ ጳውሎስ «ከተ መሠረተው በቀር ማንም ሌላ ሊመሠርት አይችልምና፤ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።» ብሏል 1ቆሮ.3፥11።

ኧረ ለመሆኑ መዳን ማለት ምን ማለት ነው? የዘላለምን ሕይወት ማግኘት አይደለምን? ጌታችን በወንጌል «እውነት እውነት እላችኋለሁ የወልደ አጓለ እመሕያው ክርስቶስን ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው» ብሎ አስተምሮናል። ዮሐ.6፥53። የአዲስ ኪዳን ቁርባን ይህ ነው ከዚህ በተመላለፍ ክርስቶስ ትድኑበታላችሁ ሕይወት ይሆናችኋል ብሎ የሰጠንን አያድናችሁም ሕይወት አይሆናችሁም ማለት ያመኑ እየመሰላቸው ክርስቶስን ሐሰተኛ እያደረጉት ነው። ክርስቶስ እኮ የማይሆነውን ይሆናል ብሎ አላስተማረም።

የቆመ የሚመስለው ማንም እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ ይላል ቅዱስ ጴጥሮስ በእነዚያ ዘንድ ለማስተዋል የሚያስቸግር ነገር አለ። ያልተማሩትና የማይጸኑትም ሰዎች ሌሎችን መጻሕፍት እንደሚያጣምሙ እነዚህን ደግሞ ለገዛ ጥፋታቸው ያጣምማሉ። እንግዲህ እናንተ ወዳጆች ሆይ ይህን አስቀድማችሁ ስለምታውቁ በዓመጸኞች ስህተት ተስባችሁ ከራሳችሁ ጽናት እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ» እንዳለን እንጠንቀቅ። 2ጴጥ.2፥61–17።

ጥምቀትንም በጥምቀቱ ባርኮ ቀድሶ የሰጠን እርሱ ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰማይ የምድር ንጉሥ ሲሆን ራሱን በትህትና ዝቅ አድርጎ በመጠመቅ አርአያ ሆነን አድርጉ ብቻ ብሎ ሳይተወን አድርጎ አሳየን። እርሱ አስፈልጎት ሳይሆን ሥጋን የለ በሰ እርሱ ለሥጋ ለባሽ ሁሉ የጥም ቀትን መንፈሣዊ ልደት ያስፈልገዋል ሲል ነው ለተመረጡ ሰዎች ለአገል ጋዮቹ ራስን ዝቅ ማድረግ እንዲገባ ንም አስተማረን። ዮሐ.1፥29።

ደቀ መዛሙርቱ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲያጠምቁ ያዘዛቸው እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ማቴ.28፥18። ጥምቀት የማመን ምልክትና ለኢየሱስ ክርስቶስ የሞቱና የትንሣኤው ምሳሌ ነው። ቆላ.2፥11፤ ሮሜ.1፥3። ጥምቀት ከውሃና ከመንፈስ በረቂቅ መንፈሣዊ ልደት ከእግዚአብሔር መወለድ ነው። ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም «ወደ እግዚአብሔርም መንግሥት አይገባም» ዮሐ.3፥3። ጥምቀት አዲስ ልደት ነው። ቲቶ.3፥5። በሥጋ ብቻ መወለድ አሮጌ ልደት ነው። በአሮጌ ልደት ደግሞ አዲሲቷን የእግዚአብሔርን መንግሥት መውረስ አይቻልም። በእምነት በተፈጸመ ጥምቀት ድኅነት ይገኛል። ማር.16፥16። በጥምቀት የክርስቶስ ወገኖች ሆነናል። ገላ.3፥24–29። ጥምቀት አንዲት ናት በዐቢይ ባሕር ቢጠመቁ በንዑስ ባሕር ቢጠመቁ በሊቀ ጳጳስ እጅ ቢጠመቁ በቄስ እጅ ቢጠመቁ ጥምቀት አንዲት ናት። ኤፌ.4፥5። በጥምቀት የኃጢአት ስርየት ይገኛል የሐዋ.2፥38። በብሉይ ኪዳን የኖኅ መርከብ፥ ግዝረት እሥራኤል ቀይ ባሕርን መሻገራቸው የጥምቀት ምሳሌዎች ነበሩ። 1ጴጥ.3፥20፤ ቆላ.2፥11፤ 1ቆሮ.10፥2። አንድ ሰው የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ የሚቀበለው ከተጠመቀ በኋላ ነው። ቅዱስ ጴጥሮስ የጰራቅሊጦስ ዕለት የሰበካቸውን ነፍሳት «...ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ» ብሏቸዋል። የሐዋ.2፥38። ጥምቀት ልጅነት የሚያሰጥ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው። ይህንንም ጸጋ ሕፃናት እንዳይቀበሉ የሚከለክል ሕግ የለም ኤርምያስ በእናቱ ማኅፀን እያለ ተቀድሷል። ኤር.1፥5። መጥምቁ ዮሐንስ በእናቱ ማኅፀን እያለ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቷል። በደስታም ዘሏል። ሉቃ.1፥15። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕፃናትን አቅርቦ አቅፏቸዋል። በእንብሮተ ዕድ (እጅ በመጫን) ባርኳቸዋል። ለመ ባረክ እስኪያምኑ ይጠብቁ አላለም። ቅዱስ ጳውሎስ የእስጢፋኖስን ቤተ ሰብ አጥምቋል 1ቆሮ.1፥16። ልድያ የተባለችው ሴት እና እነ ቅዱስ ጳውሎስ ታስረውበት ለነበረው ወኅኒ ቤት ዘበኛ የነበረው ሰው በጳውሎስ እጅ ከነቤተሰቦቻቸው ተጠምቀዋል። የሐዋ.16፥14፣34። ቤተሰብ ማለት ሕፃናትንም የሚጨምር ቃል ነው። ጳውሎስና ሲላስ የወኅኒውን ጠባቂ «በኢየሱስ ክርስቶስ እመን። አንተና ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ።» ማለታቸው የወላጆች እምነት ለልጆች እንደሚተርፍ የሚያሳይ ነው። ወላጆች አማኞች ከሆኑ ልጆቻቸውን በሃይማኖት ኰትኲተው በሥነ ምግባር አንፀው ያሳድጓቸዋል።

በብሉይ ኪዳን በእግዚአብሔር የሚያምኑ እናቶች ወንድ ሲወልዱ በአርባኛው ቀን ሴት ሲወልዱ በሰማኒያኛው ቀን ልጆቻቸውን ወደ ቤተ መቅደስ ወስደው ያስባርኩ ነበር። ይህ ንባብና ምሳሌ ነው። ትርጓሜው ምሳሌነቱ ለጥምቀት ነው። የአዲስ ኪዳን እናቶች በዚህ ምሳሌ ተመርተው ከአማናዊው ጥምቀት በመድረሳቸው ልጆቻቸውን ወንዶችን በአርባ ቀን ሴቶችን በሰማኒያ ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን ወስደው ያስጠምቋቸዋል። ያስባርኳቸዋል። ዘሌ. 12፥1–8።

ከእንግዲህ ወዲህ ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ በሮሜ.16፥17 ላይ «ነገር ግን ወንድሞች ሆይ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችኋለሁ። ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ።» እንዳለን ከመናፍቃን ትምህርት ፈቀቅ እንበል። እንሸሽ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት በአባቶቻችን ዘመን ዛሬም በእኛ ዘመን ወደፊትም በሚመጣው ትውልድ ዘመን ያው በመሆኑ እንደ ፋሽን ልዩ ልዩ በሆነ ዕንግዳ ትምህርት እንወሰድ ዕብ.13፥8። «ስለዚህ ከሰማነው ነገር ምናልባት እንዳንወሰድ ለእርሱ አብልጠን ልንጠነቀቅ ያስፈልገናል።» ዕብ.2፥1። «እንደ ስህተት ሽንገላ ባለ ተንኰል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህም እየተንሳፈፍን ሕፃናት መሆን ወደ ፊት አይገባንም።» ኤፌ.4፥14። ማንም በሚያባብል ቃል እና በሚያቆላምጥ ንግግር እንዳያስተን እንጠንቀቅ። ሮሜ.16፥18፤ ቈላ.2፥4። የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን አሜን። ✣



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ

በዚህ ዓምድ ክርስቲያኖች በማኅበራዊ ኑሯቸውን ልንመስል የሚገባንን በኅብረተሰቡ መካከል አገላለጣችንና የኦርቶዶክሳውያን ምእመናንን ኑሮ ለማውሳት ይሞከራል።

## እናቶች በቤተ ክርስቲያን

ከግርማ ወ/ሩፋኤል

የቤተ ክርስቲያን ነገር ሲነሣ የቅዱሳን እናቶች ገድልም ታላቅ ቦታ አለው። ብዙ እናቶች እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ ቤተ ክርስቲያንን አገልግለው ለቅድስና በቅተዋል። ከነዚህም ውስጥ መግደላዊት ማርያም፥ ሶስናና ዮሐና በገንዘባቸው ሉቃ.8፥2–3። እኅትማማቾቹ ማርታና ማርያም እንግዶችን በማስተናገድ፥ ዮሐ.12፥12። የማርቆስ እናት ማርያምና በፊልጶስዮስ ከተማ ትኖር የነበረችው ልድያ ቤታቸውን ለጸሎት ቤትና ለቅዱሳን ማረፊያ በመስጠት፥ የጢሞቴዎስ እናት አውንቄና አያቱ ሊይድ በጥሩ ልጅ አስተዳደግ፥ ፌቤንና ጵርስቅስ ለቅዱስ ጳውሎስ በመላላክ። ሮሜ. 16፥1–3። የድሆች ሁሉ መመኪያና የኀዙናን መጽናኛ በመሆን አገልግለዋል። ከአገራችንም እንደ ክርስቶስ ሰምራ ያሉ በጸሎት በመትጋት እንደ ወለተ ጴጥሮስ ሰማዕት በመሆን፥ እንደ መስቀል ክብራ እንግዶችን በማስተናገድና ቤተ ክርስቲያን በማሳነፅ (ለላሊበላ ቤተ ጊዮርጊስ) ለቅድስና የበቁ ብዙ ናቸው። እንዲህም ስማቸው በውል አይጠቀስ እንጂ ቅዱሳት እናቶቻችን ቴክኖሎጂ ባልዳበረበት ዘመን ፈትል ፈትለው የካህናትን ልብስ የቤተ ክርስቲያንን መጋረጃ የንዋየ ቅዱሳት አልባሳት የመዝመራንጃኖ በመፍተል፥ ስፌት ሰፍተው ሙዳይና መሶበወርቅ በማበርከት ቤተ ክርስቲያ ለእኛ እንድትደርሰን አድርገዋል። ዛሬም በዘመናችን እግዚአብሔር የቅዱሳት እናቶችን ዘር አላሳጣንም። ከላይ የተጠቀሱትን ቅዱሳት እናቶች አሠረፍኖት በመከተል ለቤተ ክርስቲያን የሚገባቸውን ድርሻ የሚያበረክቱ እናቶች አልታጡም። ከእነዚህም መካከል ዛሬ ለአብነት ያህል እግረ መንገዴን ወደ ደቡብ በተጓዝኩበት ወቅት በይርጋ ዓለም ከተማ ያገኘኋቸውንና ቅዱሳት እናቶችን እንዳስታውስ ያደረጉኝን ሁለት እናቶች አቀርባለሁ።

ወ/ሮ ኤልሳ ግርማ ይባላሉ (በስተግራ) የአራት ልጆች እናት ሲሆኑ 40ኛቸውን ዕድሜ አጠቃለው ወደ 45ኛው ዘልቀዋል። ለልደት በዓል ድራማ እየሠሩ ነበር ያየኋቸው። ብዙ ጊዜ እናቶች በሰ/ት/ቤት ገብተው በእንደዚህ ዓይነቱ ሕይወት ሲሳተፉ ዓይቼ ስለማላውቅ በመደነቅ ላነጋግራቸው ወሰንኩ። ድራማውን ጨርሰው ከመድረክ እንደወረዱ ተዋውቁአቸው ነገሩንም ገልጨላቸው ቀጠሮ አስያስኳቸው። በቀጠሮው ሰዓት ቤታቸው ስደርስ ፈገግታና ፍጹም ትህትና በተመላበት አኳኋን ከተቀበሉኝ በኋላ ወደ ውይይታችን ገባን። አነጋገራቸው ከዕለታት አንድ ቀን የቀብር ዕለት ወይም በክብረ በዓል ብቻ ቤተ ክርስቲያን ብቅ እንደሚሉት ሰዎች ዓይነት ሳይሆን ጠዋትና ማታ ከቤተ





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ክርስቲያን እንደማይለዩት ካህናት ዓይነት ነው። ውይይታችንንም እን ዲህ ጀመርን።

ሐመር - የብዙ እናቶች ተሳትፎ ወደ ማይታይበት ወደ ሰ/ት/ቤት እንዴት ሊገቡ ቻሉ።

ወ/ሮ ኤልሳ - የመጀመሪያው የሕይወቴ ዘመን እጅግ የሚያሳዝንና በኃጢአት የተመላ ነበር (ምንም አሁንም ኃጢአተኛ ብሆን ኃጢአተኛ መሆኔን በማወቄና በእግዚአብሔር ቸርነት በቤቱ በመኖሬ ደስ ቢለኝም) የሥልጣኔ ምልክት ስለሚመስለኝ ይህን አልወድም ነበር። የመጨረሻው ልጄ ተወልዶ የ8 ወር ሕፃን ሆኖ (አሁን 18 ዓመት ሆኖታል) ታመም ኩና ወሊሶ ጸበል ሄጄ ከሞት አፋፍ ዳንኩ። በዚያውም ጾም መጾምና ቤተ ክርስቲያን ማዘውተር ጀመርኩ። የዛሬ 10 ዓመት ገደማ በወጣቶች አስተባባሪነት እናቶች ብቻ በቤት ውስጥ ቃለ እግዚአብሔርን መማር ጀመርን ዘመኑም በጣም አስቸጋሪ ስለነበር ፖሊሶች ዘወትር ይሰልሉን ነበር። እኛም ይህንን ፈተና ለማለፍ መርሃ-ግብራችንን በአንድ ቤት ውስጥ ብቻ ከማድረግ በጽዋ መልክ አድርገን በየቤቱ መዘዋወር ቀጠልን። ለፈጣሪ ምሥጋና ይግባውና መከታ ተሉ ከበዳቸውና ፖሊሶቹም ተውን። ቆይተንም መርሃ-ግብራችንን ወደ ቤተክርስቲያን ወስደን በየሳምንት እሑድ እንዲሁም በወር አንድ ቀን በዓለወልድን እያስቀደስን የቻልንም እየቆረብን አጠንክርነው። ትንሽ ቆይ ተንም ዘወትር ከሰኞ እስከ ዓርብ በ11 ሰዓት መጸለይና መማር ጀመርን እስከ አሁንም በዚሁ መልክ ቀጥለናል።

ሐመር - አሁን በሰ/ት/ቤት ውስጥ አገልግሎትዎ ምንድን ነው?

ወ/ሮ ኤልሳ - እኔ እንኳ ብዙ የማገለግለው ወጣቶችና እናቶችን በማገናኘትና እንዲማሩ በማድረግ ክርስትናውን በስም ብቻ ተሸክመው ቤተ ክርስቲያን መምጣት የማይ ወዱትንና ቤተ ክርስቲያንን የሕይወት ምንጭ ሳይሆን መቀበሪያ ብቻ ያደረ ጓትን እናቶችና አባቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ በመቀስቀስ፥ አልፎ አልፎም ከወጣቶች ጋር ድራማ እሠራለሁ። ከሌሎች እናቶች ጋር በመሆንም በፊት በወጣቶች ላይ ብቻ ተጥሎ የነበረውን በትላልቅ በዓላት ነዳያንን የመመገቡን ሥራ አሁን እኛ ተረክበነዋል።

ሐመር - በሰንበት ት/ቤት (በቤተ ክርስቲያን) ውስጥ ባሳለፉት ሕይወት ያጋጠመዎት ችግር ወይም ደስታ ወይም ለየት ያለ ገጠመኝ ካለ ቢገልጹልኝ፥

ወ/ሮ ኤልሳ - ይህ ጉባኤያችን ከተጀመረ ወዲህ ለብዙ ዓመታት ተጣልተው የነበሩና ለግድያ የሚፈላ ለጉ ሰዎች ታርቀዋል። በዚህም በእ ግዚአብሔር ቤት ዕርቅና ሰላም እንዳለ ራስንም ዝቅ አድርጐ ይቅርታ መጠ የቅና ይቅር ማለት እንደሚቻል ተምሬአለሁ። ዕድሜያቸውን ሙሉ ጨሌና ዛር ወይም ቃልቻ የሚያ መልኩ ሰዎች እርግፍ አድርገው ትተውት ንስሐ ገብተው ለቅዱስ ቁርባን ሲበቁ በማየቴ ተደስቻለሁ። ለራሴም ከሦስት ጊዜ በላይ እስከሞት በሚያደርስ በሽታ ብጠቃም እግዚ አብሔር ይመስገንና በጸበል በመዳኔ በፈጣሪዬ እንድታመን አድርጐኛል። እናም በእግዚአብሔር ቤት በመሆኔ ቢሞላልኝም ቢጐድልብኝም በጣም ደስ ይለኛል። ለዚህም ሁሉ ምክንያቱ እንደቅዱስ ጳውሎስ ከአመጸኝነት በግድ መጠራቴ ሳይሆን አይቀርም ለካ ታውሮ መመለስ ፍቅርን ያጸናል።

ሐመር - በመጨረሻ በዕድሜ እርስዎን ለሚመስሉትና ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ምክንያት ለሚያ በዙ ምእመናን ምን ምክር ይለግ ሷቸዋል?

ወ/ሮ ኤልሳ - እኛ ሰዎች ደካ ሞች ነንና ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመ ሄድ ብዙ ምክንያቶችን እናነሣለን። ቤተ ክርስቲያን ስንሄድ ጤናችን የሚጐዳ ይመስለናል። በሆነው ባልሆ ነው የሚባክነው ጊዜአችንም ለቤተ ክርስቲያን ሲሆን ያጥረናል። ያሳዝነ ናል። ለዚህም ብዙ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንሂድ፥ ቃለ እግዚአብ ሔርን እንማር ተብለን ስንጠየቅ ያመኛል፥ ጊዜ የለኝም ሥራ ይበዛብ ኛል እንላለን። ነገር ግን ይህ ትክክል አይደለም። በጤና ለምናሳብበውም እግዚአብሔር ጤናን ካልጠበቀ ሰው ራሱን ጠብቆ የትም መድረስ አይችልም። ጊዜንና ንብረትንም እግዚአብሔር ካልባረከ ሁሉም ከንቱ ነው። አንዳንዶች ደግሞ ቁረቡ ሲባሉ ዕድሜአቸውን እየቆጠሩ ገና ልጅ ነኝ ይላሉ። ለመሆኑ ዛሬ እንሙት ነገ መቼ አውቀነው ነው ገና ልጅ ነኝ የምን ለው? እንደወጡ መቅረትስ አለ አይደል፥ ደግሞስ ቁርባንን ለአረጁ ትና በሞት አፋፍ ላይ ላሉት ብቻ ያደረገው ማን ነው? ብዙውን ጊዜ እኔ እንደማስበው ቁርባንን የሚከለክለን የዕድሜአችን መብዛትና ማነስ ሳይሆን ከኋላ ልንሠራ ወይም ልንኖርበት ያሰብነው ኃጢአትና የኃጢአት ኑሮ ነው። ለእንደዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች ምን ማለት እችላለሁ ራሱ ፈጣሪ ወደ ቤቱ ወደ ብርሃን ይጥራቸው እንጂ።

ስለሰጡኝ ትምህርትና ምክር ወ/ሮ ኤልሳ ግርማን አመስግኜ በዕ ድሜ እኩያቸው ወደሚሆኑ ጓደኛ ቸው ወደ ወ/ሮ ሙሉነሽ ጉልላት በስተግራ ወዳሉትና መጽሐፍ ቅዱስ ወደሚያነቡት ቤት አመራሁ። እርሳ ቸውም ፍጹም ክርስቲያናዊ በሆነ ፍቅርና ትህትና ከልጆቻቸው ጋር በመሆን ከተቀበሉኝ በኋላ ወደ ውይይታችን ገባን። ወ/ሮ ሙሉነሽን እንዴት በሰንበት ት/ቤት ውስጥ መሳተፍ እንደጀመሩ ጠየኳቸው። እርሳቸውም እድገታቸው ቤተ ክርስ ቲያን እንደሆነና ልጆቻቸው ሳይቀር ከሕፃንነታቸው ጀምሮ የሰ/ት/ቤት ተማሪዎች መሆናቸውን ገለጹልኝ። በመቀጠልም «ምንም ቤተ ክርስቲያን ባድግ በተክሊል ስላላገባሁ አልቆ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ረብኩም። በዚህም እንደማንኛውም ክርስቲያን ምንም አይሰማኝም ነበር። ነገር ግን 16 ዓመት የሞላው ልጅ ሳይታሰብ ድንገት በመኪና አደጋ ሞቶብኝ ሐዘን ተቀምጠን ሳለን ጓደኞቹ የሰ/ት/ቤት ተማሪዎች እቤት መጥተው ትምህርት ሰጡ። በዚህን ጊዜ በህሊናዬ አንድ ነገር መጣብኝ፤ ሩጦ ያልጠገበው ልጅ በድንገት የሞተ እኔ እናቱማ እንዴት አልሞት? አልኩኝ። ከዚያች ሰዓት ጀምሮ መቁረብ እንዳለብን ከባለቤቴ ጋር ተነጋገርን። ፈተና ቢኖርም እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ በዓመቱ ለሥጋ ወደሙ በቃን። በዚህም የእግዚአብሔርን ጥሪ አደንቃለሁ። ለካ በሐዘን ላይ እያለንም ይጠራናል» በማለት አስረዱኝ። በአነጋገራቸው መንፈሣዊ ብስለት እየተገረምኩኝ ወደ ቀጣዩ ጥያቄ አመራሁ።

ሐመር – በሰንበት ት/ቤት ያለ ዎት ተሳትፎ በምንድን ነው?

ወ/ሮ ሙሉነሽ – አብዛኛውን ጊዜ እኔ የማገለግለው እናቶችን ቤተ ክርስቲያንን የተማርኩትን ትምህርት በማስተማር ነው። እኔ በሕይወቴ የምጠላው በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ተሰብስቦ የማይሆን ወሬ ማውራትን ነው። በተለይም እኛ ሴቶች በወሬ በመታወቃችን በጣም አዝናለሁ። በዚህም ምክንያት በጽዋ ማኅበራት በልቅሶ ቤት እንዲሁም በየዕድሩና በየዕቁቡ ቤት ሁሉ በትንሹ የማውቃትን ቃለ እግዚአብሔር አስተምራለሁ። ከከተማ ውጪ ወደአሉትም አብያተ ክርስቲያናት በመሄድ የአካባቢውን እናቶችና አባቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ እቀሰቅሳለሁ። ከመንፈሳዊ እኅቶቼ ጋር በመሆን በገጠር የሚገኙትን የተዘጉ አብያተ ክርስቲያናት እያየን ጧፍና ዕጣን ገዝተን እናስቀድሳለን። ለዚህም በትርፍ ጊዜያችን ሥጋጃ እየሠራን ጥጥም እየፈተልን እንሸጣለን።

ሐመር – በመጨረሻም ለእናቶች የሚያስተላልፉት መልእክት ካለ?

ወ/ሮ ሙሉነሽ – ብዙ እናቶችም ሆኑ አባቶች ቃለ እግዚአብሔር ያውቃሉ። ነገር ግን መፈጸም ስለሚከብዳቸው መሸሽን ይመርጣሉ። እንደዚህ ያሉ ሰዎች ሁለት ጉዳት ነው የሚጐዱት ወይ ዐውቀውት አይፈጽሙ ወይንም ደግሞ አለማወቃቸውን አምነው ለመማር ራሳቸውን አላዘጋጁ ምክንያቱም እናስተምራቸው ብለን ጠጋ ስንላቸው ገና አንድ ከመናገራችን እነርሱ ሦስት አራቱን ያሸ ጐደጉዱታል። ታዲያ ምን ያደርጋል መንግሥተ ሰማያት በማወቅ ብቻ አትወረስ በመፈጸም እንጂ እንደዚያ ቢሆን ኖሮ ፈላስፎች ብቻ በገቡባት ነበር። እንደዚህ ያሉት ሰዎች በጣም አስቸጋሪዎች ስለሆኑ እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ካልጠራቸው ቃለ እግዚአብሔርን ሊማሩ በንስሐም ሊመለሱ አይችሉም።

ወ/ሮ ሙሉነሽም «ላይቀር መሞት የሚለውን መዝሙር ከዘመሩልኝ በኋላ ብዙ ሰዎች ሕይወት ከሆነው ከእግዚአብሔር ቃልና ከቤተ ክርስቲያን ርቀው በቁም በመሞት ላይ ይገኛሉና፣ እግዚአብሔር በቁም ከመሞት ያድነን» ብለውኝ ውይይታችንን ጨረስን። እኔም አሜን። ሁላችንንም ያድነን ብዬ አመስግኜና ተሰናብቼ ተለየኋቸው።

እንግዲህ ከእነዚህ ሁለት እናቶች ትልቅ ትምህርት ያገኘን ይመስለኛል። ኦርቶዶክሳውያን እናቶች እንዲሁም አባቶች ከዕለታት አንድ ቀን ለቀብር ወይም ለክብረ በዓል በዛቢባል ለሰንበት ቀን ለቅዳሴ ብቻ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ብቻ ሳይሆን ዘወትር የእግዚአብሔርን ቃል መማርን፣ ራሳችንን በንስሐ ለቅዱስ ቁርባን ማዘጋጀትን ባለን ዕውቀት ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን ማገልገል፣ ለቤተ ክርስ ቲያን መልካም ልጆችን ማፍራትን ከእነዚህ እናቶች መማር አለብን» እግዚአብሔርም ለዚህ ያብቃን አሜን።

✣

## ከቅዱሳን ሕይወት

አባታችን አባ መቃርስ በሚኖሩበት ገዳም ውስጥ ታዎሜጣስ የሚባል ገዳማዊ ነበር። ይህ ሰው ከገዳሙ እየወጣ ካንዲት ሴት ጋር ይውል ነበርና የገዳሙ አባቶች መጥተው ለአበምኔቱ ለአባ መቃርስ ነገሩት። አባታችንም ተው ልጄ ንጹሕ ነው አላቸው። በመጨረሻ ታዎሜጣስ ይባስ ብሎ ሴትየዋን ወደ ገዳሙ ይዟት መጣ። በዚህ ጊዜ መነኮሳቱ አሁንም ያደረገውን ለአባታችን ለአባ መቃርስ ነገሩት። እርሱም እየነገርነው ዝም ያለው ዝሙትን መፍቀዱ ነው ይሉኝ ብሎ ድምፅ እያሰማ ብዙ መነኮሳትን አስከትሎ ሄደ። ታዎሜጣስም የሰዎችን ድምፅ ሲሰማ በሴትየዋ ላይ ቅርጫት ደፋባት። አባ መቃርስም ይህንን በመንፈስ ተረድቶ በቅርጫቱ ላይ ተቀመጠና መነኮሳቱን ፈልጉት አላቸው። እርሱ ስለተቀመጠባት ሊያገኟት አልቻሉም። በዚህ ጊዜ አባታችን ንጹሑን ልጄን እንዴት ታሙታላችሁ ብሎ ተቆጥቶ ከቤት አስወጣቸው። ሁሉም ከሄዱ በኋላ አባታችን ታዎሜጦስን ልጄ ሆይ ፈጣሪህ በአንተ ላይ ሳይፈርድብህ በፊት አንተ በራስህ ላይ ፍረድ አለው። ታዎሜጦስም ተቀምጠህ ባታል አለና ነገረው። አባታችንም ሴትየዋን መክሮ ካባረረ በኋላ ለታዎሜጦስ ቀኖና ሰጠውና ወጣ። የወንድሙን ኃጢያት የደበቀ እውነተኛ አባት ስለሆነ ድንጋዮች ሁሉ እየተከተሉ መቃርስ በምድር እንደ አምላኩ ሆነ ብለው አመስግነውታል።

## እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ከሆነ

- ይጠብቅሃል። ዘፍ.28፥15።
- ምሕረት ይበዛልሃል። ዘፍ.39፥21።
- የምትሠራውን ሁሉ ያከናውንልሃል። ዘፍ.39፥2–3።
- ያሣርፍሃል። ዘጸ.33፥14።
- ታሸንፋለህ። ዘፍ.14፥9።
- አስተዋይ ያደርግሃል። 1ሳሙ.18፥14።
- አትናወጽም። መዝ.46፥5።
- ከመከራ ሁሉ ትወጣለህ። ሐዋ.7፥9–10።
- የሚቃወመህ አይኖርም። ሮሜ.8፥31።

ገዛኸኝ ዘርይሁን

ከአዋሳ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ለወላጆች

ልጆቻችሁ ሊኖሩላችሁ የምትፈልጉትን መልካም ኑሮ መጀመሪያ እናንተ ኑሩት። የእናንተ የኑሮ ፍሬ ሰላም፥ ደስታ፥ መተሳሰብ፥ ፍቅር መከባበር ከሆነ ልጆቻችሁም እንደዚያው ይሆኑላችኋል። ፍሬያችሁ ንዝንዝና ጭቅጭቅ ጠብና ዱላ፥ ስካርና ሐሜት ስድብና ግልምጫ ከሆነ ደግሞ ቢያንስ እንደናንተ ቢበዛ ከናንተ በላይ ሆነው ያስቸግሩዋችኋል።

ልጆቻችሁን ደብድባችሁ ገላምጣችሁ በሰው ፊት አታዋርዱዋቸው ራስን የመጣልና የዝቅተኝነት ስሜት ይሰማቸዋል። መንፈሳቸው ይላሸቃል። ራሳቸውን ከማንም አሳንሰው ስለሚያዩ ድንጉጦችና በኑሮ የሚጨነቁ ይሆናሉ፤ ከዚህ ይልቅ ምክሩዋቸው ለብቻ ወስዳችሁ በእግዚአብሔር ቃል ገሥጹዋቸው።

ልጅ መውለድ ብቻ ወላጅ አያሰኝም። በአካልም በመንፈስም ኮትኩቶ ማሳደግ ጭምር እንጂ። ስለዚህም በውጭው ዓለም የተበከለ አየር በስርቆትና ቅጥፈት በስድብና ተንኰል በቅናትና ምቀኝነት ሳይበክላቸው አስቀድማችሁ በእግዚአብሔር ቃል በመንፈሳዊ ሕይወት ቃኙዋቸው መጥፎውንና መልካሙን፥ ክፉውንና ደጉን በምክር አስተምሩዋቸው ለወላጅ መታዘዝና እግዚአብሔርን መፍራት ሰውን ማክበር ትምህርት መውደድን ሥራ ማፈቀርን በልባቸው ቅረፁባቸው እንደይስሐቅ የተባረኩ ይሆኑላችኋል።

ልጆቻችሁ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ክፉ ሥራን የሚጠሉ ይሆኑ ዘንድ ከልጅነታቸው ጀምሮ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሔድን መጸለይን ቅዱሳት መጻሕፍት ማንበብን፥ መስቀል መሳለም የንስሐ አባትን መውደድ አስተምሩዋቸው። ሠርታችሁም አሳዩዋቸው ያለበለዚያ ግን ዓለም በተንኮል ትምህርቷ ሞልታ ፍሬያችሁን ታበላሽባችሁና ጐረቤት ቀርቶ እናንተም የምትረግሙዋቸውና እነርሱ ብቻ ሳይሆን ወላጆቻቸው ጭምር በክፉ የሚነሱ ለሃገር ለወገን የማይጠቅሙ ሆነው ያድጋሉ።

ልጆቻችሁ የሚሠሩትን መልካም ሥራ ቢበላሽም አድንቁላቸውና ውደዱላቸው አመስግኑዋቸው ሸልሙዋቸው ወደ ካህናት አቅርቡና ሥራቸውን በፊታቸው ተናግራችሁ አስባርኩዋቸው በዚህ ጊዜ የመልካምን ሥራ ውጤት ይረዱታል። እግረመንገዳችሁን ክፉ ሥራ የሠሩ የደረሰባቸውን ንገሩዋቸውና ከራሳቸው ጋር እንዲያነፃፅሩ አድርጉዋቸው።

ልጆቻችሁ ቢያጠፉ በቁጣ አታስበርግጉዋቸው ድንጉጦች ይሆናሉ ከአቅም በላይ ፍርሃት ስለሚጫናቸው ስህተቱን በድብቅ መሠራት አለያም ደግሞ ሠርቶ መደበቅ ይጀምራሉ። ነገር ግን በተዘዋዋሪ መንገድ በሰው መስላችሁ ንገሩዋቸውና እናንተ እንዲህ አታድርጉ በሉዋቸው ያኔ ራሳቸውን በራሳቸው ይገሥፁታል። እግዚአብሔር የነርሱን ስህተት ተመሳሳይ የሠራውን ልጅ እንዴት እንደቀጣው ስትነግሩዋቸው ከራሳቸው ጋር ያዛምዱትና ፈቅደው ይናገሩታል። ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ያያል ብለው ስለሚፈሩ ከተደበቀ ስህተት ይቆጠባሉ።

ልጆቻችሁን ስታዝዙዋቸው በቁጣ አይሁን፥ የሚሠሩበት ምክንያትና የሥራውን ጥቅም አብራሩላቸው ያለበለዚያ በእልክና በትእዛዝ ብቻ የሚሠሩ ሰዎች ሆነው ያድጋሉ ሥራን ለመሥራት ትዕዛዝ ይጠብቃሉ። ካልሆነም ደግሞ የሚሠሩት ሥራ ምክንያቱን ስለሚያውቁትና ርካታ ስለማይሰጣቸው ስለጥራቱና ውበቱ ሳይጨነቁ ትእዛዝ ለመፈፀም ብቻ ይሠራሉ። ነገር ግን ሥራውን ከሠሩ እግዚአብሔር እንደሚወዳቸው እመቤታችን እንደምትባርካቸው ንገሩዋቸው። ያኔም የበለጠ እንዲ ወደዱና እንዲባረኩ በመሻት መል ካም ሥራን ይሠራሉ።

ለልጆቻችሁ የቅዱሳን ሥዕሎችን ከፊታቸው አድርገው የሚጸልዩበት ቦታ አዘጋጁላቸው ከት/ቤት ሲመለሱና ወደ ት/ቤት ሲሄዱ እንደ አቅማቸው መጸለይን አስተምሩዋቸው የእግዚአብሔር ፍቅር የቅዱሳን መውደድ ያድርባቸዋል። ሲያድጉም ይኼ ክርስቲያናዊ ሥርዓት አዲስ አይሆንባቸውም፥ በመሆኑም በችግር በፈተና በመጥፎ አጋጣሚ ከመጨነቅና ከመጠበብ ወደ መጠጥና ሱስ ሌሎች አልባሌ ቦታዎች ለመፍትሔ ከመሮጥ ይልቅ የእግዚአብሔርን መልስ የቅዱሳንን ረድኤት ወደ መጠየቁ ያዘነብላሉ።

በአጠቃላይ ልጆቻችሁ በመልካም ሁኔታ አድገው እንደ ይስሐቅ ታዛዥ፥ እንደ አቤል የዋህ እንደ ጢሞቴዎስ በቃለ እግዚአብሔር የተሞሉ፥ እንደ ቅዱስ አትናቴዎስ ለሃይማኖታቸው ቀናዒዎች እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ወቅት የማይለውጣቸው ይሆኑላችሁ ዘንድ የራሳችሁን ኑሮ ለክርስትና አስገዙ ልጆቻችሁን በመንፈሳዊ ዕውቀትና ሕይወት ኮትኩቱ

ልጅ – አባ ሳልመጻውት፥ ሳላስ ቀድስ፥ ንስሐ ሳልገባ፥ ሳልጸ ልይ እስከ ማታ ብጾም ከጽድቅ አይቆጠርልኝም?

አባ – እሱንማ ጅቦችስ ይጾሙት የለ እንዴ ልጄ!



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# በረከተ ወንጌል

ይህን ኃይለ ቃል የተናገረው ጻድቁ ካህን ዘካርያስ ነው። እርሱም በጌታ ትእዛዝና ሕግጋት ሁሉ ያለ ነቀፋ እየሄደ ከሚስቱ ከኤልሳቤጥ ጋር በአንድነት በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ነበረ። ይኸውም እግዚአብሔር የሚወደው ሕይወት ነው። ዘካርያስ በጨለማው ዘመን እንደ ብርሃን ታየ። «በመጥፎና በጠማማ ትውልድ መካከል ያለ ነቀፋ የዋሆችም ነውርም የሌለባቸው የእግዚአብሔር ልጆች እንድትሆኑ ሳታንጐራጒሩ ክፉም ሳታስቡ ሁሉን አድርጉ። በእነርሱም መካከል የሕይወት ቃል እያቀረባችሁ በዓለም እንደ ብርሃን ትታያላችሁ።» እንዳለ ማለት ነው። ፊል.2፥16።

ቅድስት ኤልሳቤጥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ ጌታንም እመቤታችንንም አመስግና ነበር። ገና ዮሐንስ በማኅፀኗ እያለ መንፈስ ቅዱስ አነቃቅቶ አስመስግኗታል። ያም ሕፃን ከማኅፀን ወጥቶ እንደ ቅ/ገብርኤል ቃል ስሙም ዮሐንስ በተባለ ጊዜ በዘካርያስም መንፈስ ቅዱስ አደረበትና ትንቢት ተናገረ። «ማንኛውም ትንቢት ከቶ ከሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።» ይላል። 2ጴጥ.1፥21።

ዘካርያስ «የእሥራኤል ጌታ አምላክ ይባረክ ጐብኝቶ ለሕዝቡ ቤዛ አድርጎአልና» ብሎ በማኅፀን ድንግል ስለነበረው አምላክ ተናገረ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው ናይን በምትባል ከተማ ሙት በማስነሣቱ በሥፍራው የነበሩ ሰዎች እግዚአብሔር ሕዝቡን ጐበኘ» እያሉ እግዚአብሔርን አመስግነዋል። ሉቃ.7፥16። እንደ ዘካርያስ ትንቢታዊ ቃል ሕዝቡን የጐበኘ ቤዛም የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ነቢዩ ዳዊት በመዝ.40፥13 ላይ «ከዘላለም እስከ ዘላለም የእሥራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ» እንዳለ ዘካርያስም «የእሥራኤል ጌታ አምላክ ይባረክ» በማለት አባቱን ዳዊትን መስሎ ተገኝቷል። ልጅ አባቱን መስሎ ሲገኝ ደስ ያሰኛል።

## የቅዱሱን ኪዳን አሰበ!!

ሉቃ.2፥67–79

ከዲያቆን ደጀኔ ሽፈራው

ቀጥሎም «ከጥንት ጀምሮ በነበሩት በቅዱሳን ነቢያት አፍ እንደ ተናገረ በብላቴናው በዳዊት ቤት የመዳን ቀንድን አስነሥቶልናል። ማዳኑም ከወደረኞቻችንና ከሚጠሉን ሁሉ እጅ ነው።» አለ። ዘካርያስ እንዳለው የመዳን ቀንድ የተባለ ኢየሱስ ክርስቶስ ከዳዊት ወገን እንዲወለድ ከጠላታችንም ከዲያብሎስ እጅ እንደሚያድነን አስቀድመው ቅዱሳን ነቢያት ትንቢት ተናግረዋል። ይኸውም ዳዊትን ከሳኦል እጅና ከጠላቶቹ በሥጋ እንዳዳነው ነፍሳትንም ከዲያብሎስ እጅ እንደሚያድን የተነገረ ነው። 2ሳሙ.22፥1። ቀንድ የሥልጣን ምሳሌ ነው። በዚህ ምሳሌ ዘካርያስ ኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊ ሥልጣን ያለው መሆኑን መናገሩ ነው። መዝ.131፥17 ላይ «በዚያ ለዳዊት ቀንድን አበቀላለሁ» የተባለውም ለዚሁ ነበረ።

ዘካርያስ ከልጁ ከዮሐንስ በኋላ ስድስት ወር ዘግይቶ በሥጋ የሚገለጠው አምላክ ወደረኛና ጠላት ከተባለ ዲያብሎስ እጅ የሚያድን መሆኑን ከተናገረ በኋላ «እንደዚህ ለአባቶቻችን ምሕረት አደረገ ለአባታችን ለአብርሃም የማለውን መሐላውን ቅዱሱን ኪዳን አሰበ። በእርሱም ከጠላቶቻችን እጅ ድነን በዘመናችን ሁሉ ያለ ፍርሃት በቅድስናና በጽድቅ እንድናገለግለው ሰጠን።» አለ። እግዚአብሔር ቃሉን ሳያጥፍ ኪዳኑን ሳያፈርስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ በማኅፀነ ድንግል ማደሩን የቤዛነት ሥራ የሚሠራበት ጊዜ መድረሱን ሁሉን ነገር ልክ እንደ ሚስቱ ኤልሳቤጥ በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ትንቢት ተናገረ። ጥንት አብርሃም ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ልጁን በመሠዊያ ላይ በእምነት በተወ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ ለሁለተኛ ጊዜ ከሰማይ ጠርቶት «እግዚአብሔር በራሴ ማልሁ ይላል። ይህን ነገር አድርገሃልና አንድ ልጅህንም አልከለከልህምና በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ። ...ዘርህም የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል። የምድር አሕዛብ ሁሉ በአንተ ይባረካሉ። ቃሌን ሰምተሃልና» ዘፍ.22፥16። ብሎ ነበረ።

የእግዚአብሔር መሐላው ለአብርሃም የገባው ቃል ኪዳን ይኸ ነበር። መሐላውን የሚያጸና ቅዱሱን ቃል ኪዳን ለልጅ ልጅ የሚጠብቅ አምላክ የምድርን አሕዛብ ሁሉ እርሱ ሊባርክ ከአብርሃም ዘር ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷም ነፍስ ነሥቶ ሊወለድ በማኅፀኗ አደረ። «የአብርሃምን ዘር ይዞአል እንጂ የመላእክትን አይደለም።» በማለት



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ቅ/ጳውሎስም የመሰከረው ለዚህ ነው። ዕብ.2፥16። የአብርሃም ዘር የተባለች ቅድስት ድንግል ማርያም ናት። ይህቺውም በአምላክ ኅሊና ታስባ የኖረች እግዚአብሔር ለእናትነት የመረጣት ለማደሪያነት ያዘጋጃት ምክንያተ ድኂን ያደረጋት ጥንተ አብሶ የሌለባት ንጽሕት ዘር ናት። «የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆንን እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር።» ብሎ ኢሳይያስም የተናገረው ይኸንኑ ነው። ኢሳ.1፥9።

እግዚአብሔር መሐላውን አስቦ በፍጻሜው ዘመን ሕዝቡ ያለ ፍርሃት በነፃነት እንዲያመልኩት ያለ ርኩሰት በቅድስና ያለኃጢአት በጽድቅ እንዲያገለግሉት አንድ ልጁን ሰጠ። «እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፥ ይኸውም ዲያብሎስ ነው። በሕይወታቸውም ሁሉ ስለሞት ፍርሃት በባርነት የታሠሩ የነበሩትን ሁሉ ነፃ እንዲያወጣ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ።» ዕብ.2፥14–15። የእግዚአብሔር መሐላው የቅዱሱ ኪዳኑ ዋነኛው ምሥጢር አብርሃም ልጁን ለእግዚአብሔር ሳይከለክል በመሠዊያ ላይ ስላቀረበው እግዚአብሔርም ወደፊት ለአብርሃምና ለዘሩ አንድ ልጁን ለመስቀል ሞት አሳልፎ መስጠትን እንደማይከለክል የሚያሳይ ነበር።

ዘካርያስ በመንፈስ ቅዱስ በተሰጠው ሀብተ ትንቢት ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ አስቀድሞ ከተናገረ በኋላ ብዙዎች «ይህ ሕፃን ምን ይሆን» ሉቃ.1፥66። ብለው ስለተደነቁበት ሕፃን ስለ ልጁ ስለ ዮሐንስ ተናገረ። ዘካርያስ ዮሐንስ ከመፀነሱም በፊት ቢሆን የምሥራቹን የነገረው መልአክ ቅ/ገብርኤል ስለ ሕፃኑ ሕይወት በሚገባ ነግሮታል። ሉቃ.1፥13–17። ከአብራኩ የተከፈለውን ያን ሕፃን በፍቅር ዓይን እያየ «አንተ ሕፃን ሆይ የልዑል ነቢይ ትባላለህ መንገዱን ልትጠርግ በጌታ ፊት ትሄዳለህና እንደዚህም የኃጢአታቸው ስርየት የሆነውን የመዳን ዕውቀት ለሕዝቡ ትሰጣለህ» አለው። ይህ አባባል ስለ ልጁ የመሰከረው እውነተኛ ምስክርነት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስም በጊዜው መስክሮለታል። «ምን ልታዩ ወደ ምድረ በዳ ወጣችሁ? ነፋስ የሚወዘውዘውን ሸምበቆን? ወይስ ምን ልታዩ ወጣችሁ? ቀጭን ልብስ የለበሰውን ሰውን? እነሆ ጌጠኛ ልብስ የሚለብሱና በቅምጥልነት የሚኖሩ በነገሥታት ቤት አሉ። ወይስ ምን ልታዩ ወጣችሁ? ነቢይን? አዎን እላችኋለሁ። ከነቢይም የሚበልጠውን እነሆ መንገድህን በፊትህ የሚጠርግ መልእክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ ተብሎ የተጻፈለት ይህ ነው» እያለ ጌታ ለሕዝቡ ተናግሯል። ሚል.3፥1። ሉቃ.7፥24–27። ዮሐንስ ነቢየ ልዑልነቱና መንገድ ጠራጊነቱ በምድራዊ አባቱ በዘካርያስ በሰማያዊ አባቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ተመሰከረለት። ዘካርያስ እንደተናገረው «ዮሐንስ በምድረ በዳ እያጠመቀ የንስሐንም ጥምቀት ለኃጢአት ስርየት እየሰበከ መጣ።» ብዙዎችም ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ ከእርሱ ይጠመቁ ነበር። ማር.1፥4።

ነቢየ ልዑል ዮሐንስ ቢፈጽሟት መንግሥተ ሰማያት የምታወርስ ወንጌል በመንግሥተ ሰማያት ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ልትሰበክ ነውና ንስሐ ግቡ እያለ መንገድ ጠረገ። የሰዎችን ልብ ለቃለ ወንጌል አመቻቸ። «ይህም ከላይ የመጣ ብርሃን በጐበኘበት በአምላካችን ምሕረትና ርኅራኄ በሞት ጥላ ተቀምጠው ላሉት ያበራል። እግሮቻችንንም በሰላም መንገድ ያቀናል ሲል ግልጥ አድርጎ ተናገረ።» ሉቃ.1፥78–79። ዘካርያስ የትንቢቱ ማሰሪያ ያደረገው ይኸንን ነው። የሚሆነው ሁሉ ጊዜውን ጠብቆ በእግዚአብሔር ምሕረትና ርኅራኄ እንደሚሆን መሰከረ።

ሚል.4፥2። «ነገር ግን ስሜን ለምትፈሩት ለእናንተ የጽድቅ ፀሐይ ትወጣላችኋለች።» እንደተባለ ፀሐየ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሕዝቅኤል ምሥራቅ ከድንግል ማርያም መውጪያው በደረሰ ጊዜ ዘካርያስ በትንቢቱ የተጐበኘው ከላይ በመጣ ብርሃን ነው አለ። እርሱም በሞት ጥላ ወድቀው ለነበሩ የሰው ልጆች ሁሉ የሕይወትን ብርሃን እንደሚያበራላቸው ገለጠ። ዘካርያስ የሰላም መንገድ ያላት ወንጌልን ነው። ሰው በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ሰላም የሚሆንለት በሕገ ወንጌል ሲመራ ነውና። አንድም ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰላሙ ፍጻሜ የሌለው የሰላም አለቃ በመሆኑ «እግሮቻችንንም በሰላም መንገድ ያቀናል» አለ። ኢሳ.9፥6–7። ከዚያ በፊት ዓለሙ ሰላም አልነበረውምና። የሚመላለሰው በጨለማ ነበረ። የጨለማ ጉዞ ደግሞ ሰላማዊ አይደለምና በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር መሐላውን ቅዱሱን ኪዳን በማሰቡ «በጨለማ የሄደ ሕዝብ ብርሃን አየ በሞት ጥላ አገርም ለኖሩ ብርሃን ወጣላቸው» የሚለው የሚፈጸምበት ቀንቀጠሮ እጅግ በጣም ቀረበ። ኢሳ.9፥2። እንግዲህ ይህ የኢሳይያስ ትንቢት መፈጸሚያው በደረሰ ጊዜ ዘካርያስ የተናገረው ትንቢት ከኢሳይያስ ትንቢት ጋር አንድ ሆነ። እግዚአብሔር የመረጣቸው ሁሉ የሚነሡበት ዘመን የተለያየና የተራራቀ ቢሆንም የሚያናግራቸው ቃል አንድ ዓይነት ነው። ዘካርያስ እርሱ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ከነበረበት ዘመን ወደ ኋላ 740 ዓመት ተጉዞ እንደ አባቱ ኢሳይያስ እንደ ተናገረ ሁሉ ይህም ትውልድ ወደ ኋላው መለስ ብሎ እንደ አባቶቹ መናገር አለበት። ቃሉን መለወጥ የለበትም የአባቶቹ መንፈስ አድሮበት ከሆነ እምነቱም ሥርዓቱም ትውፊቱም እንደ እነርሱ ይሆናል። ይህ ካልሆነ ግን አባቶቹ የተናገሩት ሌላ እርሱ የሚናገረው ደግሞ ሌላ ይሆናል። አንድ ሰው ቃሉ ከአባቶቹ እየተለየ ሲሄድ መሳሳቱን አውቆ ቶሎ መመለስ አለበት።

ዘካርያስ እግዚአብሔር ለአባቶቹ የተናገረውን ቃል ኪዳን ማሰቡን እንደተናገረ ሁሉ እመቤታችንም አስቀድማ «ለአባቶቻችን እንደተናገረ ለአብርሃምና ለዘሩ የዘላለም ምሕረቱን አስቦ እሥራኤል ብላቴናውን ረድቶአል።» በማለት ተናግራለች። ሉቃ.1፥54–55። ኪዳን ማለት ውል ስምምነት ማለት ነው። እግዚአብሔር ዓለሙንና ሕዝቡን የሚያስተዳድረው በቃል ኪዳን ሥርዓት ነው። በማናቸውም ቃል ኪዳን ውስጥ የቃል ኪዳን ሰጪና ተቀባይ የአቀባበል ምልክትና ተስፋ እንዲሁም የተስፋው ምልክት ይገኛሉ። ሰዎች ቃል ኪዳኑን ተቀብለው ቢታዘዙለት የቃል ኪዳኑን በረከት ይቀበላሉ። እግዚአብሔር ለቅዱሳን የሰጠውን ቃል ኪዳን መጠበቅ ለእርሱ መታዘዝ ነው። የአባቶችን ቃል ኪዳን መተው በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ ነው። «እውነትን በዓመፃ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአተኝነታቸውና በዓመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ይገለጣል።» ይላል። ሮሜ.1፥18።

እግዚአብሔር ለአዳም፥ ለኖኅ፥ ለአብርሃም፥ የገባው ቃል ኪዳን ነበረ። ይህም ኪዳን የምሕረት ኪዳን (ኪዳነ ምሕረት) ነው። ኪዳነ ምሕረት ደግሞ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት የምሕረት ቃል ኪዳን ሁሉ በእርሷ ተፈጽሟልና። ሰዎች ከጨለማ ወደ ብርሃን የወጣነው ሕይወት ያገኘነው፥ እግዚአብሔር ኪዳኑን አስቦ ቃሉን በመፈጸሙ ነው። ዛሬ ግን ብዙዎቻችን እግዚአብሔር ያደረገልንን ረስተን በጨለማ እየተመላለስን ነው። በሞት ፍርሃት ተከብበናል። በኃጢአት ቆሽሸናል። በበደል ረክሰናል። ከአንደበታችን ጽድቅ አይሰማም። በልቦናችን የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን አይታሰብም። ጠላታችን ሰይጣን ማርኮን ወደ ሲኦል እንደ ጠፍ ከብት እየነዳን ነው። እረኛ እንደሌላቸው በጎች ተቅበዝብዘናል። ስለዚህ አሁኑኑ ወደ ነፍሳችን እረኛና ጠባቂ እንመለስ። ዛሬም ለእኛ የሰጠንን ቅዱሱን ኪዳን ያስባል። ለእኛ የተሰጠን ኪዳን የሕይወት ኪዳን ነው። «ሥጋዬን የበላ ደሜንም የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው። በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።» ብሎናል ዮሐ.6፥53። ይህም አዲስ ኪዳን ነው። የአዲስ ኪዳንን በረከት ለማግኘት በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት በማመን አዲስ ሰው መሆን ያስፈልጋል። ከኃጢአት ወደ ጽድቅ የተመለሰ ከጨለማ ወደ ብርሃን የወጣ በኪዳኑ (በሥጋው ወደሙ) የጸና ሰው አዲስ ነው። «ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው» ይላልና። 2ቆሮ.5፥17። ከአሮጌ ሥራ ከኃጢአት ተላቅቀን በጽድቅ አዲስ ከሆንን አዲሲቷን ሰማይና ምድር እንወርሳለን። ራእ.21፥1። ስለዚህ ነገ ሳይሆን ዛሬ ለራሳችን አዲስ ልብና አዲስ መንፈስ እናድርግ እንዲህ ከሆነ በሕይወት እንኖራለን። ሁለተኛውን ሞት አንሞትም። ሕዝ.18፥31። ራእ.20፥14። የእግዚአብሔር ቸርነት የቅዱሳን የቃል ኪዳን በረከት ከእኛ ጋር ይሆናል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ምንጊዜም ቢሆን ቅዱሱን ኪዳኑን ያስባልና። የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን። አሜን ✤

## ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ

### 1. ጽንሐሕ

- 3 ገመዶቹ የሥላሴ ምሳሌ ሲሆኑ ከላይ አንድ መሆናቸው የአንድነታቸው ምሳሌ ነው። በገመዶቹ ላይ ያሉት 24ቱ ሻኩራዎች (በየገመዱ 8) የ24ቱ ካህናተ ሰማይ የሱራፌል ምሳሌ ናቸው።
- የፍሕሙ ማስቀመጫሙዳይ መሰሏ ዕቃ የእመቤታችን ምሳሌ ስትሆን ፍሕሙ ደግሞ የመለኮት ምሳሌ ነው።

### 2. መቅረዝ

- ሰባት መሆኑ የፍጹምነት ምሳሌ ነው። ሰባት በዕብራውያን ፍጹም ነውና።
- መቅረዝ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ነው። ራእይ.1፥20።
- የሚነዱት ሻማዎች የክርስቶስ ምሳሌ:- እርሱ ሞቶ ለእኛ ሕይወት ሆኖአልና ኢሳ.53፥5።
  - የቅዱሳን ምሳሌ:- የሚነዱና የሚያበሩ መብራቶች ናቸውና። ዮሐ.5፥3።
  - ብርሃኑ—ክርስቶስ ለእኛ የሰጠን ሕይወት፥
  - እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ። ዮሐ.8፥12።
  - የክርስቲያኖች ሕይወት ምሳሌ፥
  - እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ። ማቴ.5፥16።
  - በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ያበራሉ። ማቴ.13፥43።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org


# አስደሳች ዜና ለምእመናን

«ዓምድ ሃይማኖት» መጽሐፍ በድጋሚ ታትሞ በቅርቡ ለምእመናን ይደርሳል!! የብዙ ምእመናን ጥያቄ በመሆኑ የምእመናኑን ፍላጐት ለማሟላት ሲባል መጽሐፉን በድጋሚ ለማሳተም ተገደናል ። ዳሩ ግን ከአቅም ማነስ የተነሣ ፀአሁኑ ጊዜ የታተመው ኮፒ (ቅጂ) ብዛት አነስተኛ በመ ሆኑ መጽሐፉን ቀድማችሁ ታገኙ ዘንድ ከወዲሁ እናሳስባችኋለን ምንም እንኳን የኅትመት ዋጋ በእጥፍ ቢጨምርም በቀድሞው ዋጋ ላይ ምንም ያህል ጭማሪ አለመደረጉንም ልናሳስብ እንወዳ ለን ።

ስምዐ ጽድቅ ቍ. 4 ጋዜጣ

ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ በዚህ ዕትሟ የሚከተሉትን ቁም ነገሮች ይዛለች ።

— በጸበልና በአባትዋ ጸሎት በሃ ድንጋይ ከሆዷ ወጣላት!
— ለፈጣሪ የተነገረውን ለመሐመድ ?
— ከወንድሞቻችሁ መካከል ነቢይ አስነሳላችኋለሁ ለማን..........?
— ኦርቶዶክሳዊ ቤት
— ዛሬ ልብሱን ነገ ራሱን
እና ሌሎችንም አካታለች ያግኙአት ።




በስመ አብወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን ።

ከዚህ ቀደም ማርስ መንፈሳዊ መዝሙር ቤት ተብሎ ይጠራ የነበረው አሁን አርያም መን ፈሣዊ መዝሙር ቤት ተብሎ እንዲጠራ የተሰየመ መሆኑን ድርጅቱ ለሕዝበ ክርስቲያን ሲገልጽ በታላቅ ደስታ ነው ።

በቅርብ ቀን በዚሁ በአርያም መንፈሣዊ መዝሙር ቤት የመርጌታ አዲስ አዱኛን መን ፈሣዊ መዝሙር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ደንብ መሠረት ባማረ ያሬዳዊ ቅንብር አዘጋጅቶ ሊያቀርብ መሆኑን በታላቅ ትህትና ይገልጻል ።

ስልክ 75 21 35
የመ. ሣ. ቍ. 50855
አርያም መንፈሣዊ መዝሙር ቤት
አ.አ ኢትዮጵያ ።

የፊት ሽፋን ፎቶ ግራፍ ስላይድ በማዋስ ቀና ትብብር ለሚያደርግልን ለቱሪዝም ኮሚሽን በአንባብያን ስም ከፍ ያለ ምሥጋናችንን እናቀርባለን ።

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የአንድ ዓመት ውጤት



ዋጋ 3.00 ብር

ARTISTIC PRINTERS

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org